"ከእግዚአብሔር ትልቅ ነገርን ጠብቅ፣ ለእግዚአብሔር ትልቅ ነገርን ሥራ"
ዊልያም ኬሪ

# ወደ የግል መንፈሳዊ መነቃቃት የሚመራ መንገድ

*ተሻሽሎ የቀረበ እትም*

## በመንፈስ ቅዱስ መሞላት

ሄልሙት ሃውባይል

# ወደ የግል
# መንፈሳዊ መነቃቃት
# የሚመራ መንገድ

*ወደ የግል መንፈሳዊ መነቃቃት የሚመራ መንገድ* | *„Steps to Personal Revival“*

**አሳታሚ** | *Publisher*፡-
ሄልሙት ሃውባይል ከ የትንቢት ቃል የወንጌል አገልግሎት ጋር በመተባበር |
*Helmut Haubeil in cooperation with Yetnbit Kal Christian Ministries*
ሁለተኛውና ተሻሽሎ የቀረበ እትም | *2nd revised edition*
© 2010 ሄልሙት ሃውባይል | *2018 Helmut Haubeil*

Translated in Amharic from the 4th English version
Printed in Ethiopia

**አከፋፋይ** | *Distribution* ፡-
የትንቢት ቃል የወንጌል አገልግሎት | *Yetnbit Kal Christian Ministries*
የፖስታ ሳጥን ቁጥር 1655 | P.O. Box 1655
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ | Addis Ababa, Ethiopia
yetnbitkal@yahoo.com | www.yetnbitkal.org

Conception:
Simon Eitzenberger, www.desim.de
Producer:
Konrad Print & Medien, www.konrad-medien.de

**Contact and order in foreign languages:**
© Helmut Haubeil, Rosenheimer Str. 49
D-83043 Bad Aibling / Oberbayern – Germany
E-Mail: helmut@haubeil.net
Phone +49 (0)8061 4900712

The original is in German. Translations exist in Bulgarian, Croatian, Czech, Danish, English, French, Hungarian, Romanian, Russian, Serbian, Swedish, Polish, Portuguese, Spanish, Italian, Urdu (Pakistan), Filipino, Hindi (India), Telugu (India), Odiya (India), Mizo (India), Indonesia, Vietnamese, Kinyarwanda (Rwanda), Kirundi (Burundi), Amharic (Ethiopia), Afaan Oromo (Ethiopia), Tigrigna (Ethiopia). Translations into other languages are desired. Please get in touch with H. Haubeil, so that the aid can be checked.

**https://steps-to-personal-revival.info/ contains all translated languages for reading, printing and sending to others. There are testimonies, helps for churches, pastors and elders and valuable quotations.**

# ወደ የግል

# መንፈሳዊ መነቃቃት

# የሚመራ መንገድ

*ተሻሽሎ የቀረበ እትም*

## በመንፈስ ቅዱስ መሞላት

## ሄልሙት ሃውባይል

# ማውጫ


**7**

መግቢያ

**ወደ የግል መንፈሳዊ መነቃቃት የሚመራ መንገድ**

*በመንፈስ ቅዱስ መሞላት*

**9**

ምዕራፍ 1

**የየሱስ እጅግ ዉዱ ስጦታ**

*የሱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ምን አስተማረ?*

*ከየሱስ ክርስቶስ ኃይለኛ መልዕክት ጋር በደንብ ተዋውቃችኋልን?*

**20**

ምዕራፍ 2

**የችግሮቻችን ዋና መንስኤ ምንድን ነው?**

*ችግራችን የመንፈሳዊነት ይሆንን?*

*የመንፈስ ቅዱስ እጦት ይሆንን?*

**47**

ምዕራፍ 3

**ችግሮቻችን መፍትሔ አላቸው**

*እንዴት ደስተኛና ጠንካራ ክርስቲያን ወደ መሆን እናድጋለን?*

*መንፈስ ቅዱስ ሕይወታችንን የሚሞላው እንዴት ነው?*

**65**

ምዕራፍ 4

**በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ወይም ያለመሞላት ውጤቶች**

*በመንፈስ ቅዱስ በመሞላታችን ምን ጥቅም እናገኛለን?*

*በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ባንጸልይስ ምን እናጣለን?*

**90**

ምዕራፍ 5

**በተግባር ለማዋል የሚያስችል መፍትሔ**

*እግዚአብሔር ለእኔ ያለውን መፍትሔ ልተገብር እና*
*ልለማመድ የምችለው እንዴት ነው?*

*በመንፈስ ቅዱስ እየተሞላሁ መሆኔን እርግጠኛ የምሆነው እንዴት ብጸልይ ነው?*

**108**

ምዕራፍ 6

**በመንፈስ ቅዱስ ሙላት ዙሪያ የተከሰቱ ልምምዶች (ምስክርነቶች)**

*የግል ምስክርነቶች፣ የቤተክርስቲያናት፣ የሰበካ እና የዩንየን ቢሮ ተሞክሮዎች*

**122**

ተጨማሪ መግለጫ

ለተጨማሪ ጥናት የሚጠቅሙ ሃሳቦች

በርዕሱ ዙሪያ የተጻፉ ሌሎች ስነ-ፅሁፎች

የ40-ቀን የጥናት መምሪያ

ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የመኖር አዲስ ተሞክሮ

ጌታ እራሱ ነው ትዕዛዙን የሰጠው፣

# ያለማቋረጥ
# ሁልጊዜ በተደጋጋሚ
# መንፈስ ቅዱስ ይሙላባችሁ!

# መግቢያ

# ወደ የግል መንፈሳዊ መነቃቃት የሚመራ መንገድ

*በመንፈስ ቅዱስ መሞላት*

## በመንፈስ ቅዱስ ስለተሞላ ሕይወት አስፈላጊነት እንዳስብ ያደረገኝ ዋና ምክንያት ምንድን ነው?

በነሐሴ 14, 2011, በካንደርግሩንድ ቤርነር ኦበርላንድ፣ በስዊዘርላንድ በነበርኩ ጊዜ አንድ ወሳኝ ነገር በጣም ግልጽ ሆነልኝ፡፡ አንዳንድ ወጣቶቻችን ወደ ቤተ-ክርስቲያን መምጣት የሚያቆሙበትን መንፈሳዊ መንስኤ ተረዳሁ፡፡ ጉዳዩ በጣም አሳሰበኝ፡፡ ልጆቼንና የልጅ ልጆቼን አሰብኳቸዉ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለችግሩ መፍትሄ መገኘት እንዳለበት ተገነዘብኩ፡፡

የብዙ መንፈሳዊ ችግሮቻችን መንስኤ ተመሳሳይ እንደሆነ አሁን አረጋገጥኩኝ፤ በተለይም በግል ሕይወታችን፣ በአጥቢያ ቤተ ክረስቲያን ውስጥ፣ በዓለም አቀፏ ቤተ-ክርስቲያናችን ለሚከሰቱት ችግሮቻችን ዋናው ምክንያት የመንፈስ ቅዱስ እጦት ነዉ፡፡

መንስኤው ይህ ከሆነ፣ ለችግሩ አስቸኳይ መፍትሄ መፈለግ ያስፈልገናል፡፡ ይህ የችግሩ መነሻ ሊቀረፍ ከቻለ ወይም ሊቀንስ ከቻለ፣ ከችግሮቻችን አብዛኞቹ ሊወገዱ ወይም ሊፈቱ ይችላሉ ማለት ነው፡፡

# ስለመንፈስ ቅዱስ እጥረት ሌሎች ሰዎች የተናገሩት

**ኤሚል ብራነር፡-** አንድ የኢቫንጀሊካል የስነመለኮት ተሐድሶ መሪ እንዲህ ጽፎአል፡- *"መንፈስ ቅዱስ በስነ-መለኮት ትምህርት ውስጥ በብዙም ሆነ በጥቂቱ እንደ እንጀራ ልጅ ተቆጥሮአል"* (Johannes Mager, *Auf den Spurendes Heiligen Geistes*, (Lüneburg, 1999), Cover)

**ዲ. ማርቲን ሎይድ ጆንስ፡-** *"ሃቁን ለመናገር፣ ትናንትናም ሆነ ዛሬ በመጽሐፍ ቅዱስ ወስጥ እንደ መንፈስ ቅዱስ ችላ የተባለ ርእስ የለም ... ይህ ለኢቫንጀሊካሎች እምነት ድክመት መንስኤ እንደሆነ ጥርጥር የለኝም፡፡* (D. Martin Lloyd-Jones, *Vollmacht, Telos-Taschenbuch* Nr.385, Marburg 1984, p.72)

**ሌሮይ. ኢ.ፍሩም:** *"የመንፈስ ቅዱስ እጦት ከችግሮቻችን ሁሉ የከፋዉ ችግር ነዉ፡፡"* (LeRoy E. Froom, *The Coming of the Comforter* (Hagerstown, 1949), p.94)

**ድዋይት ኔልሰን፣** "ቤተ-ክርስቲያናችን አስደናቂ ስርዓቶችን፣ እቅዶችንና መርሀ-ግብሮችን (ፕሮግራሞችን) አውጥታ ትንቀሳቀሳለች፤ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ እጦት [ኪሳራ]ዉስጥ እንዳለን ብዙዎቻችን አገልጋዮችና መሪዎች የማንገነዘብ ከሆነ ከልማዳዊዉ አስመሳይ ክርስቲያንነት ልንላቀቅ በፍጹም አንችልም፡፡ (Editor Helmut Haubeil, *Missions brief Nr.34 (Bad Aibling, 2011)*, Seite 3)

**ጋሪ ኤፍ. ዊሊያም:-** *" በአብዛኞቹ የአድቬንቲስቶች የግል እና የቤተ-ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ትንሽ ሚና የሚጫወት ይመስላል፡፡ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ለክርስቲያኖች በደስታ ለተሞላ ሕይወት፤ ማራኪና ፍሬያማ ለሆነ ሕይወት መሠረት ነዉ፡፡"* (Garrie F. Williams, *How to be filled by the Holy Spirit and know it* (Lüneburg, 2007), Cover)

**ኤ.ደብልዩ.ቶዜር:-** *" ዛሬ መንፈስ ቅዱስ ከቤተ-ክርስቲያናችን ቢወሰድም እንኳን፤ አሁን ከምንሰጣቸው አገልግሎቶች 95%ቱ እንዳለ ይቀጥል ነበር፤ ልዩነቱንም ማንም አያስተዉልም፡፡ ነገር ግን፣ መንፈስ ቅዱስ ከጥንቷ ቤተ-ክርስቲያን ተወስዶ ቢሆን ኖሮ፤ ታደርግ ከነበረዉ አገልግሎት 95%ቱ ይቆም ነበር፣ ልዩነቱንም ሁሉም ይገነዘቡ ነበር"* (Dr. S. Joseph Kidder, *Anleitung zum geistlichen Leben* (Andrews University), PPP slide2)

እስኪ በቅድሚያ፣ ጌታ የሱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ የሰጠንን ምክር አንዳንዶቹን እንመልከት፡፡

## ምዕራፍ 1

# የየሱስ እጅግ ዉዱ ስጦታ

## የሱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ምን አስተማረ?

*ከየሱስ ክርስቶስ ኃይለኛ መልዕክት ጋር*

*በሚገባ ተዋዉቃችኋል ን?*

### ከአንዳንድ የግል ምስክርነቶች በጥቂቱ

***ወደ "መጀመሪያዉ ፍቅራችን" ተመለስን:-*** አንዲት እህት እንዲህ ብላ ጻፈችልኝ:- "ጓደኛዬ እና እኔ "40 ቀናት የጸሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት" የሚለውን መጽሐፍ ለሦስተኛ ጊዜ "ወደ የግል መንፈሳዊ መነቃቃት የሚመራ መንገድ" ከሚለዉ መጽሐፍ ጋር እያፈራረቅን በማጥናት ላይ እንገኛለን፡፡ ይህንን መጽሐፍ ከማግኘታችን በፊት የእምነታችንና የጸሎት ልምምድ ህይወታችን ከዚህ በፊት እንደነበረዉ አልነበረም፡፡ **"የመጀመሪያ ፍቅራችንን" እንደ ገና ለማግኘት ናፈቅን፤** አገኘንም! በሙሉ ልባችን እግዚአብሔርን አመሰገንን፡፡ አፍቃሪዉ እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንዴት እንደመለሰዉና መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ እና በምንጸልይላቸው ሰዎች ሕይወት ውስጥ እንዴት እንደሚሠራ የገለጸልን አገላለጽ አስደናቂ ነበር፡፡" (ኤም. ኤስ.)

**የሱስ ወደ ሕይወታችን ገባ፡-** አንድ ሌላ ሰው ደግሞ ስለዚህች አሁን ስለሚያነቧት መጽሐፍ እንዲህ ብሎ ጻፈ፡- "… ይህች መጽሐፍ ለሕይወቴ ታላቅና ለረዥም ጊዜ ስጠባበቀው የነበረዉን በረከት ሰጥታኛለች፡፡ እኔና አንዲት በጌታ እህቴ በእምነት ልምምዳችን ዘወትር የሚጎድለን አንድ ነገር እንደነበር ተረዳን፡፡ አሁን ግን የሱስ እንዴት ወደ ሕይወታችን እንደሚገባና እንዴት መለወጥ እንደምንጀምር የምንረዳበትን ልምምድ አገኘን፡፡ የሱስ አሁንም በእኛ ውስጥ እየሠራ ይገኛል፡፡ ደረጃ በደረጃም ወደ እርሱ እያቀረበን ነዉ፡፡" (ኤስ.ኬ.)

**"የሱስ በሰዎች ሕይወት ውስጥ ይህን የሚያህል ተጽዕኖ ማሳደር እንዴት ቻለ?" ብለዉ የየሱስ ደቀ-መዛሙርት እራሳቸዉን ጠይቀው ነበር፡፡** የየሱስ ውጤታማ መሆን ከጸሎት ሕይወቱ ጋር የተገናኘ ነበርን? በርግጥ ለዚህ ነዉ፡- "ጌታ ሆይ ጸሎትን አስተምረን" ብለዉ የጠየቁት፡፡ የሱስም ጥያቄአቸውን መለሰ፡፡

የሱስ በሉቃስ 11፡1-13 ስለ ጸሎት ያስተማራቸዉ ትምህርት ሶስት ክፍሎች አሉት፡፡ (1ኛ) የጌታችን ጸሎት ("አባታችን ሆይ…")፣ (2ኛ) ጓደኛዉ በሌሊት መጥቶ እንጀራ የጠየቀበት ምሳሌ እና (3ኛ) መንፈስ ቅዱስን ያለ ማቋረጥ ለመቀበል የመጸለይ ምሳሌን ያካተተ ነበር፡፡

ሉቃስ 11 ቁጥር 5-8 ላይ እንደተገለፀው፣ ሰውየው እንግዶች በሌሊት ሲመጡበት እንዲበሉ የሚያቀርብላቸዉ ምንም እንጀራ የለውም ነበር፡፡ ከእጦቱ የተነሳ ወዲያዉኑ ወደ ጎረቤቱ ይሄድና "የማቀርብላቸዉ ምንም የለኝምና እንጀራ ስጠኝ" ብሎ ጠየቀዉ፡፡ እንጀራዉን እስኪያገኝ ድረስ ደግሞ ደጋግሞ መጠየቁን ቀጠለ፡፡ ከዚያም እንጀራ አገኘ፤ ያዉም ለእንግዶቹና ለራሱ የሚሆን የሕይወት እንጀራ፡፡ አሁን ለራሱም ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም የሚያካፍለዉን አገኘ፡፡

የሱስ ይህን ምሳሌ፣ "ስለዚህ እኔም እላችኋለሁ ጠይቁ ይሰጣችሁማል" ከሚለዉ መንፈስ ቅዱስን ለማግኘት ከመጠየቅ ጋር አያይዞታል (ሉቃስ 11:9)

## የየሱስ ልዩ ተማጽኖ፡-

## ስለዚህ፣ መንፈስ ቅዱስን እንዲሰጣችሁ ጠይቁ

መንፈስ ቅዱስን እንዲሰጠን መጠየቅ እንዳለብን የሱስ በዚህ ልዩ የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ አዞናል፡፡ ከዚህ ጥቅስ ሌላ፣ ትኩረት እንድንሰጠው የሱስ እኛን በፍቅር ያስገደደበትን

ሌላ ጥቅስ በመጽሐፍ ቅዱስ አላገኘሁም፡፡ እነዚህ ጥቅሶች የሚገኙት የሱስ ስለ ጸሎት ባስተማረበት በሉቃስ 11፡9-13 ውስጥ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ እንዲሰጠን መጠየቅ እንዳለብን አስር ጊዜ ያህል በአጽንኦት ተናግሯል፡-

"ስለዚህ እላችኋለሁ **ጠይቁ** ይሰጣችሁማል፤ **ፈልጉ** ታገኙማላችሁ፤ **አንኳኩ** ይከፈትላችኋል፣ **ለሚጠይቅ** ሁሉ ይሰጠዋል፤ **የሚፈልግ** ያገኛል፤ **ለሚያንኳኳ** ይከፈትለታል፡፡ አባት ከሆናችሁ ከእናንተ ከማንኛችሁም ልጁ እንጀራ **ቢለምነው**፥ እርሱም ድንጋይ ይሰጠዋልን? ዓሣ ደግሞ **ቢለምነው** በዓሣ ፋንታ እባብ ይሰጠዋልን? ወይስ እንቍላል **ቢለምነው** ጊንጥ ይሰጠዋልን? እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፥ በሰማይ ያለው አባት **ለሚለምኑት** እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?"

በእነዚህ ጥቂት ጥቅሶች "ጠይቁ"ሚለዉን ግስ የሱስ ስድስት ጊዜ ተጠቅሞታል፡፡ ከዚያም ሁለት ጊዜ "ጠይቁ" የሚለዉን ግስ "ፈልጉ" በሚለዉ ግስ አጽንኦት ሰጥቶ ቀይሮታል፤ እንዲሁም "አንኳኩ" የሚለዉን የድርጊት ገላጭ ቃል ተጨማሪ ሁለት ጊዜ ተጠቅሞታል፡፡

በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት እኛ ተግባራዊ እርምጃ መዉሰድ እንደሚገባን ይህ በግልጽ አያሳየንምን? የመጨረሻዉ "ጠይቁ" የሚለዉ ቃል በግሪኩ በቀጣይነት ልናደርገዉ የሚገባን ድርጊት እንደሆነ ጥቅም ላይ ዉሎአል፡፡ ይህ ማለት አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜ መጠየቅ እንደሚገባን ይነግረናል፡፡ እዚህ ጋ የሱስ ስለነገሩ አንገብጋቢነት ብቻ ሳይሆን ያለማቋረጥ በቀጣይነት ምን ማድረግ እንደሚጠበቅብን ነግሮናል፡፡ በእርግጥም የሱስ የመንፈስ ቅዱስን አስፈላጊነት መሻት እንዳለብን በዚህ አፅንኦታዊ ግብዣዉ ገልጾልናል፡፡ ይህ እጅግ አስፈላጊ ግብዣ የሚያሳየን ስለመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ያለማቋረጥ በቀጣይነት የማንጠይቅ ከሆነ አንድ እጅግ ወሳኝ የሆነ ነገር እያጣን እንደሆነ ነዉ፡፡ ትኩረታችንን በሙሉ ወደ መንፈስ ቅዱስ መሻት እንድናደርግ እየጠራን ነዉ፡፡ በመሆኑም፣ ያለማቋረጥ የመንፈስ ቅዱስን በረከቶች እንድንቀበላቸዉ ይፈልጋል፡፡

በክራይስት ኦብጀክት ለሰንስ፡ "እግዚአብሔር፣ <አንድ ጊዜ ብቻ ጠይቁ ትቀበላላችሁ> አላለም፡፡ <ጠይቁ>፣ ያለመታከት በቀጣይነት በጸሎት ነዝንዙ እያለ ይለምነናል፡፡ የማያቋርጥ ፀሎት መፀለይ፣ የሚፀልየውን ግለሰብ ወደ ጠለቀ መንፈሳዊ የሕይወት ልምምድ ዉስጥ

እንዲገባ ማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ የጠየቀዉን ነገር እስኪቀበል ድረስ የበለጠ መሻትን ይሰጠዋል"
(E.G. White, *Christ's Object Lessons* (1900), p. 145.3)

ይህንን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ የሱስ በኃጢአተኛ ሰብአዊ አባቶች እንኳን ሊታሰቡ የማይችሉ ሶስት ምሳሌዎችን ሰጠ፡፡ የሰማዩ አባታችንን ለሚጠይቁት ሁሉ መንፈስ ቅዱስን አለመስጠት የማይታሰብ ነገር እንደሆነ የሱስ በዚህ ምሳሌ ሊያሳየን ፈለገ፡፡ መንፈስ ቅዱስን መጠየቅ በሚገባን ሁኔታ ከጠየቅን እንደምንቀበል የሱስ እርግጠኞች እንድንሆን ይፈልጋል፡፡ በዚህና በሌሎች የተስፋ ቃሎቹ በእምነት የጠየቅነዉን ነገር እንደተቀበልን እናዉቃለን፡፡ (1ኛ ዮሐንስ 5፡14-15፡፡ ተጨማሪ መረጃ በምዕራፍ 5 ላይ ያገኛሉ)

የሱስ በዚህ ልዩ ግብዣዉ እያመለከተን ያለዉ ስለመንፈስ ቅዱስ ሁልጊዜ ባለመጠየቃችን አንድ አስፈላጊ ነገር እያጣን እንዳለን ነዉ፡፡ በመንፈስ ቅዱስ የሚገኘውን ሙሉ በረከት ያለማቋረጥ እንድንለማመድ ይፈልጋል፡፡

የሱስ በዚህ ቦታ ላይ ስለጸሎት ያስተመማረው ትምህርት የተለየ ነው፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፣ ሌሎች ስጦታዎችን ሁሉ ያካተተ የእግዚአብሔር ታላቅ ስጦታ ነው፡፡ ይህ ስጦታ፣ የሱስ ለደቀመዛሙርቱ የሰጣቸው ክቡር ስጦታ እና ግልጽ የፍቅሩ ማረጋገጫ ነበር፡፡ ይህን የመሰለ ስጦታ አንድ ሰው በግዳጅ መቀበል እንደሌለበት እንስማማለነን፡፡ ይህ ስጦታ የሚሰጣቸዉ ፍላጎታቸዉን ለሚገልጹና ስጦታዉን ለሚያደንቁ ብቻ ነዉ፡፡ ይህ ስጦታ፣ ሕይወታቸዉን ለክርስቶስ ላስረከቡት ፤ እንዲሁም ያለማቋረጥ ራሳቸዉን አሳልፈዉ ለሚሰጡ ነዉ የሚሰጠው፡፡ (ዮሐንስ 15:4-5)

ሕይወታችንን ለጌታ ማስረከባችን የሚገለጸው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መንገዶች ነው፡-

- እግዚአብሔርን በመጠማት ("ማንም የተጠማ ቢኖር" ዮሐንስ 7:37)
- በእግዚአብሔር በመታመን ("መጽሐፍ እንደሚል በእኔ የሚያምን" ዮሐንስ 7:38)
- በእግዚአብሔር ከመታመን የተነሳ ሁሉንም በማስረከብ ("ሕይወታችሁን በሙሉ ለእርሱ እንድታቀርቡ" ሮሜ 12:1)
- በሁሉም ነገር እግዚአብሔርን በመከተል ("እግዚአብሔርን ለሚታዘዙት" የሐዋርያት ሥራ 5:32)
- የራስን መንገድ በመተዉ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉን በማድረግ ("ንስሓ ግቡ

ተጠመቁም" የሐዋርያት ሥራ 2:38)

- ማንኛዉንም ክፉ ነገር ለማድረግ ባለማቀድ ("በልቤ በደልን አይቼ ብሆን ጌታ አይሰማኝም ነበር" መዝሙረ ዳዊት 66:18)
- ባዶ መሆናችንንና እርዳታ የሚያስፈልገን መሆኑን በመገንዘብ ("ምንም የለኝም" ሉቃስ 11:6)
- ያለማቋረጥ የመንፈስ ቅዱስን ሙላት በመጠየቅ (ሉቃስ 11:9-13)

በእነዚህ ቅድመ-መጠይቆች ይህ እግዚአብሔር ያዘጋጀልን ስጦታ ምን ያህል የከበረ እንደሆነ በግልጽ ተገነዘባችሁን? ስለ እነዚህ ሁሉ ቅድመ-መጠይቆች ስታስቡ ምናልባት በራሳችሁ ሕይወት ዉስጥ ጉድለትን ታገኙ ይሆናል፡፡ እኔ ዮሐንስ 6፡37ን መሠረት አድርጌ በየቀኑ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት በናፍቆት መጸለይን ልማዴ አድርጌዋለሁ፡፡ "ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ" (የተስፋ ቃሉን መሰረት በማድረግ መጸለይ እጅግ አስፈላጊ ነዉ፡፡ ስለዚህ ርዕስ የበለጠ ለማወቅ ከፈለጋችሁ ምዕራፍ 5ን አንብቡ)

**እንደዚህ ብለን መጸለይ እንችላለን፦** "ጌታ የሱስ ሆይ፣ መንፈስ ቅዱስን ለመሞላት የጠየቅከኝን ቅድመ-መጠይቆች ሁሉ ሙሉ በሙሉ እቀበላለሁ፡፡ እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች አሁን ዛሬ በእኔ ሕይወት ውስጥ እንድትፈጽም በትህትና በተሞላ ልብ እጠይቃለሁ፡፡" አስደናቂዉ አምላካችን እነዚህን ቅድመ-መጠይቆች እንኳን ሳይቀር ሊያሟላልን ከጎናችን አለ፡፡

## መንፈስ ቅዱስ ለተሟላ ሕይወት ምንጭ ነዉ

የሱስ፣ እርሱ ወደ ምድር ስለመጣበት ምክንያት ሲናገር ምን አለ?

*"እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ"* (ዮሐንስ 10፡10)

የሱስ ይህን የተሟላና የተትረፈረፈ አዲስ ሕይወት ዛሬ እንድንለማመደው ይፈልጋል፡፡ እንዲሁም ከዳግም ምጻቱ በኋላ በእግዚአብሔር መንግስት ሙሉ በሙሉ ለየት ባለ ሁኔታ የዘላለም ሕይወትን ያለማቋረጥ እንድናጣጥመው ይፈልጋል፡፡

በተጨማሪም፣ የዚህ የተሟላ ሕይወት ዋናው ምንጭ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ይገልጽልናል፦ " ... ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ። በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ፥ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ። ይህን ግን በእርሱ

የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለመንፈስ ተናገረ፤ የሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና። ” (ዮሐንስ 7:37-39)

“የሕይወት ዉኃ ወንዝ!” - ለተሟላና ለተትረፈረፈ ሕይወት ይህ ጥሩ ማነጻጸሪያ አይደለምን?

## የሱስ በዚህ ምድር በኖረበት ሕይወቱ፣ ምን አይነት ምሳሌ ሰጥቶናል?

የሱስ በእናቱ በማርያም ውስጥ በፀለለው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እንደተጸነሰ እናዉቃለን፡፡ (ማቴዎስ 1፡18)፡፡ በውኃ ከተጠመቀም በኋላ የሱስ ሲፀልይ፡- *“መንፈስ ቅዱስም በአካል መልክ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ”* (ሉቃስ 3:22)፡፡ ይህ ቢሆንም፣ ለየሱስ በየቀኑ መንፈስ ቅዱስን መቀበል አስፈላጊና ጠቃሚ የነበረው ለምንድን ነው? ከኤለን ጂ. ኋይት ጽሁፍ የሚከተለውን አንብቤአለሁ፡-

*“በየማለዳው ከሰማያዊ አባቱ ጋር በመገናኘት የየዕለቱን ትኩስ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ተቀበለ፡፡”* (E.G. White, Signs of the Times, November 21, 1895, par. 3)

<አክትስ ኦፍ ዘ አፖስተልስ> በሚባለው መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ የሚል አርፍተ ነገር አለ፡- “የሚያስፈልገውን ፀጋ ለማግኘት፣ ክርስቶስ በምድር በኖረበት ዘመን ሁሉ በየቀኑ አባቱን ይለምን ነበር፡፡ ራሳቸውን ለቀደሱ የጌታ አገልጋዮች፣ ክርስቶስ እንኳን ሳየቀር በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ይጸልይ እንደነበር ማወቃቸው እጅግ ትልቅ መጽናኛ ነው፡፡” (E.G. White, *The Acts of the Apostles,* (1911) p. 56.1)

ይህን በተመለከተ የሱስ በእርግጥ ጥሩ ምሳሌያችን ነዉ፡፡ በመሆኑም፣ “የሱስ በየቀኑ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ካስፈለገዉ፣ ለእኔና ለእናንተ ምን ያህል ከዚያ በለይ ያስፈልገናል?” ብለን ራሳችንን ልንጠይቅ ይገባናል፡፡

ሐዋርያዉ ጳዉሎስ በእዉነት የየሱስን ተማፅኖ አስተዉሎአል፡፡ ለኤፌሶን ቤተ-ክርስቲያን በጻፈዉ ደብዳቤዉ በምዕራፍ 1፡13 ላይ አማኞች ጌታን ሲቀበሉ በመንፈስ ቅዱስ እንደታተሙ ጳዉሎስ አረጋግጦላቸዋል፡፡ በምዕራፍ 3፡16-17 በመንፈስ ጠንካራ እንዲሆኑ አደፋፈራቸው፡፡ በምዕራፍ 4፡30 ደግሞ “መንፈስ ቅዱስን አታሳዝነኑ” ይላቸዋል፡፡ በምዕራፍ 5፡18 ጳዉሎስ እንደ ባለስልጣን ሐዋርያ፣ የኤፌሶን አማኞችንና እኛን “... መንፈስ ይሙላባችሁ!” ወይም “ያለማቋረጥ በተደጋጋሚ በመንፈስ ቅዱስ እንድትሞሉ!” እያለ ይጋብዘናል፡፡ እንደገና

የተወለድን ጊዜ (በተጠመቅን ጊዜ) መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበልን የምናዉቅ ቢሆንም፣ በአጠቃላይ በየዕለቱ በመንፈስ መታደስ ያስፈልገናል፡፡ ለክርስቲያናዊ መንፈሳዊ ህይወት እና እድገት በየቀኑ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ (Hrsg. Werner E. Lange, Unser größtes Bedürfnis, (Lüneburg, 2011), Seite 42)

የሰንበት ትምህርታችን መምሪያ ስለ ኤፌሶን 5፡18 የሚከተለዉን ይላል፡-

"በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ማለት ምን ማለት ነዉ? የሱስ እራሱ ይህን በተመሳሳይ ቃላት ገልጾታል፡፡ አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ የሚጠመቀው (የሐዋ. 1፡5) መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ነው (የሐዋ. 1፡8)፡፡ <መጠመቅ> ማለት በሆነ ነገር ዉስጥ ሙሉ በሙሉ መስጠም ማለትነዉ (ለምሳሌ በዉኃ ዉስጥ)፡፡ ይህ ደግሞ ሙሉ ማንነትን የሚያጠቃልል ተግባር ነዉ፡፡ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ማለት ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር (ተጽዕኖ) ስር መሆን ማለት ነዉ፡፡ በእርሱ ሙሉ በሙሉ መሞላት ማለት ነዉ፡፡ ይህ የአንድ ጊዜ ብቻ ልምምድ አይደለም፤ ነገር ግን በኤፌሶን 5፡18 ጳዉሎስ እንደገለጸዉ፣ በግሪኩ ግስ <መሞላት> ባለማቋረጥ የሚደጋገም ተግባር ነዉ፡፡" (Sabbath School Study Guide July 17, 2014)

## የየሱስ የመሰናበቻ ቃላትና መንፈስ ቅዱስ

ደስታ እና ተስፋ እንዲኖራቸው ስለፈለገ፣ የሱስ በመሰናበቻ ንግግሩ መንፈስ ቅዱስ እርሱን ተከቶ እንደሚመጣ ገለጸላቸዉ፡፡ በዮሐንስ 16፡7 ላይ እንዲህ ተጽፎአል፡-

*"እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ፤ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል። እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና፤ እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልከላችኋለሁ።"* በማለት የሱስ ደቀመዛሙርቱን አስገረማቸው፡፡

# አዲሱ ጠቃሚ መፍትሄ

የሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ያልተጠበቀ ነገር ነው የነገራቸዉ፡- "እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል" በመንፈሱ አማካይነት በዉስጣችን መሆኑ በአካል ከኛ ጋር ከመሆን ይበልጣል፤ ይህ ነዉ አዲሱ መፍትሄ ማለት፡፡ ይህ ማለት፣ የሱስ አሁን ያለበት ቦታ የትም ቢሆን የት፣ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በእያንዳንዱ ክርስቲያን ልብ ውስጥ መሆን ይችላል፡፡

## መምህርትና አንድ ተማሪዋ እንዴት የእግዚአብሔርን ኃይል እንደተለማመዱ

"ወደ የግል መንፈሳዊ መነቃቃት የሚመራ መንገድ" የሚለው የሄልሙት ሃውባይል መጽሐፍ ከአንድ ዓመት በፊት ሲደርሰኝ በጥቂት ጊዜ ውስጥ አንብቤ ጨረስኩት፡፡ ይህን መጽሐፍ በማንበብ ላይ እያለሁ ከመቼውም በበለጠ ከእግዚአብሔር ጋር ብዙ ነገር ተለማመድኩኝ፡፡ መጽሐፉ በጣም ልቤን ደስ አሰኘው፣ አደፋፈረኝ፣ አበረታታኝም፡፡

በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ገጾች ላይ (ተጨማሪ ማብራሪያ በሚለው ገጽ ላይ) የሚከተለዉን አስተያየት አገኘሁ፡-

"ትምህርታዊ ጥናት እንዳረጋገጠው፣ አንድን ርዕስ በደንብ እስክናስታዉል ድረስ ከስድስት እስከ አስር ጊዜ ደግሞ ደጋግሞ ማንበብ ወይም ማዳመጥ አስፈላጊ ነዉ ይላል፡፡"

"ቢያንስ አንድ ጊዜ አንብባችሁ ሞክሩት፣ ዉጤቱ ያሳምናችኋል" የሚለው የማደፋፈሪያ ቃል አእምሮዬን ማረከው፡፡

ይህን ለመለማመድ ፈለግኩና መጽሐፉን ለሶስተኛ ጊዜ በማነብበት ጊዜ፣ ልቤ ተነካና በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ስናፍቀው የነበረው ለአዳኜ ያለኝ ትልቅ ፍቅር በውስጤ ተሰማኝ፡፡ በሁለት ወራት ዉስጥ ስድስት ጊዜ ደጋግሜ አነበብኩት፤ ውጤቱም እጅግ ጠቃሚ ነበር፡፡

ልክ የሱስ ወደ እኔ እንደ ቀረበ ተሰማኝ፡፡ ንጹህ፣ መልካምና አፍቃሪ ዓይኖቹ ምን እንደሚመስሉ ያስተዋልኩም መሰለኝ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለአዳኜ ያለኝን ደስታ ማጣት አልፈለግሁም፡፡

ጠዋት ከእንቅልፌ ስነሳ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ለማድረግ የማለዳ አምልኮ ጊዜዬ ይናፍቀኝ ጀመር፡፡ በቀን ዉሎዬ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ሃሳቤን፣ ንግግሬን፣ ምሳሌነቴን፣ በማስተምርበትና በማስረዳበት ጊዜ እንዲመራኝ በጽሞና እጸልያለሁ፡፡

ልጆች ትኩረት በሚፈልጉበት ጊዜ አስፈላጊውን እርዳታ እንዳደርግ እግዚአብሔር ብርታትና ጥበበ ሰጠኝ፡፡

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሥራ ቀናቶቼ በሙሉ በፈጣሪዬ መገኘት የተሞሉ ሆኑ፡፡ በየዕለት ኑሮዬ ሲረዳኝ አየዋለሁ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በጠዋት እና በየመሃሉ ለመንፈስ ቅዱስ መሞላት እጸልያለሁ፡፡ ወደ ሰማይ እንደቀረብኩና እዚያም ያለውን ውበት (ደስታ) የማጣጣም አይነት ስሜት ነው የሚሰማኝ፡፡

ይህችን መጽሐፍ በማነብበት ጊዜ፣ በትምህርት ቤት ላሉት ተማሪዎቼ ይህንን ልምምድ እንዳካፍላቸዉ ሐሳብ መጣልኝ፡፡ ከ10-15 እድሜ ክልል ዉስጥ ያሉትን ልጆች በአዉስትሪያ ባለዉ *ሔልያስ ሊድቬንቲስት ትምህርት ቤት* አስተምራለሁ፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር አጋጣሚውን እንዲሰጠኝ ጸለይኩኝ፡፡ ከዚያ በኋላ መንፈስ ቅዱስ በልጆች ልብ ዉስጥ እንዴት እንደሚሰራ አስደናቂ ልምምድ አገኘሁ፡፡

## የ13 ዓመቱ ታዳጊ ወጣትና መንፈስ ቅዱስ

ከዚህ ቀጥሎ የምነግራችሁ ታሪክ የተከሰተው በመንፈስ ቅዱስ ስለመሞላት የሚያስተምረውን መጽሐፍ ከማንበቤ ከአንድ ዓመት ቀደም ብሎ ነዉ፡፡ አንድ አዲስ ተማሪ ወደ ትምህርት ቤታችን በመጣ ከጥቂት ቀናት በኋላ፣ ደስ በሚያሰኝ ሰላማዊ ከባቢ አየር የተሞላ የነበረዉ አካባቢያችን በአስቀያሚ የጥል ቦታ ተተካ፡፡ ልጁ የ13 ዓመት እድሜ ያለው ቢሆንም በአንጻራዊነት ከሁሉም ይልቅ ረዥምና ጠንካራ ነበር፡፡ በትምህርት ዓመቱ ውስጥ ተማሪዎቼ የተማሩት መልካም ትምህርትና የተገኘዉ አስደናቂ ፍሬ በቅጽበት የጠፉ መሰለ፡፡

እሰቲ ይህ የ13 ዓመት ልጅ እርሱ ራሱ የተናገረውን እናንብብ፡- <አሁን ወዳለሁበት ትምህርት ቤት ስመጣ ምን እንደሚጠብቀኝ የማዉቀዉ ነገር አልነበረም፡፡ ልክ በገባሁ በሁለተኛዉ ቀን በጣም በብስጭት ጮህኩና ከክፍል ጓደኞቼ ከአንዱ ጋር መደባደብ ጀመርኩኝ፡፡ ሲታይ ከእኔ ደካማ መሆኑን ባውቅም ደበደብኩት፤ ከዚያም ሰደብኩትና ዳግመኛ ላየዉ እንደማልፈልገዉ ነገርኩት፡፡

ትንሽ ጊዜ ከቆየ በኋላ ስህተቴን ተረዳሁና ይቅርታ ጠየኩት፡፡ ከዚያ በኋላ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ፊት ቀረብኩ፡፡ በሚቀጥሉት ወራቶች በውስጤ ለውጥ መከሰት ጀመረ፡፡ የፓስተር ልጅ ብሆንም እንኳን በሚያስደንቅ ሁኔታ ገና አሁን ነበር በሕይወቴ ለውጥ ማየት የጀመርኩት፡፡ ከዚያም ከየሱስ ጋር ብዙ ጊዜ ማሳለፍ ጀመርኩኝ፡፡>

ይህ ወጣት ልዩ እንክብካቤ ያስፈልገዋል ብዬ አሰብኩኝ፡፡ ድክመቱን ተገንዝቦ፣ ተጸጽቶ እንደ ገና ሞከረ፣ ነገር ግን በራሱ ብርታት ዘለቄ የሆነ ስኬት አላገኘም፡፡ በመጀመሪያ አካባቢ ሳይደባደብ የቀረበት ቀን አልነበረም፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን ቀስ በቀስ እየተሻሻለ መጣ፡፡

ከስድስት ወራት በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር የበለጠ እንዲቀራረብ ያደረገው ፀሎት እንደሆነ መሰከረ፡፡ ብርታት እንዲያገኝ ጠዋት ተነስቶ መጸለይ እንደጀመረ መሰከረ፡፡ የሚገነፍለዉ፣ ቁጣዉና መደባደቡ እየቀነሰለት መጣ፡፡

ወደ እኛ ትምህርት ቤት ከመጣ አሁን አስራ አንድ ወራት አልፈዋል፤ እኛም ትልቅ መሻሻል አየንበት፡፡ ቢሆንም ግን ቁጠኛነቱ፣ የስድብ ናዳው፣ ጡንቻዉ በቋሚነት በቁጥጥር ስር አልነበሩም፡፡ እንደተለመደው በራሱ ብርታት እራሱን ማሸነፍ እንደሚችል በማሰብ ሞከረ፤ አንዳንድ ጊዜ ይሳካለት ነበር ሌላ ጊዜ ደግሞ በጭራሽ፡፡ ጸሎታችን የተወሰነ ስኬት ቢያመጣልንም የሚያድሰዉ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ግን ይጎድለን ነበር፡፡

አንድ ሰዉ ስህተቶቹን ቢያምንም፣ ቁጣውን ለመቆጣጠር ቢሞክርም፣ ተመልሶ ግን ሌላ ጊዜ እንደገና እንደዚያዉ ቢያደርግ ምን ፋይዳ ይኖረዋል? መፍትሔ እንዳጣሁ ባስተዋልኩ ጊዜ ነበር ከላይ የጠቀስኩትን መጽሐፍ አግኝቼ ማንበብ የጀመርኩት፡፡ በትክክለኛ ጊዜ ነው መጽሐፉን ያገኘሁት፡፡ ያን ጊዜ ነበር ምን እንደጎደለን የተረዳሁት፡፡ እርሱም የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነበር፡፡ ሌላዉ ቀርቶ እርሱ ራሱ መንፈስ ቅዱስ እንዲረዳን እንኳን አልጠየቅነዉም ነበር!

"ወደ የግል መንፈሳዊ መነቃቃት የሚመራ መንገድ" በሚለው መጽሐፍ መልእክት ልቤ ስለተነካ፤ ልጁን ስለ መንፈስ ቅዱስ ጸልዮ ያውቅ እንደሆነ ለመጠየቅ ድፍረት አገኘሁ፡፡ በጭራሽ አድርጎ አያዉቅም፡፡ መጽሐፉን ለማንበብ ፍላጎት እንዲኖረው ለማነሳሳት ሞከርኩኝ፤ እራሱ ለማንበብ ፈልጎ እስካልጠየቀኝ ድረስ መጽሐፉን አልሰጠሁትም፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ መጽሐፉን እንድሰጠው ጠየቀኝ፡፡

እንደገና ከእርሱ አንደበት የወጡትን ቃላት እናንብብ፡- <በህዳር 2012 ዓ.ም. አስተማሪዬ "ወደ የግል መንፈሳዊ መነቃቃት የሚመራ መንገድ" የሚለዉን መጽሐፍ ሰጠችኝ፡፡ በጉጉት ማንበብ ጀመርኩኝ፡፡ በዚያን ጊዜ ስለ መንፈስ ቅዱስ አሰራር በእርግጥ መረዳት አልነበረኝም፡፡>

በመጀመሪያዉ ቀን ሁለቱን ምዕራፎች አነበባቸው፡፡ መጽሐፏን አንብቦ ከጨረሰ ከጥቂት ቀናት በኋላ፡- <ስንት ጊዜ ደግመሽ አነበብሽው?> ብሎ ጠየቀኝ፡፡ በቀጣዮቹም ቀናት መጽሐፉን እንደገና ማንበብ ጀመረ፡፡ መጽሐፉ እንደሚመከረው ከ6-10 ጊዜ እንደሚያነብበውም ነገረኝ፡፡

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በእጅጉ ተለወጠ፡፡ ከታህሳስ 2012 ወዲህ መደባደብ የለም፣ ስድብ የለም፣ ለውጡን ለማመን ተቸገርኩኝ፡፡ በየዕለቱ ይደበድባቸዉ የነበሩት ልጆች አሁን ወዳጆቹ ሆነዉ በስምምነት አብረዉ መሆን ጀመሩ፡፡

ሙሉ በሙሉ ተለዉጦ ነበር፤ ትህትና፣ ታዛዥነትና ሰላማዊነት ተፈጥሮዉን ወረሰዉ፡፡

እግዚአብሔር በሥራ ላይ እንዳለ የክፍል ጓደኞቹ አረጋገጡ፡፡ እርሱም እግዚአብሔር በእርሱ ውስጥ እንዲሰራ ፈቀደለት፡፡ ፍሬዉም በየዕለቱ ይታይ ነበር፡፡ ለእግዚአብሔር ክብር መናገር የምፈልገዉ፣ ይህ ተማሪ በሰኔ 2013 ዓ.ም. ለመጠመቅ ወሰነ፡፡ እንግዲህ ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ካልሆነ ምን ሊሆን ይችላል?!

<ልጅን መቆጣጠርና ማስተካከል እችላለሁ> እያልኩ ሁልጊዜ አስብ ነበር፡፡ በትእግስት፣ ትኩረት በመስጠት፣ ብዙ በመነጋገር ይህን ማድረግ ይቻላል፤ ግን ይህ ለረዥም ጊዜ የሚቆይ ዉጤት አያመጣም፡፡ እግዚአብሔር ጣልቃ ገብቶ፣ መንፈስ ቅዱስ የማይቻለውን የሚቻል እንደሚያደርግ አስተማረኝ፡፡

ከእለታት አንድ ቀን ይህን ልጅ በሰማይ ሳገኘዉ እግዚአብሔር በተአምር እንዳመጣዉ አዉቃለሁ፡፡ የራሴ ጥበብ ሲያልቅና በመጨረሻ ልጁን ላስተካክለው እንደማልችል ሳስተዉል፤ እግዚአብሔር በእርሱ ላይ አስደናቂ ሥራዉን መሥራት ጀመረ፡፡ ይህ ልምምድ፣ ለእግዚአብሔር ተስፋ-የለሽ (መፍትሔ የሌለው) ችግር እንደሌለዉ እንዳዉቅ አደረገኝ፡፡

*ጸሎት፡- በሰማያት ያለህ አባት፤ መንፈስ ቅዱስን እንድንጠይቅ የሱስ ስላቀረበልን አንገብጋቢ ግብዣ እናመሰግናለን፡፡ ከመንፈስ ቅዱስ እጦት የተነሳ ስለመጣብኝ ኪሳራ አዝናለሁ፡፡ የሱስ ለእኔ ከሁሉም የበላይ እንዲሆን መለኮታዊ እርዳታን እፈልጋለሁ፡፡ በእያንዳንዱ የሕይወት ክፍሌ ውስጥ የእርሱ እርዳታ ያስፈልገኛል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ባህርዬን ስለሚለዉጥልኝና ለሰማይ መንግስት ገጣሚ ስለሚያደርገኝ አመሰግናለሁ፡፡ ማንነቴንና ያለኝን ሁሉ ሙሉ በሙሉ ለአንተ አስረክባለሁ፡፡ ስለተቀበልከኝ እና ስለምትሰጠኝ በረከት አመሰግናለሁ፡፡ ስለ መንፈስ ቅዱስ በማወቅ እውቀት እንዳድግ እርዳኝ፡፡ አሜን!*

## ምዕራፍ 2

# የችግሮቻችን ዋና መንስኤ ምንድን ነው?

## ችግራችን መንፈሳዊ ይሆንን?
## የመንፈስ ቅዱስ እጦትስ ይሆን?

### የእጦቱ መንስኤ

የመጽሐፍ ቅዱስ መልስ “ትመኛላችሁ ለእናንተም አይሆንም፤ ትገድላላችሁ በብርቱም ትፈልጋላችሁ፥ ልታገኙም አትችሉም፤ ትጣላላችሁ፣ ትዋጉማላችሁ ነገር ግን አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም፤ ትለምናላችሁ፥ በምኞቶቻችሁም ትከፍሉ ዘንድ በክፉ (እንደሥጋችሁ ፈቃድ፣ ሮሜ 8:5-7) ትለምናላችሁና አትቀበሉም።” (ያዕቆብ 4:2-3)

ጌታችን የሱስ በፍቅርና ያለማቋረጥ ለመንፈስ ቅዱስ እንድንጸልይ ጋብዞናል (ሉቃስ 11:9-13)፡፡ ይህን ያለማቋረጥ ማድረግ እንዳለብን እናስተውላለን፡፡ ይህን ሐሳብ በቀጣዩ ምዕራፍ የበለጠ ቀረብ ብለን እንመለከታለን፡፡

“ብዙዎች ስለ ክርስቶስና ስለ መንፈስ ቅዱስ ያወራሉ፤ ነገር ግን ምንም በረከት አያገኙም፡፡ እንዲመራቸውና መንገዱን እንዲያሳያቸው ለመለኮት ተፅእኖ ልባቸውን አይከፍቱም፡፡” (Ellen G. White, The Desire of Ages, (1898), p. 672)

እንደቤተክርስቲያን ለብዙ ጊዜ ያህል ለመነቃቃት ፀልየናል፡፡ ይህ ጥሩ እና እጅግ ዋጋ ያለዉ ነገር ነዉ፡፡ ይህንን በተመለከተ ኤ·ጂ· ኋይት እንዲህ ትላለች "ቤተክርስቲያን ዛሬ የሚያስፈልጋት ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ነዉ፡፡" (E.G. White, *Manuscript Releases* Vol. 7 p. 267) "ይህ ኃይልን የምንቀበልበት መንገድ ከሆነ ለምን ለመንፈስ ቅዱስ ስጦታ አንራብም አንጠማም? ለምንስ ስለ እርሱ አንነጋገርም? ለምን ስለ እርሱ አንጸልይም፤ አንሰብክም?" (E.G. White, *Testimonies for the Church* Vol. 8, p. 22)

ለመነቃቃት መጸለይ መልካም ነዉ፤ መፀለይ ብቻውን ግን በቂ አይደለም፡፡ ማርክ ፊንሊ እንደተናገረው፡- "ለመነቃቃት መጽሐፍ ቅዱስ የሚለንን መተግበር ያስፈልጋል፡፡" (Mark A. Finley, *Revive us again,* p. 25) በግልህ መነቃቃትን ወደምትለማመድበት መንገድ እንድትጓዝ ልጋብዝህ? ይህ ይበልጥ ወደተሟላና በኃይል ወደተሞላ ሕይወት ይመራሃል፡፡

እስቲ በመጀመሪያ ዋናውን ችግር እንለየው፡፡ ይህን በሚገባ ማድረግ አለብን፤ ይህ ካልሆነ የለውጥን አስፈላጊነቱንም ጠቃሚነቱንም ያለማስተዋል አደጋ ላይ እንወድቃለን፡፡ ከዚያም በመቀጠል አስደናቂ በረከት የሚያመጣልንን አምላካዊ መፍትሄ እንቃኛለን፡፡ በመጨረሻም ይህን ልምምድ እንዴት ተግባራዊ እንደምናደርግ እንመለከታለን፡፡

ይህ ማለት ግን እስከዛሬ ያለመንፈስ ቅዱስ የሠራናቸውና አሁንም እየሠራን ያለው በከንቱ ነው ማለት አይደለም፡፡ እጅግ በጣም ግሩም እቅዶች ነበሩን አሁንም አሉን፡፡ እግዚአብሔር በእርግጥ እስከዛሬ የሰራናቸውን ሰብአዊ ጥረቶቻችንን በእጅጉ ባርኮአቸዋል፡፡ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ብንመራና የበለጠ በእርሱ ተመርተን ብንኖር ኖሮ ምን ያህል የበለጠ ውጤት እናይና የተሻለ ሁኔታ ውስጥ እንሆን ነበር? ይህን እግዚአብሔር ብቻ ነው የሚያውቀው፡፡

ሄንሪ ቲ. ብላካቢ እንዲህ በማለት እንደገለጹት ይሆን ነበር፡- "ያለ እርሱ ለስድሳ ዓመታት ከሰራነው የወንጌል ስራ ይልቅ፣ እራሳቸውን ለእርሱ ቀድሰው በሰጡት ሰዎች እግዚአብሔር በስድስት ወራት ውስጥ ውጤታማ ስራ በሰራ ነበር፡፡" (Henry T. Blackaby, *Den Willen Gottes erkennen und tun (Experiencing God: Knowing and Doing the Will of God),* (Kassel, 2002), p. 31)

ጥያቄው በእግዚአብሔር አመራር ስር ሆኖ አሁኑኑ ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ የመሄድና፣ በዚያም ከፍተኛ ውጤታማነትን የማግኘት ጉዳይ ነው፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ስንሞላ የሚሆነው ይህ ነው፡፡

ለምሳሌ፡- አንድ ሰው ስብከት ሰብኮ ሲጨርስ ማንም ሰው ወይም ጥቂቶች፣ ብዙዎች ወይም ሁሉም መልዕክቱን ሊቀበሉት ይችላሉ፡፡ ብዙዎች ወይም ሁሉም መልዕክቱን ተቀብለው በተግባር ካዋሉት፣ ይህ ከፍተኛ ውጤታማነት ነው፡፡ ይህ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ነው፡፡

## በሶስት ጎራ የሚመደቡ ሰዎችና ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት

ከእግዚአብሔር ጋር ካላቸዉ የግል ግንኙነት አንፃር የእግዚአብሔር ቃል ሰዎችን በሶስት ጎራ ይመድባቸዋል፡፡ በእያንዳንዱ ጎራ ስር ያሉት ሰዎች ከወላጆቻቸው ባገኙት ትምህርት፣ በባህርይ፣ በግል ልምምድ፣ በእድሜ፣ በባህል፣ በትምህርት፣ ወዘተ የሚለያዩ ይገኙበታል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ቢለያዩም እንኳ ለእግዚአብሔር ባላቸው አመለካከት ግን በሶስት ጎራዎች ይከፈላሉ፡-

- ከእግዚአብሔር ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው፡- መጽሐፍ ቅዱስ <ተፈጥሮአዊ ሰው> ብሎ ይጠራቸዋል
- ከእግዚአብሔር ጋር ሙሉ ወይም እውነተኛ ግንኙነት ያላቸው፡- መጽሐፍ ቅዱስ <መንፈሳዊ ሰው> ብሎ ይጠራቸዋል
- ከእግዚአብሔር ጋር የተከፋፈለ ወይም አስመሳይ ግንኙነት ያላቸው፡- መጽሐፍ ቅዱስ <ሥጋዊ ሰው> ብሎ ይጠራቸዋል፡፡

"ተፈጥሮአዊ ሰው" "መንፈሳዊ ሰው" እና "ሥጋዊ ሰው" በመባል በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተጠቀሱት መጠሪያዎች፣ አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን የግል ግንኙነት በተወሰነ መልኩ የሚገልፁ መለያ ስሞች ናቸው፡፡

እነዚህ ሶስት ዓይነት ጎራዎች 1 ቆሮንጦስ 2:14-16 እና 1ቆሮ. 3:1-4 ላይ ተገልጸዋል፡፡ *<ተፈጥሮአዊው ሰው>* ሙሉ በሙሉ ዓለማዊ ነው፡፡ በሌሎቹ ሁለቱ ጎራዎች ውስጥ የሚኖሩት ግን በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ክርስቲያኖች ናቸው፡፡ የእነዚህን ሁለት ጎራዎች ማንነት በጨረፍታ ስንገመግም፣ ዋናው ችግር ምን እንደሆነ እናስተውላለን፡፡ ይህንን ግምገማ በምናካሂድበት ጊዜ ግን ራሳችንን መጠየቅ ያለብን ጥያቄ፡- <እኔ በየትኛው ጎራ

ውስጥ ነኝ?> የሚለውን ነው፡፡ ስለዚህ ይህንን ግምገማ ማድረጋችን ራሳችንን እንድንመረምር ይረዳናል ማለት ነው፡፡ የራሳችንን ሕይወት እንጂ የሌሎችን እንድንመለከት አይደለም፡፡

### *አንድ ሰው በአንዱ ወይም በሌላው ጎራ ውስጥ መሆኑን የምንለካበት መስፈርት ምንድን ነዉ?*

መስፈርቱ እያንዳንዱ ሰው በግል ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ባለው ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ሲሆን፣ ይህንን መስፈርት በመመልከት በየትኛው ጎራ ውስጥ እንደሚመደብ መለየት እንችላለን፡፡

### ተፈጥሯዊዉ ሰዉ

"ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለሆነ ሊያውቀው አይችልም።" (1ቆሮንጦስ 2:14)

ፍጥረታዊው ሰው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡ ዓለማዊ ኑሮ ነው የሚኖረው፤ ስለ እግዚአብሔር በጭራሽ አይገደውም ወይም እንዲሁ ለይስሙላ ብቻ ነው የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራው፡፡

### መንፈሳዊውና ሥጋዊው ሰው በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ናቸው

እነዚህ ሁለቱ ጎራዎች በ1ኛ ቆሮንቶስ 2 እና 3 እንዲሁም በሮሜ 8:1-17 እና ገላ 4 እና 6 ተገልጸዋል፡፡ የእነዚህ ጎራዎች መለያ መስፈርቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያላቸው የግል ግንኙነት እንደሆነ ልናስተውል ይገባናል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ከሰማይ ጋር የሚያገናኘን ብቸኛው መንገድ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ እግዚአብሔር ስለተናገረ ነው፡፡ (የዘመናት ምኞት ገጽ. 322 ፣ ማቴዎስ 12:32 አንብቡ) "ልባችን ለመንፈስ ቅዱስ ተጽዕኖ ክፍት መሆን አለበት፤ ካልሆነ የእግዚአብሔርን በረከቶች ልንቀበል አንችልም፡፡" (E.G. White, *Leuchtende Spuren (Steps to Christ)* (Hamburg, 1959), p. 69)

### መንፈሳዊው የቤተ-ክርስቲያን አባል

1 ቆሮንጦስ 2:15-16ን እናንብብ:

"መንፈሳዊ ሰው ግን ሁሉን ይመረምራል ራሱ ግን በማንም አይመረመርም። እንዲያስተምረው የጌታን ልብ ማን አውቆት ነው? (ኢሳይያስ 40:13) እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን።"

በሌላ ትርጉም *"በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ ሰዉ* ሁሉንም ነገር ሊመረምር ይችላል፤ እንደዚያ ያለ ሰው በፍጥረታዊ ሰው አይመረመርም። እንዲያስተምረው የጌታን ልብ ማን አውቆት ነው? እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን።"ይላል፡፡

*መንፈሳዊ* ሰው እውነተኛ ክርስቲያን ነዉ፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ስለተሞላ "*መንፈሳዊ*" ተብሎ ይጠራል፡፡ አሁንም ቢሆን መስፈርቱ፣ ያ ሰው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለው ግንኙነት ነው፡፡ መንፈሳዊ ሰው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር መልካም የሆነና እያደገ የሚሄድ ግንኙነት አለው፡፡ የሱስ *"የሕይወቱ ማዕከል ነው"* ወይም ደግሞ በሌላ አባባል 'የሱስ በልቡ ዙፋን ላይ ነው"፡፡ መንፈሳዊ ሰው እራሱን ሙሉ በሙሉ በፈቃደኝነት ለየሱስ የሰጠ ነው፣ ማለትም በየዕለት ተግባሩ፣ በየጠዋቱ እራሱንና ያለዉን ነገር ሁሉ ለጌታ መስጠቱን ያረጋግጣል፡፡ ይህ ሰው በላዉዶቂያ መልእክት "ትኩስ" ተብሎ ተጠርቷል፡፡ በአስርቱ ቆነጃጅት ምሳሌ ደግሞ "ጠቢብ" ተብሎ ተጠርቷል፡፡ ሮሜ 8:1-17 እና ገላ 5 ስለ መንፈሳዊው ሰው በዝርዝሩ ይናገራሉ፡፡

መንፈሳዊው ሰው 'የተትረፈረፈ ሕይወትን" ይለማመዳል (ዮሐንስ 10:10) ወይም ደግሞ ጳውሎስ እንደገለጸው 'እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ።" (ኤፌሶን 3:19፣ ቆላስያስ 2:9) የሚለውን ሕይወት ይለማመዳል፡፡

## ሥጋዊው የቤተ-ክርስቲያን አባል

አንድ ሰው ለአጭር ጊዜም ሆነ ለረዥም ጊዜ የቤተ-ክርስቲያን አባል ቢሆንም እንኳን ሥጋዊ ክርስቲያን ሊሆን ይችላል፡፡ ምናልባት በዚህ ሰዓት ራስህን ሥጋዊ ክርስቲያን እንደሆንክ ካስተዋልክ፤ አትበሳጭ፣ ይልቁንም ራስህን በየትኛው ጎራ ውስጥ እንደሆንክ በማወቅህ ደስ ይበልህ፤ምክንያቱም ይህን በፍጥነት መለወጥ የምትችልበት እድል አለህና፡፡ ሕይወትህን በመንፈስ ቅዱስ በመምራት ደስተኛ ሕይወት ልትመራ ትችላለህ፡፡ አብዛኞቹ ሥጋዊ ክርስቲያኖች ሥጋዊያን መሆናቸውን እንደማያውቁና የበለጠ የእምነት ልምምድ እንዲኖራቸው ፍላጎት እንዳላቸው ተረድቻለሁ፡፡ አለማወቃቸው ስህተት አይደለም፡፡ በመንፈስ ቅዱስ አመራር ከክርስቶስ ጋር ባለህ የጠበቀ ሕይወት ደስተኛ ሕይወት መምራት ትችላለህ፡፡ (የሱስ በዮሐንስ 15:11: *"ደስታችሁ ሙሉ ይሆን ዘንድ" ይላል) አንተም* ተለውጠህ ቀስ በቀስ፣ ደረጃ በደረጃ 'የተትረፈረፈ ሕይወትን"ልትለማመድ፣ እንዲሁም

አስተማማኝ የዘላለም ሕይወትን ተስፋ ልታገኝ ትችላለህ፡፡ (ዮሐንስ 10:10)

*ጸሎት:- በሰማያት ያለህ አባት ሆይ፣ እባክህ "ሥጋዊ ወይስ መንፈሳዊ ክርስቲያን ነኝ?" የሚለውን ጥያቄ እራሴን እንድጠይቅ እርዳኝ፡፡ ሥጋዊ ክርስቲያን ከሆንኩኝ ይህን ማንነቴን እንዳስተዉል እርዳኝ፡፡ አንተ እንድሆን የምትፈልገዉን ሁሉ ለመሆን ፈቃደኛ እንድሆን እርዳኝ፡፡ እባክህን ወደ ደስተኛ ክርስቲያናዊ ሕይወት እና ተስፋ ወደተገባልኝ ወደተትረፈረፈዉ ዘላለማዊ ሕይወት ምራኝ፡፡ እባክህን ልቤን ኢድስልኝ፡፡ ጸሎቴን ስለመለስክልኝ ከልቤ አመሰግንሃለሁ፡፡ አሜን!*

ጳዉሎስ ስለ ሥጋዊያን የቤተ-ክርስቲያን አባላት በ1ቆሮ. 3:1-4 : የተናገረውን እናንብብ፡-

ኢኔም፥ ወንድሞች ሆይ፥ የሥጋ እንደመሆናችሁ፥ በክርስቶስም ሕፃናት እንደመሆናችሁ እንጂ መንፈሳውያን እንደመሆናችሁ ልናገራችሁ አልቻልሁም። ገና ጽኑ መብል ለመብላት አትችሉም ነበርና ወተት ጋትኋችሁ፤ ገና ሥጋውያን ናችሁና እስከአሁን ድረስ ገና አትችሉም። ቅናትና ክርክር ስለሚገኝባችሁ ሥጋውያን መሆናችሁ አይደላችሁምን? እንደ ሰው ልማድስ አትመላለሱምን? አንዱ:- እኔ የጳውሎስ ነኝ፥ ሁለተኛውም:- እኔ የአጵሎስ ነኝ ቢል ሰዎች ብቻ መሆናችሁ አይደለምን?"

እዚህም ጋር ሥጋውያን ክርስቲያኖችን በዚህ ጎራ የተመደቡበት መስፈርት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ካላቸው የግል ግንኙነት አንጻር መሆኑ አስተዋላችሁ? በነዚህ ጥቂት ቁጥሮች ውስጥ እነርሱ ሥጋውያን እንደሆኑ ሶስት ጊዜ ጠቅሷል፡፡ <ሥጋዊ> ማለት ምን ማለት ነው? ሥጋዊ ማለት:- ይህ ሰው የሚኖረው በራሱ፣ በሥጋዊ ብርታቱ፣ ኃይሉና ችሎታው፣ ማለትም በሥጋው ፈቃድ ነው፡፡ በተጨማሪም በመንፈስ ቅዱስ አልተሞላም ወይም ሕይወቱ በመንፈስ ቅዱስ ሙሉ ቁጥጥር ስር አልሆነም ማለት ነው፡፡

<በዚህ ጎራ ውስጥ ያሉት ሰዎች፣ በአሳፋሪ ወይም በድፍረት ኃጢአት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ናቸው> ብለው አንዳንድ ሰዎች ያስባሉ፡፡ ነገር ግን ይህ አባባል በዚህ ጎራ ውስጥ ያሉትን ሀሉ የሚገልፅ አይደለም፡፡ በእያንዳንዱ ጎራ ዉስጥ የተለያዩ ሰዎች ይገኙበታል፣ ሁሉም አንድ አይነት አይደሉም፡፡

ጳዉሎስ እነዚህን *ሥጋውያን* ሰዎች *"የተወደዳችሁ ወንድሞቼ"* ብሎ ይጠራቸዋል፡፡ ይህ የሚያመለክተዉ ከቤተ-ክርስቲያን አባላት ጋር እንደሚነጋገር ነው፡፡ ጳዉሎስ እንደ "መንፈሳዊ ሰው" ሊያነጋግራቸዉ አልቻለም፡፡ ይህ ማለት በመንፈስ ቅዱስ አልተሞሉም ወይም ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር አልሆኑም ማለት ነው፡፡ "በክርስቶስ ሕጻናት" ከሆኑ ሰዎች ጋር ነው የሚነጋገረው፡፡ ይህም፣ በእምነት ማደግ በሚገባቸው መጠን እንዳላደጉ ያሳያል፡፡ አንድ ሰው ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ እዉቀት ኖሮት በመንፈሳዊነት ግን ያላደገ ሊሆን ይችላል፡፡ መንፈሳዊ እድገት የሚገለጸው ሙሉ በሙሉ ለየሱስ በተሰጠ ሕይወትና ያለማቋረጥ በመንፈስ ቅዱስ ሙላት በሚመራ ሕይወት ነው፡፡ በቆሮንጦስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይታይ የነበረውን የሥጋዊ ክርስትና ችግር መቅረፍ ለጳውሎስ አንገብጋቢ ጉዳይ ነበር

ብዙ ሥጋዊ ክርስቲያኖች በክርስትና ሕይታቸው እርካታ አይሰማቸውም፤ በራሳቸው ሁኔታ ተስፋ ይቆርጣሉ፤ ሕይወታቸው ትርጉም የሌለው እንደሆነ ይሰማቸዋል፤ ወይም ራሳቸውን ለማሻሻል ሁልጊዜ አድካሚ ጥረት ያደርጋሉ፡፡

አንዳንዶች ሥጋዊ ክርስቲያኖች ደግሞ ያሉበትን ሁኔታ ለምደውታል፡፡ "እኛ ኃጢአተኞች ነን፤ ስለዚህ ምንም ልናደርግ አንችልም" ይላሉ።

አንዳንድ ሥጋዊ ክርስቲያኖች ደግሞ ደስተኞች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት በማወቃቸው ደስተኞች ናቸው፡፡ ሥጋውያን የቤተ-ክርስቲያን አባላት በአገልግሎት የተጉ ሊሆን ይችላል፣ ከዚያም በላይ በአጥቢያ ቤተ-ክርስቲያን ወይም በከፍተኛ የአመራር ቦታዎች ላይ መሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ምናልባትም ለእግዚአብሔር አገልግሎት ትልቅ ነገር ያደረጉ ሊሆኑም ይችላሉ፡፡

***ማቴ. 7:22-23፡-*** *"በዚያ ቀን ብዙዎች። ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፥ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፥ በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል። የዚያን ጊዜም። ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።"*

ችግሩ የቱ ጋር ነው? የሱስ አላወቅኋችሁም ነው ያላቸው፡፡ ከየሱስ ጋር የላይ ላይ እንጂ እውነተኛ ግንኙነት አልነበራቸዉም፡፡ ወይ ከልባቸው ለርሱ አልተሰጡም አሊያም መሰጠታቸውን ማስቀጠል አልቻሉም፡፡ የሱስ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በልባቸው ውስጥ አልነበረም፡፡ ከዚህ የተነሳ ከየሱስ ጋር የጠበቀ የግል ግንኙነት አልነበራቸውም፡፡ ስለዚህ " ከየሱስ ጋር እውነተኛ የሚመስል ግን አስመሳይ ግንኙነት ነበራቸው…" (E.G. White, The

Desire of Ages, (1898), p. , S. 676 )። ክርስቶስ በእኛ ውስጥ የማይሆነው መቼ ነው? ስለዚህ ሁኔታ ጥቂት ጠንከር ያሉ ቃላትን አንብቤያለሁ ። ይህን ከመጥቀሴ በፊት ግን፣ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሕይወት የምንመራ ከሆንን ከዚህ በታች ከምናነበው ችግር ነጻ መሆን እንደምንችል ለመግለጽ እፈልጋለሁ፡-

"ከክርስቶስ መንፈስ ጋር ህብረት የሌለው መንፈስ፣ እርሱን ከዶታል (ምንም እንኳን <ክርስቲያን ነኝ> ብሎ ቢያስብም)። ሰዎች ክርስቶስን በክፉ ንግግራቸው፣ እውነተኛ ባልሆኑ ወይም መልካም ባልሆኑ ቃላት፣ በስንፍና ንግግር፣ ሊክዱት ይችላሉ። እንዲሁም ደግሞ የሕይወት ፈተናን በመሸሽና በኃጥአት የተሞላን ደስታ በመሻት ሊክዱት ይችላሉ። ከዓለም ጋር በመመሳሰል፣ ትህትና በሌለበት ባህርይ፤ የራስን አስተሳሰብ በመውደድ፤ በመመጻደቅ፣ ጥርጣሬን የሙጥኝ በማለት፣ ያለምክንያት በመጨነቅ እና ክፉ አስተሳሰቦችን በማሰብ ሊክዱት ይችላሉ። **እነዚህ ሁሉ በማድረግ ክርስቶስ ከእነርሱ ጋር እንዳይደለ ያረጋግጣሉ።**" (E.G. White, *The Desire of Ages,* (1898), p. S. 349)

ይህ ሁኔታ በክርስቶስ ፀጋ በቶሎ መለወጥ ይችላል። ወደዚህ ነጥብ በሶስተኛውና በአምስተኛው ምዕራፍ እንመለስበታለን።

## ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ መሰጠትና ሁሉንም ለእርሱ ማስረከብ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል "እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው" ሮሜ.12:1

"እግዚአብሔር [ከእኔነትና ከኃጢአት ባርነት] ነጻ ሊያወጣን ይፈልጋል። ነገር ግን ይህ ሙሉ በሙሉ መለወጥንና የመላው ተፈጥሮ መታደስን ይጠይቃል፤ ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለጌታ ልንሰጥ ይገባናል።" (E.G. White, *Steps to Christ* (1892), p. 43.2)። ማንነታችን ቁጡ፣ ቅናተኛ፣ ተናዳጅ፣ የሚያጉረመርም ወዘተ ነው። እግዚአብሔር ከእነዚህ ባህርዮች ነጻ ሊያደርገን ይፈልጋል።

"እርሱ [እግዚአብሔር] ፈቃዱን በእኛ ላይ ይፈጽም ዘንድ ራሳችንን [እኔነትን] ለእርሱ እንድንሰጠዉ ይጋብዘናል፡፡ ከኃጥአት ባርነት ነጻ በመውጣት የእግዚአብሔር ልጅነትን ደስታ የመለማመድ ምርጫ በእጃችን ነው፡፡" (E.G. White, *Steps to Christ* (1892) p. 43.4)

***"እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ" ሮሜ 12፥1***

የመጀመሪያውን ሙሉ በሙሉ ለጌታ መስጠታችንን፣ እግዚአብሔር ለእኛ አዲስ ሕይወትን በመስጠት (በዳግም መወለድ) ይባርከዋል (ዮሐንስ 3:1-21)፡፡ ከዳግም መወለድ በኋላ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ለእርሱ እንደተሰጠን መቆየት አለብን (ዮሐንስ 15:1-17)፡፡ ስለዚህ ነጥብ በምዕራፍ ሶስት ውስጥ በሰፊዉ እናያለን፡፡

ሞሪስ ቨንደን ሕይወታችንን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ስለ መስጠት እንዲህ ይላል፡-

"ሕይወትን በከፊል ለጌታ መስጠት አይቻልም፡፡ በከፊል ማርገዝ እንደማይቻል ሁሉ፣ እንዲሁም በከፊል ሕይወትን ለጌታ መሰጠት አይቻልም፡፡ ወይ ሙሉ በሙሉ የእርሱ ነህ ወይም ደግሞ የእርሱ አይደለህም ፤ መሃል ሰፋሪ መሆን አይቻልም (መካከለኛ የሚባል ነገር የለም)፡፡"(Morris Venden, *95 Theses on Righteousness by Faith* (Pacific Press, 1987), p. 63)

ኤለን. ጂ. ኋይት በየቀኑ ስለ መሰጠት እንዲህ ትላለች፡-

"ከየሱስ ጋር አብሮ-ሰራተኛ መሆን የሚፈልጉቱ፡- <ጌታ ሆይ እኔና ለኔ ያለኝ ሁሉ ያንተ ነዉ> የሚሉ ናቸው፣ <የእግዚአብሔር ወንድና ሴት ልጆች ናችሁ> የሚባሉትም እነዚህ ብቻ ናቸው ፡፡"(E.G. White, *Desire of Ages,* p. 623)

ስለዚህ አንድ ሰዉ በቤተ-ክርስቲያን ዉስጥ ሆኖ ሊጠፋ ወይም ላይድን ይችላል ማለት ነው፡፡ ይህ እንዴት አሳዛኝ ነዉ! የአስርቱ ቆነጃጅት ምሳሌና የሎዶቅያ መልእክት ይህንን ነጥብ በደንብ ይገልጹታል፡፡

## *ሥጋዊ ክርስትናን ለመለየት አስቸጋሪ የሆነው ለምንድን ነው?*

የሥጋዊ ክርስቲያን ሕይወት "በሃይማኖት" የተሞላ እስከሆነ ድረስ አንድን ወሳኝ ነገር በሕይወቱ እንዳጣ አይገነዘብም፤ ማለትም ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀና የሚያድን ህብረት

እንደጎደለው አያስተውልም፡፡ ክርስቶስ ሞላ ማንነታችንን እንዲቆጣጠረዉ ካልፈቀድን፣ እርሱ በደጅ ላይ ቆሞ ከማንኳኳት እና <ይህ ሁኔታችሁ ካልተለወጠ ከአፌ እተፋችኋለሁ> ከማለት በስተቀር አያስገድደንም፡፡ (ራዕይ 3:20)

የሥጋዊ ክርስቲያንነታችንን እንዳናስተውል ያደረገን አንድ ሌላ ነጥብ አለ፡- በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሰረተውን አስተምህሮ በተመለከተ ጠንካራ አቋም አለን፡፡ ቢሆንም፣ በተመሳሳይ ጊዜ ተጨማሪ እውነቶችንም ለመቀበል ፈቃደኞች መሆን አለብን፡፡ የተገለጠልንን እውነትን ያለጥርጥር፣ ሙሉ በሙሉ እናምናለን፤ ይህም በርግጥ እጅግ ያስደስተናል፡፡ ብዙ ጠቃሚ እውቀቶች አሉን፡፡ ትክክለኛውን ነገር እንናገራለን፣ እናስተምራለን፡፡ ነገር ግን ይህ ነዉ የሥጋዊነታችንን ችግር እንዳንገነዘብ ያደረገን፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተመራ ሕይወት መኖሬ ሚና መጫወት የለበትምን? ሚና የሚጫወት ከሆነስ፣ ልዩነቱን እንዴት ላውቅ እችላለሁ?

አንድ ፓስተር እንዲህ ጽፎአል፡- “በ40 ቀናት ጸሎት አብራ ከምትሳተፍ አንዲት እህት የስልክ ጥሪ ደረሰኝ፡፡ (ስለ <40 ቀናት የጸሎት እና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ> በምዕራፍ አምስት ላይ በዝርዝር እንመለከታለን)፡፡ እርሷም ይህ የጸሎት ጊዜ ሕይወትዋን እንደቀየረዉ ነገረችኝ፡፡ እድሜዋን በሙሉ በመንፈሳዊ ሕይወትዋ ምን እንደጎደላት ስትጠይቅ ነበር፤ የጎደላት መንፈስ ቅዱስ መሆኑን አሁን ተረዳች፡፡ ምስክርነትዋን ሰምታችሁ ቢሆን ብዬ ተመኘሁ፡፡ በሕይወትዋ ለመጀመሪያ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር የተለየ ግንኙነት ዉስጥ መግባትዋን እንዳስተዋለች ነገረችኝ፡፡ ሌሎችም በሕይወትዋ ለውጥን ተገነዘቡ”(Email an H. Haubeil – received on February 15, 2012)። ሰዎች በሕይወታቸው አንድን ወሳኝ ነገር እንዳጡ ሊያውቁ ይችላሉ፤ ምን እንዳጡ ግን አያውቁም፡፡ ብዙዎች አብዝተው ለማግኘት ምኞቱ አላቸው፤ ነገር ግን ምን እንደሆነና እንዴት እንደሚያገኙት አያውቁም፡፡

በ1 ቆሮንጦስ 3፡ 1-4 ሶስት ጊዜ *“እስካሁን”* የሚለውን ቃል በመጠቀሙ ደስተኛ ነኝ፡፡ “እናንተ እስካሁን ሥጋዊያን ናችሁ” ይላል፡፡ ይህ የሚያሳየዉ ለሥጋዊ ክርስቲያን ወደ መንፈሳዊነት ለመለወጥ የሚቻል መሆኑን ነዉ፡፡ ማንም ሥጋዊ ሆኖ መቅረት የለበትም፡፡ በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ እስካለ ድረስ ይህን ሁኔታውን የመረዳትና የመለወጥ እድል አለው፡፡ እንዴት መንፈሳዊ መሆን እንደሚቻል በኋላ እንመለከታለን፡፡

ሌላው ልንመለከተው የሚገባን ሁኔታ ደግሞ ስለ <ቅናት> እና <ጠብ> ወይም መጽሐፍ

ቅዱስ፡- *"በመካከላችሁ ቅናትና ጠብ አለ" የሚለውን ነው፡፡* ለጳዉሎስ ይህ ዓይነቱ ባህርይ የቤተ ክርስቲያን አባላት በመንፈስ ቅዱስ ሳይሆን እንደ ሌሎች አህዛብ በ*ሥጋ* እንደሚኖሩ *ማረጋገጫ ነበር፡፡ ምንም እንኳን የሃይማኖት ጭምብል ቢያጠልቁም ልክ እንደ ሥጋዊ ሰዉ* ይኖራሉ። ይህ *ማለት* በቤተ-ክርስቲያን ዉስጥ *ያለው ወይም የሚታየው* ጠብ ከ*ሥጋዊ* የቤተ ክርስቲያን አባላት የመነጨ ነዉ ማለት ነዉ? (ይሁዳ ቁ. 19 ይመልከቱ)፡፡ በየሱስ *ዘመን ፈሪሳዊያንና ሰዱቃውያን* እርስ በርስ ይፎካከሩ አልነበረምን? ይህ *ማለት* በወግ አጥባቂዎችና ለዘብተኛ አስተሳሰብ ባላቸው *መካከል ግጭት ያኔም* እንደነበረ ነው፡፡ አንዱ ቡድን የሚያጠብቅ ሲሆን ሌላው ዳግሞ ለዘብተኛ ነበር፡፡ *ነገር ግን ሁለቱም* ቡድኖች *መጽሐፍ* ቅዱስን በትክክል እንደሚተረጉሙና ጥሩ አመለካከት እንዳላቸው እርግጠኛ ነበሩ፡፡ የሱስ *ግን ሁለቱም ሥጋዊያን* እንደነበሩ፤ *ማለትም* በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ እንዳልነበሩ አሳየን፡፡ ዛሬም ተመሳሳይ *ነገር ሊሆን* ይችላል፡፡ ወግ አጥባቂ ክርስቲያኖች *ሥጋዊ* ክርስቲያን ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

እንደ አለመታደል ሆኖ ሰዎች ዛሬም ‹በወግ አጥባቂነት› ወይም ‹በለዘብተኝነት› መነፅር ነው የሚያዩት፡፡ *ነገር ግን* በመጽሐፍ ቅዱስ መሰረት፣ ‹*ሥጋዊ*› ወይም ‹*መንፈሳዊ*› ጎራችንን እንድንለይ ግድድሮሽ ቀርቦልናል፡፡ ለራሳችን ጥቅም ስንል ይህን ማድረግ ይገባናል፡፡ እግዚአብሔር በገላቲያ 6፡7-8 በግልጽ የነገረንን እናስተውል፡-

"... አትሳቱ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና፤ በገዛ *ሥጋው* የሚዘራ ከ*ሥጋ* መበስበስን ያጭዳልና፥ በመንፈስ ግን የሚዘራው ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳል።"

*ሥጋዊ* ሰው ክርስቶስን ለመከተልና ለማስደሰት ይፈልጋል፤ *ነገር ግን* እራሱን ሙሉ በሙሉ ለእርሱ አላስረከበም፤ አስረክቦ ከነበረም በሆነ ምክንያት ወደ ኃላ አፈግፍጓል (ገላትያ 3:3፣ ራዕይ 2:4-5)። *ይህ ማለት* ምናልባት ሳያስተውል በአንድ በኩል እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በራሱ ምኞት ተመርቶ መኖር ይፈልጋል፡፡ *ነገር ግን* ይህ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ሙሉ በሙሉ ሕይወቱን በራሱ እየመራ ስለሆነ፡፡ ‹በልብ ውስጥ ሁለት ነፍሳት አሉ› እንደሚሉት አባባል *ማለት* ነው፡፡ ታዲያ እግዚአብሔር እንደዚህ ባለ ሁኔታ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣልን? ያዕቆብ 4:3 ለዚህ ጥያቄ መልሱን እንዲህ በማለት ይሰጣል፡-"ትለምናላችሁ፥ በምኞቶቻችሁም ትከፍሉ ዘንድ በክፉ ትለምናላችሁና አትቀበሉም"። ይህ በ*ሥጋዊ* አመለካከት ውስጥ ሆኖ

መጠየቅ ማለት እንደሆነ ነው የምረዳው፡፡ ለዚህ ልመና መልስ ቢመጣ ኖሮ፣ ራስ ወዳድነት የበለጠ የሚበረታታ አይሆንም ነበርን? ውጤቱም ይህ የቤተ-ክርስቲያን አባል በተለመደው ሥጋዊ ችሎታና ኃይል ኑሮውን እንዲቀጥል ያጠናክረዋል፡፡ እንደዚህ አይነቱ ምእመን በራዕይ 3፡16፡- "ለብ ያለ" ፣ በማቴዎስ 25 ደግሞ "ሰነፍ" ተብሎ ተጠርቶአል፡፡

## የሱስ ሥጋውያን የቤተ ክርስቲያን አባላትን <ለብ ያሉ> ብሎ የጠራቸው ለምንድን ነው?

እጅግ ብዙ ክርስቲያኖች ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ልምምድ የሌላቸው ለምንድን ነው? ይህን ጥያቄ ለመመለስ በቅድሚያ የሎዶቅያን ሁኔታ እንመለከት፡፡ በሎዶቅያ ቤተ-ክርስቲያን ያሉትን አማኞች የሱስ ለምን <ለብ ያልክ> ብሎ ጠራቸዉ? የሱስ ራሱ ግልጽ የሆነ ፍንጭ ሰጥቶናል፡፡ "እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ" (ራዕይ 3:20) ሲል፣ የሱስ በአማኞቹ ሕይወት ውስጥ ሳይሆን ከውጭ መሆኑን ያሳያል፡፡ እርሱ ከውጭ በደጅ ቆሞ ነበር፡፡ ለምንድን ነው ወደ ውስጥ ያልገባው? መልሱ፡- ወደ ዉስጥ እንዲገባ ስላልተጋበዘ ነው የሚለው ነው፡፡ የእኛን የምርጫ ነጻነት ስለሚያከብር የሱስ በግድ አይገባም፡፡

አማኞች ለምንድን ነዉ የሱስን ከበሩ ውጭ የተዉት? ለዚህ የተለያዩ ምክንያቶች ይኖራሉ፡፡ አንዳንዶች ልክ እንደ ፈሪሳዊዉ ኒቆዲሞስ መንፈሳዊ ሕይወታቸው በአእምሮ እዉቀት ላይ ብቻ ስለተመሰረተ ነው፡፡ ክርስቲያናዊ ኑሮ በዳግም መወለድ የሚገለጸው ራስን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር መስጠት እንደሆነ አያስታውሉም (ከዮሐንስ 3፡1-10 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡ ሌሎች ደግሞ ልክ እንደ ሃብታሙ ወጣት የደቀ መዝሙርነት ዋጋው እጅግ ከፍተኛ ስለሆነ ሁሉንም ለመተው ፈቃደኞች አይደሉም (ከማቴዎስ 19:16-24 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡ የሱስን መከተል እራስን መካድን እና ሕይወት እንዲለወጥ ፈቃደኛ መሆንን ይጠይቃል (ከማቴዎስ 16:24-25 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡ እንዲሁም እራስን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር መስጠትን ይጠይቃል (ሮሜ 12:1)፡፡ የሱስን ከበሩ ውጭ መተው ከቸልተኝነትና ከየሱስ ጋር በቂ የህብረት ጊዜ ካለመውሰድ ምክንያት የተነሳ ሊሆን ይችላል፡፡

የሱስ በራእይ 3፡20 ላይ የጠቀሰውን የለብታ ምክንያት ደግሜ ለመግለጽ እፈልጋለሁ፡-

*"እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ"* የሚለው ጥቅስ የሱስ በአማኙ ሕይወት ውስጥ ሳይሆን፤ ከውጭ ወይም ጥግ ይዞ እንደቆመ ያሳያል:: አስተውሉ:- <ማንም ለሁለት ጌቶች መገዛት አይችልም> ማቴዎስ 6፡24:: ወይ አንተ ነህ፣ ወይ የሱስ ነው ሕይወትህን የሚመራው:: ስለዚህ ይህ ለብታ አንድ ሰው ከክርስቶስ ጋር ያለውን ግንኙነት ይገልጻል (ያሳያል):: ምናልባት በሌሎች ጉዳዮች ላይ ያ ሰው ለብ ያለ ላይሆን ይችላል::

ምሳሌ:- አንድ ሰዉ በሚሰራበት መሥሪያ ቤት በሥራው እጅግ ውጤታማ ሆኖ ሚስቱን ቸል ሊላት ይችላል:: በርግጥ በስራ ቦታው የተዋጣለት ነው፣ ነገር ግን የትዳር ግንኙነቱ ለብ ያለ ነው:: አንድ ሰዉ በጣም የተሰጠ የቤተክርስቲያን አባል ወይም ጠንካራ የቤተክርስቲያን መሪ ወይም የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ወይም ፕሬዝደንት ሆኖ ከክርስቶስ ጋር ባለው ግንኙነት ግን ለብ ያለ ሊሆን ይችላል:: ያ ሰው የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት ከመትጋቱ የተነሳ ከክርስቶስ ጋር ያለውን የግል ግንኙነት ችላ ይላል:: ይህንን ለብታነት ነው ክርስቶስ ለማስወገድ የሚፈልገው:: አንድ ሰው በእግዚአብሔር ሥራ (በቤተክርስቲያን አገልግሎትና በወንጌል ሥርጭት) ባተሌ ከመሆኑ የተነሳ ፤ የአገልግሎቱን ጌታ ችላ ማለቱ እጅግ የሚያሳዝን ነው::

## የአስርቱ ቆነጃጅት ምሳሌ

ስለ አስርቱ ቆነጃጅት የሱስ የተናገረዉ ምሳሌ ስለመንፈሳዊና ሥጋዊ ክርስቲያኖች ምን ያሳየናል?

- አስሩም ቆነጃጅት(ደናግልት) ናቸው
- ሁሉም ኩራዝ ይዘዋል
- ሁሉም ሙሽራዉን ሊቀበሉ ወጥተዋል
- ሁሉም ዳግም ምጻቱን ይጠባበቃሉ
- ሁሉም አንቀላፍተዋል
- ሁሉም የማንቂያውን ድምጽ ሰምተው፣ ነቅተዋል
- ሁሉም መብራታቸውን አዘጋጅተዋል
- የሁሉም ኩራዞች እየበሩ ነበር
- ግማሾቹ መብራታቸው ሊጠፋባቸዉ እንደሆነ ተገንዝበዋል

ሁሉም መብራቶቻቸውን ስላዘጋጁ የሁሉም እየበራ ነበር፤ ነገር ግን የሚበራ ኩራዝ ዘይት ያስፈልገዋል፡፡ ከአጭር ጊዜ በኋላ አምስቱ መብራታቸው ሊጠፋ እንደሆነ አወቁ፡፡ የሰነፎቹ ደናግልት መብራት ለአጭር ጊዜ ብቻ መብራቱ የሚያሳየን፣ ትንሽም ቢሆን እንኳ መንፈስ ቅዱስ እንደነበራቸው ነው፡፡ ነገር ግን የያዙት በቂ አልነበረም፡፡ ዘይቱ ጥቂት ነበር፡፡ ያ ነበር ዋናው ልዩነት፡፡

አምስቱ ሰነፎች ዘይት ከገዙ በኋላ ተመልሰው የሱስ በሩን እንዲከፍትላቸዉ ሲጠይቁት፣ ***"አላዉቃችሁም"*** ብሎ መለሰላቸዉ፡፡ ዘይትን፤ ማለትም መንፈስ ቅዱስን ፍለጋ የጀመሩት ከረፈደ በኋላ ነው፡፡ በሩም ተዘጋባቸው፡፡

ይህ የየሱስ ምሳሌ የሚያሳየው፣ ከየሱስ ጋር የሚኖረን የግል ግንኙነት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ከሚኖረን ግንኙነት ጋር እንደሚያያዝ ነው፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት የማይፈቅደውን ማንንም ቢሆን የሱስ አያውቀውም፡፡ በሮሜ 8:8-9 እንዲህ ይላል፡፡ "በሥጋ የሚኖሩት እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም፡፡ *... የእግዚአብሔር መንፈስ የሌለው እርሱ የእርሱ ወገን አይደለም፡፡"*

በእርግጥ ከየሱስ ጋር እውነተኛ የግል ግንኙነት ሊኖረን የሚችለው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ብቻ ነው፡፡ 1 ዮሐንስ 3:24 እንዲህ ይላል፡- *"በዚህም [የሱስ] በእኛ እንዲኖር ከሰጠን ከመንፈሱ እናውቃለን"*፡፡ ይህ ማለት፣ በመንፈስ ቅዱስ የመሞላቴ እርግጠኛነት፣ እኔ በየሱስ፣ የሱስም በእኔ የመኖሩ ማረጋገጫ ነው፡፡

ያች እህት በ40 ቀናት የጸሎት እና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ ያገኘችው ልምምድ በእርግጠኝነት የዚህ አይነት ልምምድ ነበር ማለት ነው፡፡ በውስጥዋ መንፈስ ቅዱስ በመኖሩ ከእግዚአብሔር ጋር ሙሉ በሙሉ የተለየ ልምምድ ውስጥ ከመግባትዋ የተነሳ እርስዋ ለውጡን ተለማመደች፤ ሌሎችም ይህን ለውጥ በእርስዋ ሕይወት ተመለከቱ፡፡ ይህን ጽሁፍ ካጠናች በኃላ አንዲት በደቡብ ጀርመን የምትኖር እህት የሚከተለውን ፃፈች፡- "40 ቀናት የጸሎት እና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ ለክርስቶስ ዳግም ምጻት ለመዘጋጀት" ከሚለው በዴኔስ ስሚዝ ከተጻፈው መጽሐፍ በተጨማሪ ይህ መጽሐፍ በሕይወቴ ለረዥም ጊዜ ስጠባበቀው የኖርኩትን በረከት አምጥቶልኛል፡፡ ልክ እንደ ሌሎች የቤተ ክርስቲያን አባላት፣ እኔና አንዲት በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለች እህት በእምነት ልምምዳችን ሁልጊዜ አንድ ነገር እንደሚጎድለን ይሰማናል፤ አሁን ግን የሱስ ወደ ዉስጣችን በመግባት ጉድለታችንን ሊሞላልንና

ሊለዉጠን የሚችልበትን ልምምድ አገኘን፡፡ እርሱ እስካሁን ድረስ በእኛ ዉስጥ ደረጃ በደረጃ እየሰራ ወደ እርሱ እያቀረበን ነዉ" (Email an H. Haubeil, 31 March 2013)

አንድ ወንድም የሚከተለውን ጻፈ፡- "ወደ የግል መንፈሳዊ መነቃቃት የሚመራ መንገድ" የሚለው መጽሐፍ ልቤን በጣም ነክቶታል፡፡ በተለይ ስለ አስርቱ ቆነጃጅት የተጻፈዉ እና በሮሜ 8፡9 ላይ፡- *'የእግዚአብሔር መንፈስ የሌለው እርሱ የክርስቶስ ወገን አይደለም'* የሚለዉ ጥቅስ በጣም አስደንግጦኛል፡፡ የመንፈስ ፍሬዎችን በሕይወቴ ማየት ስላልቻልኩ፣ መንፈስ ቅዱስ በውስጤ ስለመኖሩና በውስጤ እየሰራ ስለመሆኑ እርግጠኛ አልነበርኩም፡፡ ዛሬ ሰንበት ከሰዓት፣ መጽሐፉን አንብቤ ከጨረስኩኝ በኃላ ልገልጸው ከምችለው በላይ በሀዘን ተዋጥኩኝ፡፡ ከዚያ በገጽ 105 ላይ ያለውን ሞዴል ጸሎት ካነበብኩኝ በኃላ መንፈስ ቅዱስን የመቀበል እና እግዚአብሔር አብ እንደ እርሱ ፈቃድ ሕይወቴን እንዲለዉጥልኝ ጥልቅ ፍላጎት አደረብኝ፡፡ ስለዚህ የሚባርክ ፅሁፍ አመሰግናለሁ፡፡" A.P.

የሥጋዊ ክርስቲያን በጣም አሳዛኝ የሆነ ነገር ቢኖር ይህ ሁኔታዉ ካልተቀየረ በስተቀር የዘላለምን ሕይወት አለመውረሱ ነው፡፡ *'የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም"* ሮሜ 8:9

ስናጠቃልለው፡- በመንፈሳዊና በሥጋዊ ክርስቲያን መካከል ያለው ልዩነት መንፈስ ቅዱስን ከመቀበል ጋር የተገናኘ ነው፡፡ መንፈሳዊ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ነው፡፡ ሥጋዊ ክርስቲያን ግን ያልተሞላ ወይም በበቂ ሁኔታ ያልተሞላ ነው፡፡

ሥጋዊ ክርስቲያን መሆንህን ከተገነዘብክ አትበሳጭ፡፡ እግዚአብሔር መፍትሄዉን፤ መንፈስ ቅዱስን አዘጋጅቶልሃል፡፡ በአንዳንድ ቡድኖች መንፈስ ቅዱስ ያለአግባብ ተጋኖአል፤ በሌላዉ ቦታ ደግሞ ጭራሽ ችላ ተብሎአል፡፡ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ሚዛናዊነት እንድንመጣ እግዚአብሔር ይርዳን፡፡

## በቀድሞዋ እና በመጨረሻው ዘመን ቤተ-ክርስቲያን መካከል ያለው ንጽጽር

የቀድሞዋን ቤተ-ክርስቲያን ከአሁንዋ ጋር ስናነጻጽራት የቀድሞዋ በመንፈሳዊ ሰዎች የተሞላች እንደሆነች እንገነዘባለን፡፡ በኃይልና በፍጥነት የማደጋቸዉ ምክንያት ይህ ሁኔታቸዉ እንደሆነ የሐዋርያት ስራ መጽሐፍ ይነግረናል፡፡ ሌላ መፍትሄ (ረዳት)

አልነበራቸዉም፡፡ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ነበራቸዉ፡፡ እኛም ዛሬ አስደናቂ ስልቶች (እቅዶች) ሊኖሩን ይችላሉ፡፡ ነገር ግን የመንፈስ ቅዱስ እጥረት አለብን፡፡

ኤ. ደብልዩ. ቶዘር እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፡- “መንፈስ ቅዱስ ዛሬ ከቤተ ክርስቲያናችን ቢወሰድም፣ ከምናከናውናቸው ነገሮች 95%ቱ እንደነበር እንደተለመደው ይቀጥላሉ፣ ማንም ልዩነቱን አያስተውልም፡፡ ነገር ግን፣ ከቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ ቢወሰድ ኖሮ፣ ያከናውኑ ከነበሯቸው ነገሮች 95%ቱ (ይህ ማለት ሁሉም ነገር ማለት ይቻላል) በቆመና እያንዳንዱም ሰው ልዩነቱን ባስተዋለ ነበር፡፡” (Dr. S. Joseph Kidder, *Anleitung zum geistlichen Leben* (Andrews University), PPP Folie 2)

## ያለ መንፈስ ቅዱስ መኖርን ለምደነዋልን?

## የዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን በይበልጥ ሥጋዊ ክርስቲያኖችን ያቀፈች ናትን?

ኃይል ያጣነውና በከፍተኛ መጠን ድል የሌለን የሆንነው በዚህ ሳቢያ ይሆንን? በብዙ ሥፍራዎች ቤተ ክርስቲያናችን የማታድገው ሥጋዊ አመለካከት ያላቸው ምእመናን በውስጧ በመኖራቸው ይሆንን? በብዙ ቦታዎች የሚታዩት አብዛኞቹ አደገኛ ችግሮቻችን ከሥጋዊ አመለካከታችን የተነሳ የመጡ ይሆንን? በግለሰብ ደረጃም ሆነ እንደቤተክርስትያን የችግሮቻችን ማዕከል የመንፈስ ቅዱስ እጦት እንደሆነ በበለጠ እያስተወላን እንሄዳለን፡፡ በግለሰብ ደረጃ ያሉብንን ችግሮች በእግዚአብሔር እርዳታ በፍጥነት መለወጥ እንችላለን፡፡ (በምዕራፍ 3 ላይ ስለዚህ የበለጠ እናጠናለን)

የሚከተለው ዓረፍተ ነገር ለአገልጋዮች የተሰጠ ቢሆንም በእርግጥ ለሁሉም ሰው የሚያገለግል ነው፡-

ጆሃንስ ሜገር ሲናገር እንዲህ አለ፡- “ጳውሎስ በሥጋዊና በመንፈሳዊ ክርስቲያኖች መካከል፣ በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉትና በሕይወታቸው ውስጥ ለመንፈስ ቅዱስ ሥፍራ በሌላቸው መካከል፣ በመንፈስ ቅዱስ በተጠመቁትና፣ ለመንፈስ ቅዱስ ቦታ በማይሰጡት መካከል ልዩነት እንዳለ ግልጽ አድርጓል፡፡

ለአንድ ቄስ (ፓስተር) ይህ ማለት፡- ጥሩ የሆነ የሥነ-መለኮት ሥልጠና ሊኖረኝ ይችላል፤ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈባቸውን የጥንት ቋንቋዎችን ጠንቅቄ የማውቅ ይሆናል፣ ጥቅሶችንም

በደንብ መግለጽ የምችል ልሆን እችላለሁ፤ ታላላቅ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶችን በመመራመር የደረስኩበትና የተረዳሁ፣ እንዲሁም በተለያዩ ዘመናት የነበሩትን የሥነ-መለኮት ጥናቶች ጠንቅቄ አውቅ ይሆናል፤ የአሰባበክ ዘዴን ጥሩ አድርጎ በመረዳት ከጊዜው ጋር ወቅታዊነት ያላቸውንና ተግባራዊ የሆኑ ስብከቶች እሰብክ ይሆናል፤ ይህ ሁሉ እውቀትና መክሊት ቢኖረኝም በመንፈስ ቅዱስ ያልተሞላሁ ልሆን እችላለሁ፡፡ መጽሐፍት፣ ትምህርት፣ ጥሩ የቴክኒክ ቁሳቁሶች፣ እንዲሁም ሰዎችን የሚስብ ልዩ ችሎታ፣ የመንፈስ ቅዱስ አለመኖርን ሊሸፍን ይችላል፡፡ መስበክ፣ በሕብረት መጸለይ፣ የቤተ-ክርስቲያንን ፕሮግራሞች ማደራጀት፣ የወንጌል ስርጭት ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፣ የፓስተርነት የምክር አገልግሎት መስጠት፣ እነዚህ በሙሉ በቀለም ትምህርት ሊገኙና ከመንፈስ ቅዱስ ውጭ ተግባራዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ኤለን ጂ. ኋይት ስለዚህ አደገኛና የመከሰት ዕድል ስላለው ሁኔታ እንዲህ ትገልጻለች፡- "የእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል እጅግ በጥቂቱ የሚታይበት ምክንያት፣ አገልጋዮች ከእርሱ ውጭ መስራት ስለለመዱ ነው" (ኤለን ጂ. ኋይት፣ ቴስቲሞኒስ ፎር ዘ ቸርች፣ ቅጽ 1፣ (1868)፣ ገጽ፣ 383.1)፡፡ ምንም እንኳን መሠረታዊ እና ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ለአንድ ፓስተር አስፈላጊ ቢሆኑም፣ ያለማቋረጥ በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ፈቃደኛ መሆኑ ከዚያ የበለጠ ነው"፡፡ (Johannes Mager, *Auf den Spuren des Heiligen Geistes (Following the Steps of the Holy Ghost),* (Lüneberg, 1999), pages 102-103.)

***ለማጠቃለል ያህል፡-** ሥጋዊ መሆን ማለት በሰብአዊ ሰው ኃይልና ችሎታ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ሙላት ውጪ ወይም መጠኑ አነስተኛና በቂ ባልሆነ መንፈስ መኖር ማለት ነው፡፡*

## በሥጋዊ ክርስትና ውስጥ ያለ ዋና መሰናክል

ታላላቆቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ሥነ-ምግባራት፡- ጠላትን መውደድ፣ ስለ ሁሉም ነገር ሰዎችን ይቅር ማለት፣ ኃጢአትን ማሸነፍ፣ ወ.ዘ.ተ ተፈጻሚ ሊሆኑ የሚችሉት በሰብአዊ ጥረት ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ ነው፡፡ ይህ የሚያመለክተው በሥጋዊ ክርስትና ውስጥ ያለው ዋናው ችግር በሰብአዊ ኃይል ብቻ የተደገፈ መሆኑ ነው፡፡ በራሳችን ኃይል ብቻ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ አንችልም፡፡ ከዚህ ርዕስ ጋር የሚሄዱ ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን እናንብብ፡-

ኢሳይያስ 64፡6፡ "ጽድቃችንም ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው፡፡"

ኤርምያስ 13፡23 "በውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዝንጕርጕርነቱን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን? በዚያን ጊዜ ክፋትን የለመዳችሁ እናንተ ደግሞ በጎ ለማድረግ ትችላላችሁ፡፡"

ሕዝቅኤል 36፡26-27፡ "አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ፤ የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ፣ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ፡፡ መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ በትዕዛዜም አስሄዳችኋለሁ፣ ፍርዴንም ትጠብቃላችሁ ታደርጉትማላችሁ፡፡"

ሮሜ 8፡7፡- "ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና፤ ለእግዚአብሔርም ሕግ አይገዛምና፤ መገዛትም ተስኖታል"

ኤለን ኋይት ግልጽና ትክክለኛ በሆነ መልኩ እንዲህ ትላለች፡- "በራሱ ሥራ፣ ሕግን በመጠበቅ ሰማይ ለመድረስ የሚጥር ሰው፣ የማይቻል ነገር እየሞከረ ነው፡፡ እርግጥ ነው፣ ሰው ካልታዘዘ መዳን አይችልም፣ ሆኖም ግን መታዘዙ (ተግባራቱ) ከራሱ የመነጩ መሆን የለባቸውም፤ በጎ ነገር መፈለግንም ሆነ ማድረግን ክርስቶስ በርሱ ውስጥ መሥራት አለበት" (E.G. White, *Review and Herald,* July 1, 1890)

እነዚህ ማጣቀሻዎች በቂ በሆነ ሁኔታ የሚያሳዩት እኛ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከመንፈስ ቅዱስ ውጭ ማድረግ እንደማንችል ነው፡፡ ዋናው ነገር ፈቃዱን ለመፈፀም ፈቃደኛ መሆናችን ነው፤ እግዚአብሔር ደግሞ እንድንፈጽመው ብርታት ይሰጠናል፡፡ የዚህን የጽድቅ በእምነት አስተምህሮ መረዳት እጅግ በጣም አስፈላጊና ነጻነትን የሚሰጥ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ስለዚህ ጉዳይ፣ እዚህ ጋር በጥልቀት መወያየት አንችልም፡፡

## አንድ ሰው ከአቅሙ በላይ የሆነን ነገር ለማድረግ ሲሞክር ምን ሊከሰት ይችላል?

<ብዙ ጊዜ ሞከሬ ሞከሬ አቃተኝ!> <እንደገና ደግሜ ተመሳሳይ ስህተት ውስጥ ገባሁ!> የሚሉት ልምምዶች በተወሰነ መጠን ተስፋ የመቁረጥ ስሜትን ያስከትላሉ፡፡

እንዳተዋለኩት ከሆነ፣ ይህ ችግር የሚጠነክረው በዕድሜ ጠና ካሉት ሰዎች ይልቅ በወጣቶች ላይ ነው፡፡ በዕድሜያአቸው ጠና ያሉ ሰዎች በቤተሰብ፣ በትምህርት ቤትና በሥራ ገበታ ላይ የኃላፊነት ሸክም ያለበትን ሕይወት ለምደዋል፡፡ ስለዚህ የወጣቶችን ያህል በቀላሉ

ተስፋ በመቁረጥ አይበሳጩም፡፡ በርግጥ ችግሩ በወጣቶችና በዕድሜ ጠና ባሉ ሰዎች ላይ እኩል ነው፡፡ ልዩነቱ፣ ወጣት የሆኑት ለነገሩ የበለጠ ቦታ ይሰጡታል፡፡ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ፣ የእምነትን ጎዳና በራስ ብርታት መጓዝ የእያንዳንዱ ሥጋዊ ክርስቲያን ግንባር ቀደም ችግር ነው፡፡

ይህን ችግር እንዴት ነው የምንፈታው? አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ዕርዳታ ለማግኘት እጅግ ይጸልይና ለመተግበርም እጅግ ይተጋ ይሆናል፡፡ ሌላው ሰው ደግሞ፣ <እንደዚህ አይነት ውስን አዕምሮ ያለን ልንሆን አይገባንም> ብሎ ሊያስብ ይችላል፡፡ ከዚያም ነገሮችን አቅልሎ በማየት ነጻነት ይሰማዋል፡፡ ምናልባት ደግሞ ሌላው ሰው እምነቱን ሙሉ በሙሉ በመተዉ ጥሩ ስሜት ይሰማው ይሆናል፡፡ ነገር ግን ዋናው ችግሩ ያለው፡- እነዚህ ጥሩ የሚመስሉ መፍትሔዎች የሃሰት መፍትሔዎች መሆናቸው ላይ ነው፤ ምክንያቱም የምርጫዎቻችን ውጤቶች ፈጥነው ወይም ዘግይተው መምጣታቸው አይቀሬ ነው፡፡ ትክክለኛው መንገድ ግን፡- የእግዚአብሔርን ሕግጋት ከልብ መቀበል ነው፤ ምክንያቱም እነርሱ በእግዚአብሔር ፍቅር ለጥቅማችን ሲባል የተሰጡን ናቸው፡፡ ሆኖም ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ የእግዚአብሔር ኃይል ያስፈልገናል፡፡ ትክክለኛው መንገድ፡- በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ውስጥ ሆኖ፣ በደስታ፣ በተነሳሽነት፣ በብርታት፣ በፍሬያማነትና በአሸናፊነት መኖር ነው፡፡

## ዋናው ችግር

ዋናው ችግር ከሥጋዊ ክርስትና ጋር የተያያዘ እንደሆነ አስተውለናል ብዬ አስባለሁ፡፡ የሱስ ለምን ለብ ያሉ ተከታዮች እንዲኖሩት እንደማይፈልግ እጅግ ግልጽ እየሆነ አልመጣምን? ሥጋዊ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ሊሰጣቸው እንደሚፈልገው አይነት የተትረፈረፈ ሕይወት የላቸውም፣ ከዛም ባሻገር ብዙዎቹ ሳያውቁት (ባያስተውሉትም) መጥፎ አርአያ ናቸው፡፡ ችግሩ እኛ ከምናስበው ይልቅ አደገኛ ነው፡፡ "በግማሽ ልብ የሚንቀሳቀሱ ክርስቲያኖች ከአምላክ የለሾቹ (ከማያምኑቱ) የባሱ ናቸው፤ ምክንያቱም አታላይ ቃላቸውና አቋም አልባነታቸው ሌሎችን ከትክክለኛው መንገድ ይወጡ ዘንድ ስለሚመራ ነው፡፡" (EGW Letter 44, 1903, quoted in *Adv. Bible Commentary,* Vol.7, p.963 on Rev. 3: 15-16)

## ወደ ሥጋዊ ክርስትና ሊመሩ የሚችሉ ምክንያቶች

ወደ ሥጋዊ ክርስትና የሚመሩ ምክንያቶች ወይም ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. **አለማወቅ፡-** "በመንፈስ ቅዱስ የተመራ ሕይወት" የሚለውን ኃሳብ በበቂ ሁኔታ አልመረመርነውም (አላጠናነውም) ወይም ደግሞ ወደ ተግባር የምንለውጥበትን ቁልፍ አላገኘንም፡፡

2. **አለማመን ወይም የእምነት ማነስ፡-** ሕይወትን ሙሉ በሙሉ ለየሱስ አሳልፎ ማስረከብ በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት የመጀመሪያው መስፈርት ነው፡፡ አለማመን ወይም የእምነት ማነስ ሊከሰት የሚችለው ባለማወቅ ወይም ደግሞ ምናልባት <እግዚአብሔር እኛ ከምንፈልገው በተለየ ሁኔታ ይመራናል> በሚል ፍርሃት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም ማለት፣ እኛ በእግዚአብሔር ፍቅርና ጥበብ ላይ በበቂ ሁኔታ መታመን የለንም ማለት ነው፡፡

3. **የተሳሳቱ አመለካከቶች፡-** አንድ ሰው ሙሉ በሙሉ ወይም በቂ ባልሆነ ሁኔታ በመንፈስ ቅዱስ ሳይሞላ፣ እንደተሞላ ሊሰማው ይችላል፡፡ ይህ አብዛኛውን ጊዜ የሚከሰት ችግር ይመስላል፡፡

4. **እጅግ በሥራ መወጠር፡-** ብዙ ሰዎች <እጅግ በሥራ ስለተወጠርን ከክርስቶስ ጋር ያለንን ግንኙነት የምናጠናክርበት በቂ ጊዜ የለንም> ብለው ያስባሉ፡፡ ወይም ጊዜ ቢወስዱም እንኳን ከእግዚአብሔር ጋር በጠበቀ ሁኔታ በመገናኘት ረገድ ምንም ለውጥ አያሳዩም፡፡

5. **ድብቅ ኃጢአት፡-** ወይም ደግሞ በሙሉ ልብ ንስሃ አለመግባት፡- ይህ እንደ ተቋረጠ የኤሌክትሪክ ኃይል ነው፣ ማለትም ከእግዚአብሔር ኃይል ጋር ግንኙነቱ ተቋርጧል፡፡

6. **በአብዛኛው በስሜት መመላለስ፡-** የእግዚአብሔር ቃል፡- "ጻድቅ በእምነት ይኖራል" ይላል፡፡ ውሳኔዎችን ስወስን እምነቴን የምጥለው በእግዚአብሔር ላይ ነው ወይስ በራሴ ስሜት? ይህ የሮጀር ሞርኖ አገላለጽ በጣም አስደንቆኛል፡- "ከክርስቶስና ከነቢያት ቃላት ይልቅ ሰዎች የራሳቸውን ስሜቶች እንዲያዳምጡ ከፉ መናፍስት ያበረታቷቸዋል፡፡ ሰዎች ምን እየተከሰተ እንዳለ ሳያስተውሉ፣ ሕይወታቸው በመናፍስት ቁጥጥር ስር የሚሆንበት ከዚህ የተሻለ መንገድ የለም፡፡" (Roger Morneau, A Trip into the Supernatural, Review and Herald 1982, p. 43)

## በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቼ እያለሁ ለምን መንፈስ ቅዱስ እንዲሰጠኝ እጠይቃለሁ?

በአንድ በኩል መንፈስ ቅዱስ የተሰጠን በውስጣችን እንዲቆይ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መንፈስ ቅዱስን በቀጣይነት ያለማቋረጥ በእምነት መጠየቅ አለብን፡፡ የዚህ፣ እርስ በርሱ የሚቃረን የሚመስል ጥያቄ መፍትሔ ምንድን ነው?

**በአንድ በኩል፡-**

የሱስ በዮሐንስ 14፡17 “ነገር ግን እርሱ [መንፈስ ቅዱስ] ከእናንት ዘንድ ስለሚኖር፣ በውስጣችሁም ስለሚሆን” ብሏል፡፡ በሐዋ. ሥራ 2፡38 ደግሞ እንዲህ ይላል፡- “ንስሃ ግቡ፣ እያንዳንዳችሁ በየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፣ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ፡፡”

**በሌላ በኩል፡-**

ክርስቶስ ስለ ጸሎት ሲያስተምር በሉቃስ 11፡9-13 ላይ እንዲህ አለ፡- “ለምኑ፣ ይሰጣችሁማል፤ … በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?”፡፡ ኤፌሶን 5፡18 ላይም እንዲህ ይላል፡- “ጌታ ራሱ አዝዟል፣ መንፈስ ይሙላባችሁ…”፡፡ ይህ ቃል፣ ዋናው የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጅ (ኦሪጅናል) በሆነው የግሪክ ቋንቋ፣ <ያለማቋረጥ፣ ሁልጊዜ እንደ አዲስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ> የሚል ሃሳብ የያዘ ነው፡፡

**መፍትሔ፡**

ኤለን ጂ. ኋይት እንዲህ ትላለች፡- “የመንፈስ ቅዱስ አሠራር ሁልጊዜ ከተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ጋር አብሮ ይሄዳል፡፡ በተፈጥሮ ዓለም ውስጥ እንዳለ ሁሉ፣ በመንፈሳዊው ዓለምም እንዲሁ ነው፡፡ ተፈጥሮአዊው ሕይወት መኖሩን የሚቀጥለው በመለኮት ኃይል ነው፡፡ ነገር ግን ይህ የሚሆነው በድንገተኛ ተዓምር ሳይሆን፣ በአካባቢያችን የቀረበልንን በረከት በመጠቀም ውስጥ ነው፡፡ እንደዚሁም መንፈሳዊ ሕይወት መኖሩን የሚቀጥለው የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚሰጣቸውን እነዚያን በረከቶችን ጥቅም ላይ በማዋል ነው፡፡ የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሰው፣ <ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፣ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ … ድረስ> (ኤፌ. 4፡13) ለማደግ ከፈለገ፣ የሕይወትን እንጀራ መብላትና የድነትን (የመዳንን) ውሃ መጠጣት አለበት፡፡ በሁሉ ነገር በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተሰጡትን መመሪያዎች በመከተል የሚተጋ፣ የሚያድግ፣ የሚጸልይና የሚሠራ መሆን አለበት፡፡” (E.G. White, *The Acts of the Apostles,* (1911), p. 284.2)

ስንወለድ ሕይወትን ተቀብለናል፡፡ ይህንን ሕይወት ለማስቀጠል መብላት፣ መጠጣት፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ወዘተ ማድረግ አለብን፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወታችንም እንዲሁ ነው፡ መንፈስ ቅዱስ በኛ ይኖር ዘንድ፣ በውሃና በመንፈስ በተጠመቅንበት ጊዜ (እንደገና ስንወለድ) መንፈስ ቅዱስን ተቀብለናል፡፡ ይህን መንፈሳዊ ሕይወት እንዳለ ጠብቆ ለማቆየት እግዚአብሔር የሚሰጣቸውን መንፈሳዊ መመሪያዎች መከተል ይኖርብናል፣ ማለትም መንፈስ ቅዱስን መሞላት፣ የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ፣ መጸለይ እና መመስከር ወዘተ ጥቅም ላይ ማዋል ተገቢ ነው፡፡

የሱስ በዮሐንስ 15፡4 ላይ: "በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ" ይላል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ኤለን ኋይት እንዲህ ትላለች፡- "በክርስቶስ መኖር ማለት ሳያቋርጡ የእርሱን መንፈስ መቀበል፤ ያለመቆጠብ ለእርሱ አገልግሎት መሰጠት ማለት ነው" (E.G. White, *The Desire of Ages,* (1898), p. 676.2)

ለዚህ ነው በየቀኑ መንፈስ ቅዱስን በእምነት መጠየቅ ያለብንና በየማለዳው ራሳችንንና ያሉንን ነገሮች በሙሉ አሳልፈን ማስረከብ ያለብን፡፡

## የቱ ጋር ነው ያለሁት?

አሁን እጅግ ወሳኙ ጉዳይ በየትኛው ቡድን (ጎራ) ውስጥ እንደሆንኩኝ መለየት ነው፡፡ የትኛው ቡድን (ጎራ) ውስጥ ነው ያለሁት?

እናቴ የ20 ዓመት እድሜ ሳለች፣ እግዚአብሔር በሕይወትዋ ውስጥ ስለመኖሩ ወይም ስላለመኖሩ አንድ ሰው ለጠየቃት ጥያቄ ስለ እምነት ጉዳይ ምንም ፍላጎት እንደሌላት መልስ ሰጠችው፡፡ እርሱም መልሶ፡- <ዛሬ ማታ ብትሞቺስ?> ሲል ጠየቃት፡፡ ይህ ጥያቄ ከፉኛ ልቧን ቢነካውም፣ አዎንታዊ ተጽዕኖ ነበረው፡፡ ሕይወቷን ለየሱስ እንድትሰጥና የእርሱን ቤት ክርስቲያን ለመቀላቀል ውሳኔ ታደርግ ዘንድ መራት፡፡

ምናልባት ይህ ጥያቄ አንተንም ይረዳህ ይሆናል::

*ኢያድርስና.... ዛሬ ብትሞት ኖሮ...! (በልብ ድካም? በድንገተኛ አደጋ?)*

*ከየሱስ ክርስቶስ ጋር የዘላለምን ሕይወት እንደምትኖር እርግጠኛ ነህ?*

*እርግጠኛ ሳትሆን እንዳትቀር!*

## ለሕይወት ደስታን የማግኘት ጉዳይ ነው

የዚህን ችግር (የመንፈስ ቅዱስን እጦት) ጥልቀት ስረዳ እጅግ በጣም ደነገጥኩ፡፡ ከዚህ በታች ያለውን አንቀፅ ከመጨመሬ በፊት ብዙ አሰቤያለሁ፤ ፀልያለሁ፡፡ ይህ አሁን ለምምናረው ሕይወት ደስታን የማግኘት ጉዳይ ስለሆነ፣ የዘላለም ሕይወትንም የማግኘት ጉዳይ ስለሆነ፣ እንዲሁም በትዳር፣ በቤተሰብ፣ በሥራ እና በአገልግሎታችን ውስጥ ከሚያስከትልልን አዎንታዊ ተፅዕኖ ጋር ይያያዛል ብዬ ስላመንሁ ይህንን አንቀፅ ጨምሬአለሁ፡፡ በርግጥ ይህ ማንን እንደሚመለከት አላውቅም፡፡ ነገር ግን ይህ ኃሳብ እኔን ስላገዘኝ የሚመለከታቸውንም ሰዎች መርዳት እፈልጋለሁ፡፡ ይህ እጅግ ወሳኝ ነገር ነው፣ ማንኛውም ሥጋዊ ሰው ይህን ማወቅ አለበት፤ አለበለዚያ እርሱ በእግዚአብሔር እርዳታ መለወጥ አይችልም፡፡ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከየሱስ ጋር በሚኖረን ጥብቅ ግንኙነት እግዚአብሔር በፍቅሩ አትረፍርፎ ሊባርከን ይፈልጋል፡፡ በውጤቱም፣ ታላቅ ኪሳራን ማስወገድና ከቁጥር በላይ የሆነ በረከት ልንለማመድ እንችላለን፡፡ አስደናቂው ነገር ደግሞ፣ ሁኔታችንን በእግዚአብሔር እርዳታ በፍጥነት መፍትሔ ልናገኝለት መቻላችን ነው፡፡ (ዝርዝሩን በምዕ. 3 እና 5 ላይ ይመልከቱ)

የሥጋዊ ክርስትና ችግር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያዩ አይነት አገላለፆች ቀርቧል፡፡ እያንዳንዱ ጎራ እና በጎራዎቹ ውስጥ ያሉት ሰዎች የተለያዩ የትኩረት ነጥቦች ሊኖራቸው ይችላል፣ ነገር ግን ዋናውና መሰረታዊው ችግር ተመሳሳይ ነው፡፡ ስለ ሥጋዊ ክርስትና የተለያዩ ገለጻዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

➢ **"ሥጋዊ"**፡- እናንተ ግን፣ **የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችሁ የሚኖር ከሆነ**፣ በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ ናችሁ። ማንም የክርስቶስ መንፈስ ከሌለው፣ እርሱ የክርስቶስ አይደለም። ሮሜ 8፡9፡፡ በተጨማሪም ሮሜ 8:1-17፤ 1ኛ ቆሮንጦስ 3:1-4, ገላ. 5:16-21 አንብቡ፡፡

➢ **"ሰነፎች"**- የአስርቱ ቆነጃጅት ምሳሌ ማቴዎስ 25፡1-13፡፡ "በሰነፎቹ ቆነጃጅት ሴቶች የተመሰለው የቤተ-ክርስቲያን ሁኔታ፣ የላውዶቂያ ሁኔታ እንደሆነም ተነግሯል" (E.G. White, Review and Herald, Aug. 19, 1890)

➢ **"ለብ ያለ"**፡- ለላውዶቂያ የተጻፈ ደብዳቤ ራዕይ 3፡14-21

"በራድ ወይስ ትኩስ ብትሆን መልካም በሆነ ነበር፡፡" (ራዕይ 3፡15) ይህ አይገርምምን? የሱስ

ለብ ካለ ይልቅ በራድን ይመርጣል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ምንድነው? "ከአምላክ የለሾች ይልቅ በግማሽ ልብ የሚንቀሳቀሱ ክርስቲያኖች የባሱ ናቸው፤ ምክንያቱም አሳሳች ቃላቶቻቸውና አቋም አልባ መሆናቸው ብዙዎች ከትክክለኛው መንገድ እንዲስቱ ያደርጋል፡፡ አምላክ የለሹ ትክክለኛውን መልኩን ያሳያል፡፡ ለብ ያለ ክርስቲያን ግን ሁለቱንም ቡድን ያታልላል፡፡ እርሱ ጥሩ ዓለማዊ ወይም ጥሩ ክርስቲያን አይደለም፡፡ ሰይጣን ማንም ሊሰራለት የማይችለውን ተግባር ይሰራ ዘንድ በእርሱ (ለብ ባለ ክርስቲያን) ይጠቀምበታል፡፡" (E.G. White, Letter 44, 1903, quoted in the Seventh Day Adventist Bible Commentary, Vol.7, p. 963 on Rev. 3: 15.16)

➢ ***"እንደገና ያልተወለደ"*** *ወይም ዳግም ከተወለደ በኋላ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ያልቆየ፡-* ዮሐንስ 3፡1-21

"በዚህ ዘመን እንደገና መወለድ እምብዛምም የማይታይ ልምምድ ነው፡፡ ለዚህ ነው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እጅግ ብዙ ችግሮች ያሉት፡፡ የክርስቶስን ሥም ከያዙት እጅግ ብዙዎቹ ያልተቀደሱ (ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ያልተሰጡ) ናቸው፡፡ ተጠምቀዋል ሆኖም ግን በሕይወት እንዳሉ የተቀበሩ ናቸው፡፡ እኔነት አልሞተም፣ ስለዚህ በክርስቶስ ውስጥ ሆነው ለአዲስ ሕይወት አልተነሱም፡፡" (E.G. White, MS 148, 1897, quoted in the *Seventh Day Adventist Bible Commentary* Vol.6, p. 1075 Many buried alive)

➢ **የአምልኮ መልክ፡-** "የአምልኮ መልክ አላቸው ኃይሉን [መንፈስ ቅዱስን] ግን ክደዋል" 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡5፡፡ ይህንን በተመለከተ አርተር ጂ. ዳንኤልስ "ክርስቶስ ጽድቃችን" በተሰኘው መጽሐፍ ላይ የሚከተለውን ጽፏል፡-

"አስመሳይ ክርስትና እጅግ አታላይና አጥፊ ነው፡፡ አስመሳይነት ለዘመናት ቤተ ክርስቲያን ሥጋት ውስጥ የገባችበት ስውር ገደል ነው፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስ፣ ይህ ያለ-እግዚአብሔር ኃይል የሚገለጽ 'የአምልኮ መልክ' ክርስትና (የመንፈስ ቅዱስ ሙላት የማይታይበት) በመጨረሻ ዘመን ከሚታዩ አደጋዎች አንዱ እንደሆነ በማስጠንቀቅ፣ በዚህ ምቹና ራስን የመደለል አመለካከት እንዳንወሰድ ይገስጻናል (2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡5)፡፡" (Arthur G. Daniells, *Christ our Righteousness,* p. 20)

በሌለን ኋይት ጽሁፎች ውስጥም እጅግ አስደንጋጭ የሆኑ መልእክቶች አሉ፡-

### ➢ እጅግ በጣም ጥቂቶች

"በሌሊት ሕልሜ፣ አንድ ጠባቂ መልዓክ ወሳኝ በሆነ ሕንጻ በር ላይ በመቆም ወደ ውስጥ ለመግባት የመጣውን እያንዳንዱን ሰው 'መንፈስ ቅዱስን ተቀብለሃልን?' በማለት ሲጠይቅ ተመለከትኩት፡፡ የመለኪያ ዘንግን በእጁ ይዞ ሲለካ፤ ወደ ሕንጻው ውስጥ ይገቡ ዘንድ የተፈቀደላቸው እጅግ ጥቂቶች ብቻ ነበሩ፡፡" (E.G. White, *Selected Messages,* Vol. 1 (1958), p. 109.2)

### ➢ ከሀያ ሰዎች አንዱም የተዘጋጀ አይደለም

"ስማቸው በቤተ ክርስቲያን መዝገብ ላይ ከተጻፉ ሃያ ሰዎች ውስጥ አንዱም እንኳ ምድራዊ ሕይወቱን ለመተው እንዳልተዘጋጀና ልክ እንደማንኛውም ኃጢአተኛ ከእግዚአብሔር ውጭና ያለ ተስፋ በምድር ላይ መኖርን እንደሚመርጥ ለወገኖቼ ስገልፅ ታላቅ ሃዘን እየተሰማኝ ነው" (E.G. White, *Christian Service* (1925), p. 41.1)

### ➢ ለምን እጅግ እንቅልፋም ሆንን?

"የክርስቶስ ወታደሮች እንቅልፋምና ግድ የለሾች የሆኑት ለምንድነው? ምክንያቱ እነርሱ ከክርስቶስ ጋር ያላቸው ግንኙነት እጅግ ጥቂት ስለሆነ ነው፤ ምክንያቱ የመንፈስ ቅዱስ እጥረት ስላለባቸው ነው፡፡" (E.G. White, The Great Controversy (1911), p. 507.3)

### ➢ ታላቅ አደጋ

"ሕይወት አጭር መሆኗንና እርግጠኛ አለመሆኗን በመናገር ጊዜ መውሰድ አልፈልግም፡፡ ነገር ግን አንድ ታላቅ አደጋ አለ፤ ሰዎች በቂ በሆነ ሁኔታ ያልተረዱት አደጋ፣ ያም ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የልመና ድምጽ ጆሮአችንን ለመስጠት መዘግየት እና በኃጢአት መኖርን መምረጥ ነው" (E.G. White, Selected Messages, Vol. 1 (1958), p. 109.2)፡፡ ለመሆኑ መሰረታዊው ኃጢአት የትኛው ነው? "በእኔ ስለማያምኑ ነው" ይላል ሐዋሪያው ዮሐንስ (ዮሐንስ 16፡9)፡፡ የሱስን በእርግጥም የማመናችንና በእርሱ መተማመናችን ምልክት ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለእርሱ ማስረከባችን ነው፡፡ ይህም ሙሉ በሙሉ ራስን ከመስጠት እና በሁሉም ነገር እርሱን ለመከተል ፈቃደኝነት ከማሳየት ጋር የተያያዘ ነው፡፡

እንደገና ለማስታወስ እፈልጋለሁ፡- ይህ አሁን ለምምኖረው ሕይወት ደስታን የማግኘት ጉዳይ ስለሆነ፣ የዘላለም ሕይወትንም የማግኘት ጉዳይ ስለሆነ፣ እንዲሁም በትዳር፣

በቤተሰብ፣ በሥራ እና በአገልግሎታችን ውስጥ ከሚያስከትልልን አዎንታዊ ተፅዕኖ ጋር ይያያዛል ብዬ ስላመንሁ ይህንን አንቀፅ ጨምሬአለሁ፡፡

## እጅግ አያሌ ጥያቄዎች

ወሳኙ ጥያቄ <በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተሃል ወይስ አልተሞላህም?> የሚለው ነው፡፡ ነገር ግን አንድ ሰው መቼ ነው በመንፈስ ቅዱስ የሚሞላው? ቅድሚያ መሟላት ያሉባቸው መስፈርቶች ምን ምንድናቸው? ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የሚመራ ሕይወት ምን አይነት አዎንታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል? በትክክለኛው መንገድ ሳይሆን በተሳሳተ አስተሳሰብህ በመንፈስ ቅዱስ እንደተሞላህ አድርገህ ስለራስህ ብታስብ እንዴት ይሆን?

## እነዚህን ምክሮች ስለ ሰጠን አመስጋኞች እንሁን

በመነቃቃትና በተሃድሶ ርዕሶች ዙሪያ ላይ ጊዜያችንን እያሳለፍን በመሆናችን ጌታን እናመስግን፡፡ ታላቁና አስደናቂው አምላካችን ዛሬውኑ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ወደመነቃቃት እንድንነሳሳ የሚያደርግበት ወሳኝ ምክንያቶች እንዳሉት አስባለሁ፡፡ ምክንያቶቹ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ይሆኑ?

- የጎደለንን ሊሞላልንና ካለንበት የሎዶቂያነት ሕይወት ሊያላቅቀን ይፈልጋል፡፡
- ለክርስቶስ ዳግም ምፅአት እና ከዚያ በፊት ላለው የተለየ ጊዜ እንድንዘጋጅ ይፈልጋል
- የመጨረሻው ታላቁ መነቃቃት በዓለማችን እንዲመጣ ይፈልጋል፡፡ (ራዕይ 18÷1-2) ይህም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በሚጠብቁ እና የክርስቶስ ምስክር ባላቸው ... እንዲሁም በክርስቶስ እምነት ባላቸው አማካኝነት ይሆናል (ራዕ. 12÷17) (ራዕ. 12÷17)

ማንኛውም ሥጋዊ ክርስቲያን መንፈሳዊ ክርስቲያን የመሆን እድል ስላለውና በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የሚኖር ሁሉ ወደ ክርስቶስ ሙላት ማደግ እንዲችል ስለሚያደርግ እግዚአብሔርን እናመስግነው፡፡ ይህንን ምዕራፍ ከመደምደሜ በፊት፣ አንድ ሰው የጻፈልኝን ምስክርነት ላካፍላችሁ፡-

## አዲስ መነሳሳት እና ውስጣዊ ሀሴት

"እንዲት እህት "ወደ የግል መንፈሳዊ መነቃቃት የሚመራ መንገድ" የሚለውን መጽሐፍ ሰጠችኝ፡፡ በመጽሐፉ ይዘት በጣም ተገርምኩ፡፡ ለረዥም ጊዜ እንደዚህ አይነት መጽሐፍ ስፈልግ ነበር፤ እናም በስተመጨረሻ አገኘሁት፡፡ ከዚያም መንፈሳዊ ሕይወቴን ማደራጀት ስጀምር ያኔ አንድ ነገር ማድረግ እንዳለብኝ አስተዋልኩ፡- እራሴን ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ አሳልፌ ሰጠሁ! ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ፈጣሪዬ በጠዋቱ ከእንቅልፌ ያነቃኝና ለብቻዬ ከርሱ ጋር ለመገናኘት ጊዜ ይሰጠኛል፡፡ ከዚያም በመቀጠል በየቀኑ አንድ ምዕራፍ <40 ቀን > ከሚለው መጽሐፍ ማጥናት ጀመርኩኝ፡፡ ከክርስቶስ ጋር ያለኝ ግንኙነት በየጊዜው እያደገ እንደሄደ ተረዳሁ፡፡ መንፈስ ቅዱስ በእኔ ላይ እየሰራ እንደሆነ አስተዋልኩ፡፡ ከ <40 ቀን የጸሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ ለክርስቶስ ዳግም ምጻት ለመዘጋጀት - ቁ. 1> መጽሐፍ በኋላ ሁለተኛውን <40 ቀን > መጽሐፍ አጠናሁ፡፡ ከዚያም እነዚህን መጽሐፍት ለ4 ዙር ደጋግሜ አጠናኋቸው፡፡ ከዚያም በየቀኑ ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ሕብረት እንዲኖረኝ ብቻ መጸለይ ሆነ ፍላጎቴ፡፡ ውጤቱም በጣም የሚገርም ነበር፡፡ ምክንያቱም ይህ አዲስ መነሳሳቴና በውስጤ የሚሰማኝ ሃሴት በውጪ የሚታይ ሆኖ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ልዩ ልምምድን የማድረግ ብዙ እድልን አገኘሁ፡፡ ምስክርነቴን ለሌሎች ለማካፈል አጋጣሚዎችን ለማግኘት ፍላጎቴ ጨመረ፡፡ ከክርስቶስ ጋር የቀረበ ግንኙነት ሲኖረን ብዙ ነገሮች አላስፈላጊ መሆናቸውን እንረዳለን፤ ከንቱ ጭንቀቶችም መፍትሔ ያገኛሉ፤ ይህንን፣ እኔ ለማግኘት የታደልኩትን ልምምድ ሌሎች ብዙዎች እንዲያገኙት ምኞቴና ፀሎቴ ነው፡፡" H.S.

ምዕራፍ 3

# ችግሮቻችን መፍትሔ አላቸው

## እንዴት ደስተኛና ጠንካራ ክርስቲያን ወደ መሆን እናድጋለን? መንፈስ ቅዱስ ሕይወታችንን የሚሞላው እንዴት ነው?

በ የወይን ግንድና ቅርንጫፎቹ ምሳሌ የሱስ እንዲህ ተናግሯል፡-
<በእኔ ኑሩ፣ እኔም በእናንተ እኖራለሁ> ዮሐ. 15፡4፡፡ ይህ ምን ማለት ነው?
<ይህ ማለት ፡- በአንድ በኩል ያለማቋረጥ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ራስን ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ አገልግሎት ያስረከበ ሕይወትን መኖር ማለት ነው>፡፡ E.G. White, *Das Leben Jesu* (Hamburg, 1973), S. 675 / *The Desire of Ages*, S. 675

መሠረታዊ ለሆነው ችግራችን መፍትሔ የሆነው ይህ ባለ ሁለት ክፍል መለኮታዊ መፍትሔ፣ ደስተኛ የክርስትና ሕይወት የማግኛ መንገድም ነው፡፡ እንዴት? ምላሹን የሱስ በሚከተለው በዚህ ጥቅስ ላይ ሰጥቷል፡፡ “ደስታዬም በእናንተ እንዲሆን ደስታችሁም እንዲፈጸም ይህን ነግሬአችኋለሁ” (ዮሐንስ 15፡11)፡፡ በነዚህ በሁለቱ ደረጃዎች (ያለማቋረጥ መንፈስ ቅዱስን በመቀበል እና ራስን ሙሉ ለሙሉ አሳልፎ በመስጠት) ክርስቶስ በእኛ ውስጥ ሲኖር፣ ይህ ነው ለእውነተኛ ደስታ ትክክለኛው መንገድ፡፡ ቆላስያስ 1፡17 ስለ “የክብሩ ባለጠግነት” ይናገራል፡- ማለትም “የሱስ በእናንተ ውስጥ”፡፡ የሱስ ይህንን የወይን ግንድ ምሳሌ በዮሐንስ 14 ላይ ቃል ስለገባው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለማስረዳት፣ እንዲሁም በዮሐንስ 16 ላይ ደግሞ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ ለማስረዳት መጠቀሙ አይገርምምን?

ዋናው ነጥብ፡- በየቀኑ ራሳችንን፣ እኛ ያለንን ሁሉ እና የሆንነውን ሁሉ ለጌታ አሳልፈን መስጠታችን ነው፡፡ እንዲሁም በየቀኑ በእምነት ደግመን ደጋግመን በመንፈስ ቅዱስ እንድንሞላ መፀለይና መንፈስ ቅዱስን መቀበል ነው፡፡

## በየቀኑ ለጌታ ራሳችንን አሳልፈን መስጠቱ ለምን አስፈለገ?

የሱስ በሉቃስ 9:23 እንዲህ አለ፡- "በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፣ ራሱን ይካድ መስቀሉንም **ዕለት ዕለት** ተሸክሞ ይከተለኝ"

ደቀ-መዝሙርነት የየዕለት ተግባር እንደሆነ የሱስ ተናግሯል፡፡ ራስን መካድ ማለት፣ የሱስ የሕይወታችን መሪ እንዲሆን መፍቀድ ማለት ነው፡፡ መስቀሉን መሸከም ማለት በየቀኑ ፈተና እና ችግር ይደርስብናል ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን በየቀኑ መስቀሉን መሸከም ማለት፣ ትምክህታችንን ወይም < እኔ > ን በደስታና በፈቃደኝነት በሁሉም ሁኔታ ለየሱስ ማስረከብ ማለት ነው፡፡ ልክ ጳውሎስ ስለ ራሱ "በየቀኑ እሞታለሁ" ብሎ እንደተናገረው፡፡ ክርስቶስ በምድር በኖረበት ዘመን አንድ ሰው መስቀልን ተሸክሞ ከሄደ ለሞት ተላልፎ የተሰጠ እናም ወደ ሚሰቀልበት ቦታም እየሄደ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ስለዚህ ይህ ጥቅስ የሚያሳየን፣ ለክርስቶስ ያለን መሰጠት በየቀኑ መታደስ እንዳለበትና የሱስን በመከተል ሊመጡ የሚችሉትን ተግዳሮቶች መጋፈጥ እንዳለብን ነው፡፡

ዋናውን ነጥብ ልድገምላችሁ፡- ስንወለድ ሥጋዊ ሕይወትን አግኝተናል፡፡ በሕይወት ለመኖር፣ ኃይል ለማግኘትና ጤነኛ ለመሆን በየቀኑ ምግብ እንመገባለን፡፡ በክርስቶስ ዳግም ስንወለድ ደግሞ መንፈሳዊ ሕይወትን አግኝተናል፡፡ መንፈሳዊ ሕይወታችንን ለማቆየት፣ መንፈሳዊ ሕይወታችን ብርቱና ጤነኛ እንዲሆን በየዕለቱ ለውስጣዊ ማንነታችን እንክብካቤ ማድረግ አለብን፡፡ ስለዚህ ለሥጋዊ ሕይወታችንም ሆነ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ጥንቃቄ የማናደርግ ከሆነ እንደክማለን፣ እንታመማለን፣ ጭራሽ ልንሞትም እንችላለን፡፡ በአንድ ቀን ውስጥ ለብዙ ቀን የሚያቆይ ምግብ መብላት አንችልም፤ ለብዙ ቀንም የሚቆይ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት የለም፡፡

<The Acts of the Apostles> በሚለው መጽሐፍ ውስጥ ትልቅ ዋጋ ያለው ምክር አለ፡፡ እርሱም እንዲህ ይላል፡- "በተፈጥሮአዊ ሕይወት ውስጥ የሚሆነው ሁሉ በመንፈሳዊ

ሕይወትም ውስጥ ይሆናል፡፡ ተፈጥሮአዊው ሕይወት ዕለት ዕለት፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚጠበቀው (የሚኖረው) በመለኮታዊ ኃይል አማካኝነት ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ተፈጥሮአዊ ሕይወት በማያቋርጥ ሁኔታ ተጠብቆ ያለው ድንገት በሚከሰት ድንቅ ተዓምር ሳይሆን፣ በአካባቢያችን ያሉትንና በቅርበት የምናገኛቸውን በረከቶች ጥቅም ላይ በማዋል ነው፡፡ መንፈሣዊ ሕይወትም እንዲሁ በማያቋርጥ ሁኔታ በመኖር የሚቀጥለው፣ መለኮት የሚለግሳቸውን መንገዶች (ምክሮች) በተግባር በማዋል ነው፡፡" (E.G. White, The Acts of the Apostles, (1911), p. 284.2)

<የዘመናት ምኞት> በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ የሚለው አስተያየት በጣም አስደንቆኛል፡- "እኛ የሱስን በየዕለቱ ልንከተለው ያስፈልጋል፡፡ እግዚአብሔር ለነገ የሚሆን ዕርዳታ ዛሬ አይሰጠንም፡፡" (E.G. White, The Desire of Ages (1898), p. 313.4)

ኤለን ኋይት ስትናገር፡-

"የሱስን መከተል በሙሉ ልብ ራስን ማስረከብን ይጠይቃል፡፡ ይህም ራስን መስጠት **በየቀኑ** መታደስ አለበት፡፡" (Editor Francis D. Nichol, *Adventist Bible Commentary Vol. 1* (Review and Herald, 1976), p. 1113) " ጌታን የግል አዳኛችን አድርገን በተለወጥን ጊዜ የቱንም ያህል ራሳችንን ከሙሉ ልባችን ቀድሰን የሰጠን ቢሆንም፣ ይህንን በየዕለቱ የምናድሰው ካልሆነ ምንም አይረባንም"(E.G. White, Review and Herald, Jan. 6, 1885)፡፡ "በየጠዋቱ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር ቀድሳችሁ ስጡ፣ ጸሎታችሁ መሆን ያለበት፣ <አ አምላኬ ሆይ፣ ውሰደኝ ሙሉ በሙሉ ያንተ አድርገኝ፡፡ በአንተ በሁሉን ቻይ አምላክ እግር ሥር ሁሉንም እቅዴን አስቀምጣለሁ፡፡ ለአንተም ሥራ ተጠቀምብኝ፡፡ በእኔ ውስጥ ሁን፣ የማደርገው ማንኛውም ነገር ሁሉ አንተ በእኔ ውስጥ ሆነህ የማደርገው ይሁን>፡፡ ይህንን ፀሎት በየቀኑ ፀልዩ፡፡ በየጧቱ ራሳችሁን ለክርስቶስ ቀድሳችሁ ለዚያ ቀን አስረክቡ፡፡ ከዚያም ዕቅዳችሁን አምላክ በመራው መሠረት አከናውኑ ወይም ደግሞ ፈቃዱ ካልሆነ ተቀበሉት፡፡ በዚህ መልኩ ቀን በቀን ሕይወታችሁን ለእግዚአብሔር እጅ አሳልፋችሁ ስትሰጡ፣ ሕይወታችሁ በክርስቶስ ሕይወት እየተቀረጸ እንዲሄድ ታደርጋላችሁ" (E.G. White, Steps to Christ (1892), p. 70.1)

ሞሪስ ቬንደን እንዲህ ይላል፡-

"በየዕለቱ ራስን የማስረከብ ጥቅምን እስከዛሬ ድረስ አስተውለህ ካልነበረ፣ ዛሬ ይህንን ማወቅህ በሕይወትህ ትልቅ ለውጥን ያመጣልሃል፡፡ <Thoughts From The Mount of Blessing> የተሰኘው መጽሐፍ ላይ ኤለን ኋይት እንዲህ በማለት ታረጋግጥልናለች፡- "ከክርስቶስ ጋር ሕብረት እንዲኖርህ የምትፈልግ ከሆነ፣ በየቀኑ ራስህን የምታስረክብ ከሆነ፣ የምታጉረመርምባቸው ነገሮች ሁሉ ፀጥ ይላሉ፤ የከበዱህ ነገሮች በሙሉ ይወገዳሉ፤ ሁሉም ግራ ያጋቡህና የተገዳደሩህ ችግሮችህ አሁን መፍትሔ አግኝተው ታያለህ"፡፡ (Morris Venden, *95 Theses on Righteousness by Faith* (Pacific Press, 1987), p. 96)

በየዕለት-መታደስ ራሳችንን አሳልፈን በመስጠት ከክርስቶስ ጋር መጣበቅ፣ ልክ መጀመሪያ ጌታን የግል አዳኛችን አድርገን ስንቀበል እንደነበረው በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

ሞሪስ ቬንደን በመቀጠል እንዲህ ይላል፡- "ከክርስቶስ ጋር ያለን የዕለት ተዕለት ግንኙነት ራሳችንን ያለማቋረጥ አሳልፈን እንድንሰጥና በእያንዳንዱ ደቂቃ በእርሱ ላይ እንድንተማመን ያደርገናል፡፡" (Morris Venden, 95 *Theses on Righteousness by Faith* (Pacific Press, 1987), p. 233)

በማስተዋል በየጠዋቱ ሕይወታችንን ለክርስቶስ አሳልፈን ስንሰጥ፣ እያደረግነው ያለው የእርሱን ምኞት እንደሆነ እርግጠኛ መሆን እንችላለን፣ ምክንያቱም ክርስቶስ ሲናገር "ወደ እኔ ኑ…" ብሏል (ማቴ 11፡28) እንዲሁም ይህንን ብሏል፡- "ወደ እኔ የሚመጣውንም ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም" (ዮሐንስ 6፡37)

"አምላካችን ለእኛ ታላላቅ ነገሮችን ለማድረግ ዝግጁ ነው፡፡ እንዴት? ነፍሳችንን ሙሉ በሙሉ ለየሱስ በሙሉ አሳልፎ በመስጠት እንጂ በቁጥር በመብለጥ ድል አናገኝም፡፡ በእስራኤል አምላክ በመታመንና በእርሱ ብርታት ወደፊት ልንገሰግስ ይገባናል" (E.G. White, *Sons and Daughters of God,* p. 279) "በመንፈሴ እንጂ፣ በኃይልና በብርታት አይደለም" (ዘካርያስ 4፡6)

ሙሉ በሙሉ ራሳችንን ለእርሱ አሳልፈን ስንሰጥ ጌታ በእኛ ላይ ሊያደርግ ስለሚችለው ታላቅ ተፅዕኖ ጆን ዌስሊ እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፡- "ራሳቸውን ለእግዚአብሔር 99% አሳልፈው ከሰጡ ሠራዊት ይልቅ ራሱን 100% አሳልፎ በሰጠ አንድ ሰው እግዚአብሔር ታላቅ ነገር ማድረግ ይችላል፡፡" (Dr. S. Joseph Kidder, Anleitung zum geistlichen Leben (Andrews University), PPP slide 14)

ኤለን ኋይት ስትፅፍ፡-

"ከክርስቶስ ጋር ተባባሪ ሠራተኛ የሚሆኑት ብቻ፣ <አምላኬ ሆይ፣ እኔ እና ያለኝ ነገር ሁሉ ያንተ ነው> የሚሉት ብቻ የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች እንደሆኑ ይቆጠራሉ" (E.G. White, *The Desire of Ages* (1898), p. 523.1) "ነፍሳቸውን፣ ሰውነታቸውን እንዲሁም መንፈሳቸውን ለጌታ ቀድሰው የሰጡ ናቸው አዲስ አካላዊ እና አዕምሮአዊ ኃይልን ያለማቋረጥ የሚቀበሉት... በእንደዚህ አይነት ሰዎች ልብ እና መንፈስ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ በታላቅ ኃይሉ ይሠራል፡፡ የእግዚአብሔር ፀጋ አእምሮአቸውን ያሰፋል፣ ማስተዋላቸውንም ይጨምራል፣ የመለኮት ፍጽምና ደግሞ ከእነርሱ ጋር በመሆን ነፍሳትን በማዳን ሥራ ያግዛቸዋል፣ ምንም እንኳን ሰብአዊ ድክምና ቢኖራቸውም የኃያሉን አምላክ ድንቅ ሥራዎች የመሥራት ብቃት ይኖራቸዋል፡፡" (E.G. White, *The Desire of Ages* (1898), p. 827.3)

ስለ *መቀደስ* ወይም *መሰጠት* ወይም *ሕይወትን ሙሉ በሙሉ ለጌታ አሳልፎ ስለ መስጠት* ይህንን ያህል ካልን ይበቃናል፡፡

## አንድ ክርስቲያን በየዕለቱ በመንፈስ ቅዱስ እንዲጠመቅ መጠየቅ ለምን አስፈለገው?

በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን መጠየቅ ማለት፤ የሱስን <ከኔ ጋር ሁን> ብሎ እንደ መጋበዝ ነው። ምክንያቱም እርሱ [የሱስ] በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በእኔ ውስጥ ስለሚኖር። ግን ለምን በየዕለቱ?

የሱስ ለዚህ ምሳሌአችን ነው፡፡ ኤለን ጂ. ዋይት <አክትስ ኦፍ ዘ አፖስትልስ> በተሰኘው መጽሐፍ እንዲህ ብላለች፡- ራሱን ሙሉ በሙሉ ለለጌታ ለሰጠ ክርስቲያን አገልጋይ አንድ አስደናቂ የሚያጽናና ምሳሌ አለለት፡፡ ክርስቶስ በምድር በኖረባቸው ዘመናት **የሚያስፈልገውን ትኩስ ጸጋ ለማግኘት ዕለት በዕለት የአባቱን ፊት ይሻ ነበር፡፡** የእርሱ ምሳሌ፣ ከልባቸው ያለማቋረጥ ራሳቸውን እና አገልግሎታቸውን በእምነት በጸሎት ለእግዚአብሔር የሚሰጡ ክርስትያኖች ከኃጢአት ጋር በሚያደርጉት ፍልምያ የመንፈስ ቅዱስ እርዳታን እንደሚያገኙ ያረጋግጣል፡፡ (E.G. White, Acts of the Apostles, (1911), p.56.1)

ይህ ለየሱስ በየዕለቱ የሚያስፈልገው ከነበረ፤ ለእኛ ከዚህ በበለጠ እንዴት አስፈላጊ ይሆን!

በ 2ኛ ቆሮንጦስ 4፡16 አንድ ወሳኝ የሆነ ነጥብ አለ፡-

"..... የውስጥ ሰውነታችን ***ዕለት ዕለት ይታደሳል*** "

የውስጥ ሰውነታችን ዕለት ዕለት እንክብካቤ ይፈልጋል፡፡ ይህ የዕለት ተዕለት መታደስ በምን መልኩ ነው የሚካሄደው? በ ኤፌሶን 3፡16-17፣19 እንደተጻፈው ይህ የሚሆነው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው፡- ***"በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ*** *ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለጠግነት መጠን ይስጣችሁ፤ የእናንተ ስር እና መሰረት በፍቅር ይጸና ዘንድ፤ ... እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ"*

ስለዚህ፡-

- በየዕለቱ በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት መጸለይ አስፈላጊ ነው፡፡
- መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ ሲኖር ክርስቶስ በእኛ ውስጥ ይኖራል ማለት ነው፡፡
- እንደ ክብሩ ባለጠግነት መጠን ለውስጥ ማንነታችን ኃይልን ይሰጠናል፡፡ የእግዚአብሔርን ኃይል፣ ማለትም መለኮታዊውን ኃይል ማለት ነው፡፡
- ስለዚህ በዚህ አማካኝነት የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ውስጥ ይሰጠናል፡፡
- እንዲሁም ይህ "በእግዚአብሔር ሙላት" ውስጥ ወደሚኖር ሕይወት የሚመራ መንገድ ነው (ዮሐንስ 10፡10፤ ቆላስያስ 2፡10 ይመልከቱ)

ሌላ እጅግ ጠቃሚ ቃል በ ኤፌሶን 5፡18 ላይ ይገኛል፡- *"...መንፈስ ይሙላባችሁ"*፡፡ ይህ ጥቅስ ምክር ብቻ እንዳልሆነ አስተውሉ!፡፡ ይህ መለኮታዊ ትዕዛዝ ነው! እግዚአብሔር ከመንፈስ ቅዱስ ጋር መኖርን እንድንፈልግ ይጠብቅብናል፡፡ የግሪክ ቋንቋ ሊቆች የሚከተለው አርፍተ ነገር በኤፌሶን 5፡18 ላይ ያለው ጥቅስ ምን ለማለት እንደፈለገ በትክክል ይገልጸዋል ይላሉ፡- "ሁልጊዜ፣ ያለማቋረጥ በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፡፡" (Editor Werner E. Lange, Unser grÖßtes Bedürfnis (Lüneburg, 2011), p. 42)

የሰንበት ትምህርት ጥናታችን እንዲህ ይላል፡- "በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ማለት ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ተጽእኖ ውስጥ መሆን ማለት ነው፣ ሙሉ በሙሉ በእርሱ "መሞላት" ማለት ነው፡፡" ጳውሎስ በኤፌ 5፡18 በግሪክ ግስ "ይሙላባችሁ" ብሎ እንደተናገረው ይህ የአንድ ጊዜ ተሞክሮ አይደለም፤ ነገር ግን ሁልጊዜ ሚደጋግም ነገር ነው፡፡ (Sabbath School Study Guide July 17, 2014)

ሐዋሪያው ጳውሎስ በኤፌሶን 1፡13 ላይ የሚከተለውን ቢጽፍም "...ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታትማችሁ" የሚለውን ምክር ቢሰጣቸውም፣ በድጋሚ በምዕራፍ 5 ላይ ይህንኑ እንደገና

አሳሰባቸው በርግጥ የኤፌሶን ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ነበር፣ ቢሆንም <በመንፈስ መጠንከር> ነበረባቸው፣ እንዲሁም <በመንፈስ መሞላት> ነበረባቸው፣ <ሁልጊዜ ያለማቋረጥ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት> ነበረባቸው፡፡ በኤፌሶን 4፡30 ደግሞ መንፈስ ቅዱስን እንዳያሳዝኑ ያስጠነቅቃቸዋል፡፡

ኤለን ዋይት ስትናገር፡-

"ማንኛውም የጌታ ሠራተኛ **በየዕለቱ** በመንፈስ ቅዱስ ለመጠመቅ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት ማቅረብ አለበት" (E.G. White, The Acts of the Apostles (1911), p. 50.2)

"የክርስቶስ ጽድቅ እንዲኖረንና የመለኮትም ተካፋይ ለመሆን በየዕለቱ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መለወጥ አለብን፡፡ መንፈሳዊ ፍላጎትን መቀስቀስ፣ ልብን መቀደስ፣ ሰውን ሙሉ ማድረግ የመንፈስ ቅዱስ ስራ ነው፡፡" (E.G. White, Selected Messages 1, (1958), p. 374.1)

በሌላ መጽሐፍ ላይ ጌታ በኤለን ኋይት በኩል እንዲህ ይላል፡- "የእግዚአብሔር ቃል በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ሕይወታቸው የተቀየረ እና አስተምህሮዉን ለመከተል የሚሹ ሃቀኛ አማኞች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት አማካኝነት የሚሰጠውን አዲስ መንፈሳዊ ኃይል **በየዕለቱ** ቃሉን በማጥናትና **በየዕለቱ መንፈሳዊ ጥማትን** በማሳየት ሊበቀሉ ይገባቸዋል፡፡" (E.G. White, The signs of the Times March 8, 1910, par, 1)

በተጨማሪም ስትናገር፡ "እኛ ክርስቶስን ዕለት ተዕለት መከተል አለብን፡፡ እግዚአብሔር ለነገ የሚያስፈልገንን እርዳታ አስቀድሞ አይሰጠንም፡፡" (E.G. White, The desire of Ages (1898), p. 313. 4)

በሌላ ቦታ ደግሞ፣ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ለማደግ "ከመለኮታዊ ኃይል ጋር የማያቋርጥ ግንኙነት ማድረግ አለብን፡፡ ከዚህ በፊት የእግዚአብሔርን መንፈስ በመጠኑ አግኝተን ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን በጸሎትና በዕምነት ከዚህ በበለጠ **መንፈስ ቅዱስን ያለማቋረጥ መሻት ይኖርብናል**፡፡" (E.G. White, The Review and Herald, March 2, 1897, par. 5)

ሌላም አስገራሚ ጽሁፍ አነበብኩ፡- "በሐዋሪያት ዘመን የየሱስ ደቀመዛሙርት አንድ ልብ እና አንድ አሳብ አድርጓቸው የነበረው **የፍቅር ጥምቀት እኛም በየዕለቱ ያስፈልገናል**፡፡" (E.G. White, Testimonies to the Church (1904), vol. 8, p. 191)

ሮሜ 5፡5 በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን እንደፈሰሰ ይነግረናል፡፡ ተመሳሳይ ነገር በኤፌ. 3፡17 ላይ እናገኛለን፡- በየዕለቱ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ (በመንፈስ ቅዱስ መሞላት)፣ በየዕለቱ የፍቅር ጥምቀትን መጠመቅን ያስከትላል (በእግዚአብሔር አጋፔ ፍቅር መሞላትን)፡፡ በተጨማሪም በገላ 5፡16 እና በሮሜ 8፡2 ላይ፣ የኃጢአት ኃይል በዚህ ምክንያት እንደሚሰበር በግልፅ ይናገራል፡፡

## የግል አምልኮ አስፈላጊነት

ራሴን በየዕለቱ ለየሱስ ማስረከብ እና በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላኝ መጠየቅ በጣም አስፈላጊ ከሆነ የግል አምልኮ ያለው ሚና ምንድን ነው?

መንፈሳዊ ሕይወታችን ዕለት ተዕለት መታደስ እንደሚገባው የሚያሳዩ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችንና ሌሎች የተለያዩ ጥቅሶችን ከላይ ዘርዝሬአለሁ፡፡ እነርሱም ስለ የየዕለት የግል አምልኮ አስፈላጊነት በጉልህ ብርሃን ያሳዩናል፡፡

በማለዳና በማታ ይቀርብ የነበረው የሚቃጠል መስዋዕት፣ የጥንቱ የቤተ-መቅደስ አምልኮ አገልግሎት ዋና መሠረት ነበር፡፡ በሰንበት ቀን ደግሞ ሌላ ተጨማሪ የሚቃጠል መስዋዕት ይቀርብ ነበር (ዘኁልቁ 28፡4፤10)፡፡ የሚቃጠለው መስዋዕት የነበረው ትርጉም ምንድን ነበር?

"የሚቃጠለው መስዋዕት ኃጢአተኛው ሙሉ በሙሉ ራሱን ለጌታ እንደሰጠ ያመላክት ነበር፡፡ ሁሉም ነገር የጌታ ስለሆነ፣ እዚህ ጋር ግለሰቡ ለራሱ ምንም ነገር አያስቀርም ነበር" (Fritz Rienecker, *Lexikon zur Bibel* (Wuppertal, 1964), p. 1017)

"በማለዳ እና በማታ የሚቃጠል መስዋዕት የሚቀርብባቸው ሰዓታት የተቀደሱ ሰዓታት እንደሆኑ ይቆጠሩ ነበር፡፡ መስዋዕቱም በመላው የአይሁድ ሕዝብ በእነዚህ ለፀሎት በተወሰኑ ሰዓታት ይቀርቡ ነበር፡፡ ይህ ልምድ ለክርስቲያኖች የጠዋትና የማታ ጸሎት ማድረግ አስፈላጊነት ምሳሌ ነው፡፡ በርግጥ እግዚአብሔር የአምልኮ መንፈስ የሌለውን ከንቱ ሥርዓትን ይኮንናል፣ ነገር ግን እርሱን ከልባቸው የሚወዱትና ለሠሩት ኃጢአት ሥርየት ለማግኘትና በረከትን ለማግኘት ጠዋትና ማታ ለሚንበረከኩት ተማፅናቸውን ለመመለስ በደስታ ይመለከታቸዋል፡፡" (E.G. White, *Patriarchs and Prophets* (1890) p. 353.3)

የየዕለት አምልኮ (ሰንበትን ጨምሮ)፣ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን መሠረት እንደሆነ እያስተዋልን ነውን? ይህም፣ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በእኛ ውስጥ እንዲኖር ለተጋበዘው ለየሱስ በየዕለት ራስን ከማስረከብ ጋር ስላለው ተያያዥነት እንደሚጠቁም ግልጽ ሆኖልናልን?

ከመንፈሳዊ መመሪያዎች ሁሉ ዋነኛው በየዕለቱ ለእግዚአብሔር ቅድሚያ መስጠት ነው፡፡ የሱስ በተራራው ስብከት እንዲህ አለ፡- "ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ፅድቁንም ፈልጉ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል" ማቴዎስ 6፤33

የእግዚአብሔር መንግሥት ማለት፣ ክርስቶስን አሁኑኑ በልባችን ውስጥ ማኖር ማለት ነው። ስለዚህ ነው መንፈስ ቅዱስ ዕለት ዕለት ራሳችንን እንዲገዛንና በአምልኮ ጊዜያችን መንፈስ ቅዱስ እንዲገኝ የምንፀልየው። በጌታ ፊት በምንቀርብበት ጊዜ ወሳኙ ጥያቄ የሚሆነው፡-

የሚያድን የግል ግንኙነት ያለማቋረጥ ከክርስቶስ ጋር ነበረንን? በክርስቶስ ሆነን ፀናን? (ዮሐንስ 15፣1-17 ተመልከቱ)፡፡ አንቤቢ ሆይ፡- አንተስ እምነትህ በታላቅ በረከት የተሞላ እንዲሆን አትናፍቅምን?

ከጌታ ጋር ጥቂት ጊዜ የሚያሳልፉ ወይም ደግሞ ምንም ጊዜ የማያሳልፉ ወይም ደግሞ በቂ ያልሆነ የአምልኮ ጊዜ ያላቸው ምናልባት በሳምንት አንድ ጊዜ በሚደረገው የሰንበት የአምልኮ ፕሮግራም ብቻ ነው የሚታነፁት። ይህ በሳምንት አንዴ ከሚመገብ ሰው ጋር ይመሳሰላል፡፡ በሳምንት አንዴ መመገብ በጭራሽ የማይሆን ነገር አይደለምን? ይህ ማለት፣ አንድ ክርስቲያን ያለ የግል አምልኮ ሲኖር ሥጋዊ ነው ማለት አይደለምን?

ስለዚህ ይህ ክርስቲያን ያለማቋረጥ በዚህ ሁኔታ (በሥጋዊነት) ከቆየ አልዳነም ማለት ነው፡፡ ሥጋዊ ክርስቲያኖች ከሆንን የግል አምልኮ ጊዜ እንደ ግዴታ ሆኖ ነው የሚታየን፡፡ መንፈሳዊ ክርስቲያን ከሆንን ግን የግል አምልኮ ጊዜ ፍላጎታችን ወይም የምንመኘው ይሆናል፡፡

## *"የክርስቶስ ጽድቅ እንዲኖረንና የመለኮት ባህርይ ተካፋዮች እንድንሆን በየዕለቱ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መለወጥ አለብን"*

ከዓመታት በፊት "ወሮበላ ነበርኩ" የሚለውን በጂም ቫውስ የተጻፈውን መጽሐፍ አንብቤ ነበር፡፡ ይህ ሰው ወንጀለኛ የነበረ፣ ነገር ግን በጌታ የሱስ አዲስ ሕይወት ያገኘ ሰው ነበር፡፡ የሠራቸውን ኃጢአቶች በፍፁም ልቡ ተናዘዘ፡፡ ለምሳሌ፡- በሀሰት መመስከር፣ ስርቆት፣ ወዘተ። እሱ እጅግ ብዙ ጊዜ የመለኮትን ጣልቃ ገብነትን በሕይወቱ ተለማምዷል፡፡ ይህ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ልምምድ እኔን አስደነቀኝ። ለራሴም እንዲህ አልኩት፡- <የተሟላ ሕይወት እየመራህ ነው ያለው፣ በሁሉ ነገር ጥሩ ሁኔታ ላይ ነው ያለኸው፣ ነገር ግን የዚህ ሰውዬ ዓይነት ልምምድ የለህም>። ከዚያም ወደ ጌታ መጣሁና እንዲህ ብዬ ፀለይኩኝ፡- <በሰማይ ያለህ አባት ሆይ፡- እኔ እስከዛሬ የተገለጠልኝንና አንተ ገና የምታስታውቀኝን ኃጢአቴን መናዘዝ እፈልጋለሁ፣ እንዲሁም ለፀሎት እና መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ ከዚህ ቀደም ከምነሳበት ሰዓት አንድ ሰዓት ቀደም ብዬ እነሳለሁ፡፡ ከዚያም በሕይወቴ ጣልቃ ትገባ እንደሆነ አያለሁ።>

እግዚአብሔር ይመስገን። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር በሕይወቴ ጣልቃ ገባ። ከዚያን ጊዜ ወዲህ በተለይ የማለዳ የግል አምልኮ ጊዜዬ፣ ከሰንበት አምልኮ ጋር ተደምሮ ከጌታ ጋር ላለኝ ሕይወት መሠረት ሆነኝ፡፡

> በየዕለቱ ራስን ለጌታ በማስረከብ እና በየዕለቱ በመንፈስ ቅዱስ በመሞላት ሕይወታችን በአዎንታዊ መንገድ ይቀይራል፡፡ ይህም የሚሆነው በግል የአምልኮ ጊዜ ነው

## በመንፈስ እና በእውነት ማምለክ (መስገድ)

በምድር ላይ ያለው ዋናው ጉዳይ እግዚአብሔርን ማምለክ በተመለከተ ነው። እግዚአብሔር ለሰብአዊ ዘር በሰጠው የመጨረሻ መልዕክት ውስጥ ያለው የአምልኮ ጉዳይ ፈጣሪን ማምለክ ወይንም አውሬውን ማምለክ በተመለከተ ነው (ራእይ 14፣6-12)፡፡ ፈጣሪ እግዚአብሔርን የማምለክ ውጫዊ ምልክቱ ሰንበትን ማክበር ነው [ዕለተ ቅዳሜን/በዕብራይስጥኛ "ሻባት"]። የአምልኮ ውስጣዊ ምልክት ደግሞ በዮሐንስ 4፡23-24 ላይ እንዲህ ተብሎ ተገልጿል፡- "ነገር ግን **በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስ እና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል** አሁንም ሆኖአል፤ አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻልና። እግዚአብሔር መንፈስ ነው፣ የሚሰገዱለትም በመንፈስ እና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል"

**በመንፈስ** መስገድ (ማምለክ) ማለት በአዕምሮ ሆነን በማስተዋል ማምለክ ማለት ሲሆን፣ በመንፈስ ቅዱስ መሞላትም ማለት ነው፡፡ **በእውነት** ማምለክ ማለት፣ በርግጥም ራሱ እውነት ለሆነው ለየሱስ ራስን ሙሉ በሙሉ ያስረከበ ሕይወት መኖር ማለት ነው፡፡ "እኔ እውነት ነኝ " አለ የሱስ (ዮሐ 14፡6)። እንዲሁም በእውነት ማምለክ ማለት፣ የሱስ በእኔ ውስጥ ስለሚሆን፣ በእግዚአብሔር ቃልና ትእዛዝ መሠረት መኖር ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም የሱስ እንዲህ ብሏል፡ "በእውነትህ ቀድሳቸው፣ ቃልህ እውነት ነው" (ዮሐ. 17፡17)። መዝ 119፡142 ደግሞ፡- "ቃልህም እውነት ነው" ይላል፡፡ ዛሬ እኛ የአምልኮ ሕይወት ከሌለን ወሳኝ በሆነ ሰዓት ላይ ለመውደቅ አደጋ ተጋላጮች እንሆን የለምን? ይህ ሥጋዊ ለሆኑ ክርስቲያኖች ሁሉ ትልቅ ችግር መሆኑ እርግጥ ነው፡፡ በርግጥ ሁላችንም በክርስትና ሕይወታችን በእግዚአብሔር እርዳታ ዕድገት ማሳየት እንፈልጋለን፣ በእግዚአብሔር እርዳታ በዕውቀት ማደግም እንመኛለን፡፡ ምናልባት

ለአንዳንድ ክርስቲያኖች ወደፊት እንዳይራመዱ እንቅፋት የሆነባቸው ከዚህ በታች ባለው ርዕስ ውስጥ የተገለፀው የተሳሳተ አስተሳሰብ ሊሆን ይችላል፡፡

## ጥምቀት እና መንፈስ ቅዱስ

አንዳንድ ሰዎች በውሃ ጥምቀት ስለተጠመቁ በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተሞሉ አድርገው ራሳቸውን ያያሉ፡፡ በመሆኑም፣ ሁሉም ነገር የተስተካከለ እንደሆነ እና ምንም ነገር እንዳልቀረባቸው ያስባሉ፡፡ ዲ. ኤል. ሙዲ እንዲህ ብለው አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡- "ብዙ ክርስተያኖች አንዴ በመንፈስ ቅዱስ ስለተሞሉ ለሁልጊዜ የተሞሉ ይመስላቸዋል፡፡ አ ወዳጆቼ! እኛ እኮ ባለቀዳዳ ዕቃዎች ነን፡፡ ስለዚህ ሁልጊዜ ሙሉ ለመሆን ሳናቋርጥ ከምንጩ ሥር መሆን ያስፈልገናል፡፡" (D. L. Moody, *They Found the Secret,* p. 85, 86; quoted in *"10 Days – Prayers and Devotions …"* by Dennis Smith, p. 23)

ጆሴፍ ኤች ዋጎነር እንዲህ ብሏል፡-

**"የውሃ ጥምቀት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የሚሰጥበት ነው የሚለው አስተሳሰብ፣ ንስሐ የገባውን ኃጢአተኛ ሥጋዊ በሆነ ዋስትና ራሱን እንዲታልል ያደርገዋል፡፡** እርሱ፣ የውሃ ጥምቀት ብቻ የእግዚአብሔር ጸጋ ምልክት እንደሆነ ያምናል። በእርሱ ልብ ውስጥ የሚኖረውን መንፈስ ሳይሆን፣ የውሃ ጥምቀትን ብቻ እንደምልክት ወይም እንደማረጋገጫ ይመለከታል፡፡" (Joseph H. Waggoner, *The Spirit of God* (Battle Creek, Michigan 1 877), p.35f, quoted in Garrie F. Williams, *Erfüllt vom Heiligen Geist* (Lüneburg, 2007), S. 58)

የውሃ ጥምቀት በእርግጥ ትክክለኛና ታላቅ ውሳኔ ነው፡፡ ይህም ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ይስማማል። የውሃ ጥምቀት አስፈላጊነቱ እንደተጠበቀ ይቆያል፡፡ ነገር ግን ያለፈውን ክስተት በመንፈስ ቅዱስ ስለመሞላታችን እንደማረጋገጫ ማየት የለብንም፡፡ በዚህ ፈንታ በመንፈስ ቅዱስ መሞላታችንን **አሁኑኑ** ማወቅና መለማመድ አለብን፡፡

አንዳንድ ሰዎች ከመጠመቃቸው **በፊት** ነው መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉት፡፡ ለምሳሌ ቆርኔሌዎስ እና ቤተሰቡ እንዲሁም ሳውል። ሌሎች ደግሞ ከተጠመቁ **በኋላ** ነው መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉት፡፡ ለምሳሌ ሳምራዊያን እና 12ቱ የኤፌሶን ሰዎች። አንድ ግለሰብ መንፈስ ቅዱስን ከውሃ ጥምቀት በፊት፣ በውሃ ጥምቀት ጊዜ፣ ወይም ደግሞ ከውሃ ጥምቀት በኋላ ቢቀበልም፣ ሁሉም ተመሳሳይ ነው። ዋናው ነገር ግን፣ አንድ ጊዜ የተቀበልነውን መንፈስ

ቅዱስን **አሁኑኑ** በልባችን ውስጥ ማኖራችን ነው፡፡ ቁም ነገሩ ከዚህ በፊት የሆነው ነገር ሳይሆን <ዛሬ እና አሁን የእኔ በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቅ ሁኔታ ምን ይመስላል?> የሚለው ነው፡፡

እንደገና ላስታውሳችሁ እፈልጋለሁ፡- አካላዊ ሕይወታችንን በመወለድ አገኘን፡፡ ይህ ሕይወታችን በየዕለት በምንመገበው ምግብ፣ በምንጠጣው ውሃ፣ በምናደርገው የአካል እንቅስቃሴ፣ መኘታ እና የመሳሰሉት ተጠብቆ ይቆያል፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ በሕይወት አንኖርም ነበር። ለአካላዊ ሕይወታችን የምናውለው ሕግ በተመሳሳይ ሁኔታ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ይሠራል። ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ ባስረከብንበት ቀን (ዳግም በተወለድንበት ቀን) በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት አዲስ ሕይወትን ተቀብለናል። ይህ አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት በቀጣይነት ተጠብቆ እንዲቆይ፣ ጌታ የሰጠንን መንገዶች መከተል አለብን፣ ማለትም፡- በመንፈስ ቅዱስ በመሞላት፣ በጸሎት፣ የጌታን ቃል በማጥናት ወ.ዘ.ተ።

ኤለን ጂ ኋይት እንዲህ ብላለች፡- "አካላዊ ሕይወት በማያቋርጥ ሁኔታ ተጠብቆ ያለው በእግዚአብሔር ኃይል ነው፡፡ ይህም የሚሆነው ድንገት በሚከሰት ተዓምር ሳይሆን እግዚአብሔር በአካባቢያችን ባስቀመጣቸውና በአካባቢያችን በምናገኛቸው ምድራዊ በረከቶች ነው፡፡ መንፈሣዊ ሕይወትም እንዲሁ በማያቋርጥ ሁኔታ ተጠብቆ የሚቀጥለው፣ መለኮት የሚለግሰንን መንገዶች (ምክሮች) በተግባር በማዋል ነው፡፡" (E.G. White, The Acts of the Apostles (1911), p. 284.2)

አካላዊም ሆነ መንፈሳዊ ሕይወት እንዲሁ በራሱ አይኖርም፡፡ ይህ ሕይወት ተጠብቆ እንዲኖር እግዚአብሔር የሰጣቸውን መንገዶች መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡

ይህ ማለት፣ ዳግመኛ በተወለድንበት ቀን መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ እንዲያድር ይሰጠናል፡፡ ነገር ግን ያ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ በቀጣይነት እንዲቆይ ጌታ የሰጠንን መንገዶች ዕለት ዕለት መጠቀም አለብን፡፡ እነዚህን መንገዶች ካልተጠቀምን ምን ዓይነት ውጤት ልንጠብቅ እንችላለን?

ከእነዚህ ሁሉ መንገዶች *በመንፈስ ቅዱስ መሞላት* እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም *ፀሎት* በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ እንዲሁም *ከጌታ ጋር በቃሉ አማካኝነት መገናኘት፣ በአምልኮ አገልግሎቶች መሳተፍ* እና *ማገልገል* እናም ሌሎች ተመሳሳይ መንገዶች እንዲሁ አስፈላጊ ናቸው፡፡

ውስጣዊ እኛነታችንን **ዕለት ዕለት** መንከባከብ እነዳለብን አስፈላጊ መሆኑን እንደምንስማማ አስባለሁ፡፡ ይህንን ካላደረግን የሚፀፅተንን ውጤት እንለማመዳለን፡፡ ለነገ የሚጠቅመንን

ምግብ ዛሬ መብላት አንችልም፣ እንዲሁም ለነገ የሚጠቅመንን መንፈስ ቅዱስ ዛሬ ልንቀበል አንችልም፡፡ “እግዚአብሔር ለነገ የሚያስፈልገንን እርዳታ ዛሬ አይሰጠንም“ (E.G. White, *The Desire of Ages*, (1898), p.313.4)፡፡ በየዕለት ራስን ለክርስቶስ ማስረከብና መንፈስ ቅዱስን በየቀኑ ወደ ሕይወታችን መጋበዝ አለብን፡፡

ሁለቱም ነገሮች አንድ ዓላማ አላቸው (ማለትም ዳግም መወለድና በየቀኑ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት)፡፡ ሁለቱም የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ ናቸው፡፡ ዓላማቸውም ከክርስቶስ ጋር የጠበቀ ወዳጅነት እንዲኖረን ነው፡፡ ዳግም በተወለድኩበት ጊዜ፣ ራሴን ለክርስቶስ አስረክባለሁ፣ በመንፈስ ቅዱስ እንደሞላ በምጠይቅበት ጊዜ ደግሞ የሱስ በልቤ ውስጥ እንዲኖር እጋብዘዋለሁ፡፡ ሐዋሪያው ዮሐንስ በ1ዮሐንስ 3፡24 ላይ፣ የሱስ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በእኛ ውስጥ እንደሚኖር ይነግረናል፡- “እርሱም [የሱስ] … በእኛ እንዲኖር ከሰጠን ከመንፈሱ እናውቃለን::” (እንዲሁም ዮሐንስ 14፡17ና23 አንብቡ)፡፡

## በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ውጤቶች

መንፈስ ቅዱስ በእኔ ውስጥ ሲሆን፣ ክርስቶስ በምድር ሳለ የሠራውን አይነት ሥራ በእኔም ውስጥ ሆኖ ይሠራል፡፡ ሮሜ 8፡2 እንዲህ ይላል፡- “በክርስቶስ የሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና”፡፡ “የመንፈስ ሕግ” የሚለው አባባል “ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር በተሰጠ ልብ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የሚሠራበት መንገድ” በማለት መግለፅ እንችላለን፡፡ ክርስቶስ በምድር ሳለ የሠራው ሥራ፣ በእኔ ሕይወት ውስጥም እንዲፈፀም (እንዲታይ) ማድረግ የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው፡፡ ኤለን ጂ ኋይት ይህንን እንዲህ በማለት ትገልፀዋለች፡- “መንፈስ ቅዱስ የተሰጠን ደግሞ ደጋግሞ እንዲያድሰን ነው፡፡ ይህ የሚያድሰን መንፈስ ቅዱስ ባይኖር ኖሮ ክርስቶስ የከፈለው መስዋዕትነት ከንቱ ይሆን ነበር፡፡ መድኃኒዓለም ያደረጋቸው ነገሮች ሁሉ በእኛ ሕይወት ውስጥ ተግባራዊ የሚሆኑት በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ልባችንን ያፀዳል፡፡ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ማንኛውም አማኝ የመለኮት ባሕርይ ተካፋይ ይሆናል፡፡ መንፈስ ቅዱስ፣ አማኞች ሁሉ እርሱን እስኪሹት፣ በእነርሱ ሕይወት ውስጥ እስኪገባ ድረስ እስኪጠይቁት፣ ፈቃዳቸውን እስኪገልጡለት ይጠብቃል፡፡” (E.G. White, *The Desire of Ages*, (1898) p. 671.2 and 672.1)

ቶማስ ኤ. ዴቪስ ይህንን ሂደት እንደሚከተለው ይገልፀዋል፡- “ይህ ማለት ያለ መንፈስ ቅዱስ፣ ክርስቶስ ለሰዎች የሠራው ሥራ ውጤታማ አይሆንም ማለት ነው፡፡ ክርስቶስ በምድር

ላይ ያከናወናቸው፣ ማለትም፡- በጌቴሴማኒ፣ በመስቀል ላይ፣ በትንሳኤ ዕለት እንዲሁም አሁን በሰማይ እያከናወነ ያለው የክህነት አገልግሎት፣ ያለ መንፈስ ቅዱስ ውጤታማ አይሆንም፡፡ የመንፈስ ቅዱስ *ሥራ* ከሌለ፣ ክርስቶስ በምድር የሠራቸው *ሥራዎች* ውጤት በዚህ ዓለም ካሉት ሌሎች *ታላላቅ ኃይማኖቶች* ወይም ደግሞ የስነ-ምግባር *መሪዎች* ከሚያስተምሩት የተለየ አይሆንም ነበር፡፡ ምንም እንኳ ክርስቶስ ከእነዚህ ጋር ሲነፃፀር እርሱ አምላክ ቢሆንም፣ ሰብዓዊውን ዘር በምሳሌነቱና በትምህርቱ ብቻ ማዳን አይችልም ነበር፡፡ ሰዎችን ለማዳን በእነርሱ ውስጥ ሆኖ *መሥራቱ* አስፈላጊ ነበር፡፡ በሰዎች ልብ ውስጥ ሆኖ ሰዎችን የማዳን *ሥራ* የሚሠራው ደግሞ በክርስቶስ በኩል ይህንን *ሥራ* እንዲሠራ በተላከው በመንፈስ ቅዱስ ነው፡፡" (Thomas A. Davis, *Als Christ siegreich leben,* (HW-Verlag), Seite 43 / How to be a victorious Christian, R&H.)

በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ፍላጎትን ለመቀስቀስ ይህ ምክንያት ብቻ አይበቃም ነበር?

"የእግዚአብሔር መንፈስ በአማኙ ልብ ውስጥ ሲገባ፣ ሕይወቱ ይቀይራል፡፡ ኃጢአተኛ አስተሳሰቦች ተሸቀንጥረው ይጣላሉ፡፡ ክፉ *ሥራዎች* አይስተናገዱም፡፡ ፍቅር፣ ትህትና እና ሰላም የቁጣን፣ የቅናትን እና የጠብን ቦታ ይተካሉ፡፡ ሐዘን በደስታ ይለወጣል፡፡ የፊታችን ገፅታ የሰማይን ብርሃን ያንፀባርቃል፡፡" (E.G. White, The Desire of Ages, (1898), p. 173.1)

በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሕይወት ሌሎችም ብዙ የከበሩ ውጤቶች አሉት፡፡ ያለ እርሱ የሚኖር ሕይወት ደግሞ ብዙ እጥረቶችና ኪሳራዎች አሉት፡፡ በመንፈስ ቅዱስ በተሞላና ባልተሞላ ሕይወት መካከል ያለውን ልዩነት በምዕራፍ 4 ላይ በዝርዝሩ እንመለከታለን፡፡

## በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቻለሁን?

እስኪ ከዚህ በታች በመንፈስ ቅዱስ ስለ መሞላት የተጠየቁ ጥያቄዎችን ራስህን ጠይቅ፡-

➢ መንፈስ ቅዱስ በእኔ ሕይወት ውስጥ እየሠራ እንደሆነ የሚያሳዩ ምልክቶች ይታያሉን? ለምሳሌ፡- መንፈስ ቅዱስ ጌታ የሱስን ለእኔ ታላቅና ሕያው መሆኑን (እንደሆነ) አሳይቶኛልን? (ዮሐንስ 15፡16)

➢ ለውስጤ የሚናገረኝን የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ ማዳመጥና መረዳት ጀምሬአለሁን? በሕይወቴ ውስጥ በምወስናቸው ትልቅና ትንሽ ውሳኔዎች እንዲመራኝ ፈቅጄለታለሁን? (ሮሜ 8፡14)

➢ ሌሎች ሰዎችን ለማፍቀር አዲስ/ትኩስ የሆነ የፍቅር ስሜት በውስጤ ተቀስቅሷልን? መንፈስ ቅዱስ እንደ ጓደኞቼ ለማልቆጥራቸው ሰዎች ከፍ ያለ ርህራሄና ፍቅር እንዲሁም ለእነርሱ የመጨነቅ ስሜት ሰጥቶኛልን? (ገላትያ 5፡22 ፣ ያዕቆብ 2፡8-9)

➢ ከባልንጀሮቼ ጋር እንዴት መግባባት እንዳለብኝ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ደጋግሞ ሲያግዘኝ እየተለማመድኩ ነውን? በችግር ምክንያት ያዘኑትን ሰዎች ልብ ለማፅናናት ገንቢ ቃላትን ይሰጠኛልን?

➢ ለሌሎች ስለ የሱስ እንድመሰክርና እነርሱን ወደ እርሱ ዘላለማዊ መንግስት ለመምራት የሚያስችል ብርታት መንፈስ ቅዱስ ሰጥቶኛልን?

➢ መንፈስ ቅዱስ በፀሎት ሕይወቴ ሲረዳኝና በልቤ ውስጥ ያለኝን ጥልቅ ስሜት ለእግዚአብሔር በትክክል ለመግለፅ ሲያስችለኝ ይታወቀኛልን?

ስለ እነዚህ ጥያቄዎች ስናስብ፣ ምን ያህል በመንፈስ ቅዱስ ልምምድ ማደግ፣ እርሱን የበለጠ ለማወቅና እርሱን የበለጠ ለመውደድ ስላለን ፍላጎት ማስተዋል እንጀምራለን፡፡

## በአባትና በልጅ መካከል የተፈጠረው እርቅ

አንድ ወንድም እንዲህ ብሎ ጻፈልኝ፡- "አባቴና እኔ ታረቅን፡፡ *ወደ የግል መንፈሳዊ መነቃቃት የሚመራ መንገድ* የሚለዉንና *የ40 ቀናት ቁ. 1 እና ቁ. 2 መጽሐፎችን* ካጠናሁ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ የመሞላትን አስደናቂ ልምምድ አገኘሁ፡፡ የመንፈስ ቅዱስን አሠራር በሕይወቴ ስለማመድና በእኔ በራሴ ሕይወት ውስጥ መሥራቱን ስመለከት እጅግ በጣም ተደሰትኩኝ፡፡

የእኔና የአባቴ ግንኙነት በአብዛኛዉ የተወሳሰበ ነበር፡፡ በልጅነትም ሆነ በወጣትነት እድሜዬ ጀምሮ ጸሎቴም ሆነ ምኞቴ የነበረዉ ከአባቴ ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲኖረኝ ነበር፡፡ ነገር ግን ከቀን ወደቀን ግንኙነቴ እየተበላሸ መጣ፡፡ ሌሎች ስድስትና ሰባት ዓመታት ካለፉ በኋላ፤ እግዚአብሔር የልቤን ታላቅ ባዶነት ሞላዉ፡፡ እኔና ባለቤቴ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት ስናጠናና ስንጸልይ ከእግዚአብሔር ጋር ብዙ ነገሮች ተለማመድን፡፡ ለቤተሰቦቻችን፣ በተለይም ደግሞ ለአባቴ እንጸልይ ነበር፡፡ በዚህን ጊዜ ነበር አባቴን እንድወደዉ አዲስ ኃይል የተቀበልኩት፡፡ ከዚህም የተነሳ በልጅነት ዕድሜዬ ከአባቴ ጋር መልካም ስላልነበረዉ ግንኙነት ሁሉ አባቴን ይቅር ማለት ቻልኩ፡፡ አሁን እኔና አባቴ በጣም ተግባብተናል፡፡ ባሁኑ ሰዓት አባቴ ጥሩ መንፈሳዊ ሰዉ መሆን ጀምሮአል፤ እንዲሁም ለሌሎች ስለ እግዚአብሔር ማንነት

ይመሰክራል፤ አሁንም፣ ከሁለት ዓመታት በኋላ ማለት ነው፣ እኔ ከአባቴ ጋር ያለኝ ግንኙነት እጅግ መልካም ነዉ፡፡ ስለዚህ ልምምድ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡ ከዚህ ልምምድ በፊት ብዙ ጊዜ ደካማነትና ብቸኝነት ይሰማኝ ነበር፡፡ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት በየቀኑ መጸለይ ከጀመርኩ ወዲህ ግን አዲስና አስደናቂ ሕይወት እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጋር ጥሩ ግንኙነት ማድረግ ችያለሁ"፡፡

**ፀሎት፡-** ጌታ የሱስ ሆይ፣ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በዉስጤ ለመኖር ስለምትፈልግ አመሰግናለሁ፡፡ በየቀኑ ራሴን ላንተ ስለማስረከብ፣ እርስ በርስ ያለን የመተማመንና የፍቅር ግንኙነት ስለሚያድግ አመሰግንሃለሁ፡፡ ጌታ ሆይ መንፈስ ቅዱስን በተለየ ሁኔታ እንዳዉቅና ሥራዉንም እንድረዳ እርዳኝ፡፡ ለኔ፤ ለቤተሰቤ፤ ለቤተ-ክርስቲያኔ መንፈስ ቅዱስ ሊያደርግ የሚፈልገዉን ሁሉ ለማወቅ እናፍቃለሁ፡፡ የመንፈስ ቅዱስን ሙላት በየቀኑ ስጠይቅህ፣ በእርሱ እንደተሞላሁ እርግጠኝነት እንዲሰማኝ እርዳኝ፡፡ ፀሎቴን ስለሰማህልኝ አመሰግናለሁ፡፡ አሜን!!

## ኤፌሶን 5፡18ን በተመለከተ ተጨማሪ ሃሳብ፡-
## "መንፈስ ይሙላባችሁ"

ኤፌሶን 5፡18ን በምናነብበት ጊዜ ሃሳቡ በትእዛዛዊ ዐርፍተ ነገር እንደተፃፈ እንመለከታለን፡፡ በተጨማሪም ትእዛዙ የሚመለከተዉ አንድን ሰው ብቻ ሳይሆን ሁላችንንም ነዉ፡፡ ሌላዉ በዚህ ጥቅስ ዉስጥ የምናየዉ ነጥብ ደግሞ፣ የመንፈስ ቅዱስን ሙላት መፈለግ የሁላችንም ሃላፊነት (ተግባር) መሆኑን ነዉ፡፡ የግሪኩ ዋናዉ ስርወ ቃል ይህንን ይበልጥ ግልጽ ያደርግልናል፡፡

*ዮሐንስ ማገር* የተባለው ፀሐፊ ስለዚህ ጥቅስ አስተያየት ሲሰጥ እንዲህ ብሎ ነበር፡- "በአዲስ ኪዳን ከተጻፉት ደብዳቤዎች መካከል ስለ መንፈስ ቅዱስ መሞላት በግልጽ የሚናገረዉ <*መንፈስ ይሙላባችሁ*> የሚለዉ በኤፌሶን 5፡18 ላይ የተፃፈው ጥቅስ ብቻ ነዉ፡፡ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የተጠቀሰው <በመንፈስ ቅዱስ መሞላት>፣ በልዩ ሁኔታዎች ውስጥ ስንሆን ከሚሰጡን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ጋር በተያያዘ መልኩ ነው፡፡ በአንፃሩ ግን ጳውሎስ በኤፌሶን መልእክት ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ ስለ መሞላት አስፈላጊነት በትዕዛዝ መልኩ ነው ያስቀመጠው (የተናገረው)፡፡ ይህም ትእዛዝ ሁሉንም የክርስቶስ ተከታዮች ይመለከታል፡፡ ይህ አጭር፣ ነገር ግን አስፈላጊ የሆነው ትእዛዝ በዉስጡ አራት ወሳኝ ነጥቦችን አካቶ ይዞአል፡-

1. **"ይሙላባችሁ"** (plerein) በሚለው ግስ የተገለጸው ቃል የተጻፈዉ በትእዛዝ መልኩ ነዉ። ጳውሎስ ይህንን ሲጽፍ፣ ሰዉ ሊቀበለዉ ወይም ሊተወዉ ይችላል የሚለዉን ምክር አይደለም እየሰጠ ያለዉ፡፡ ስልጣን ያለው ሐዋሪያ እንደመሆኑ፣ ትዕዛዝ እየሰጠን ነው ያለው፡፡ እንዲሁም ደግሞ ነጻ ምርጫችንን ተጠቅመን እንድንወስን ያሳስበናል፡፡ ስለዚህ አንድ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ወይም ላለመሞላት የራሱ ምርጫ ሚና ይጫወታል ማለት ነው። **ክርስቲያኖች <መንፈስ ቅዱስን ለመሞላት የተጋችሁ ሁኑ> ለሚለዉ ትእዛዝ ራሳቸዉን ሊያስገዙ ይገባቸዋል፡፡** በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን በተመለከተ ይህ የእያንዳንዳችን ኃላፊነት ነው፡፡

2. ግሱ የተፃፈዉ በብዙ ቁጥር ፎርም ነዉ፡- <ይሙላባችሁ>፡፡ ትእዛዙ የሚመለከተዉ በቤተክርስቲያን ዉስጥ አገልግሎት ለመስጠት ኃላፊነትን ለወሰዱ ጥቂት ሰዎች ብቻ አይደለም፡፡ ስለዚህም፣ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ለጥቂት ልዩ ኃላፊነት ላላቸው ሰዎች ብቻ የሚሰጥ ልዩ ስጦታ አይደለም፡፡ **ጥሪዉ በቤክርስቲያን ዉስጥ ላሉ ሁሉም ምእመናን ነዉ፡፡ በየትኛዉም ጊዜ፣ በየትኛዉም ቦታ፣ በማንም ላይ እግዚአብሔር አድልዎ አያደረግም፡፡** ለጳዉሎስ ምንም ልዩነት አልነበረዉም፤ ሁሉም ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ ሊሞሉ ይገባቸዋል፡፡

3. ግሱ በቀጣይነት ፎርም ነዉ የተጻፈዉ፡፡ <በመንፈስ ተሞሉ> ሳይሆን የሚለው፤ <መንፈስ (በቀጣይነት/ያለማቋረጥ) ይሙላባችሁ> ነዉ የሚለዉ፡፡ ማንም ሰዉ ራሱን በመንፈስ ቅዱስ ሊሞላ አይችልም፡፡ ይህ የመንፈስ ቅዱስ ብቻ ሥራ ነዉ፡፡ ይህ የእርሱ ልዕልና ነዉ፡፡ **ነገር ግን ማንኛውም ግለሰብ በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር አለበት፡፡ ያለ ግለሰቡ ፈቃድ መንፈስ ቅዱስ በግለሰቡ ሕይወት ሊሠራ አይችልምና፡፡**

4. በግሪከኛ ቋንቋ የተፃፈው ይህ ትዕዛዝ የተፃፈዉ 'በአሁን ጊዜ' (present time) ፎርም ነዉ፡ ፡ ይህ በአሁን ጊዜ ግስ የተጻፈዉ የግሪኩ ቃል የሚያመለክተዉ ተግባሩ በቀጣይነት የሚደጋገም መሆኑን ነዉ፡፡ ተቃራኒው ቃል 'aorist tense' የሚለው ነዉ፡፡ ይህ የሚያመላክተው የአንድ ጊዜ ተግባርን ነዉ፡፡ ስለዚህ በዚህ ዓረፍተ ነገር ዉስጥ የተገለፀው <*በመንፈስ ቅዱስ መሞላት*> የሚለው ቃል የአንድ ጊዜ ክስተት ወይም ልምምድ ሳይሆን ነገር ግን ተደጋጋሚና ቀጣይነት ያለዉ ሂደት መሆኑን ነዉ፡፡ **አንድ ክርስቲያን፣ አንዴ ከሞላ በኋላ ሌላ የማያስገባ እንስራ**

**ሳይሆን፤ ነገር ግን ያለማቋረጥ መልሶ መላልሶ የሚሞላ እንስራ ነዉ፡፡** በመሆኑም አረፍተ ነገሩ **<ሳታቋርጡ፣ እንደገና፣ በአዲስ መልክ፣ በተደጋጋሚ መንፈስ ቅዱስ ይሙላባችሁ>** ለማለት ነዉ የፈለገዉ፡፡

**ጌታን ለመከተል ከወሰንን በኋላ በውሃ ጥምቀት በተጠመቅን ጊዜ የተሰጠን የመንፈስ ቅዱስ መሞላት ያለማቋረጥ በዉስጣችን ማቆየት ካልቻልን ልናጣዉ እንችላለን፡፡** በርግጥ ምናልባት በተለያየ ምክንያት ብናጣውም እንኳ እንደገና ልናገኘው እንችላለን፡፡ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ያለብን በተደጋጋሚ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ መላው ኑሮአችንን ስለሚሞላው፣ በመንፈሳዊ ሕይወታችን መጠዉለግና መቀጨጭ አይኖርም፡፡ መንፈስ ቅዱስን መሞላት ማለት በውስጣችን በቁጥር እጅግ ብዙ መንፈስ ቅዱስ ይኖረናል ማለት ሳይሆን፣ መንፈስ ቅዱስ እኛን ሙሉ በሙሉ ሲቆጣጠረን ስናስተውል ማለት ነው፡፡ ለዚህ ነዉ ጳዉሎስ ለአማኞች በሙሉ <መንፈስ ቅዱስ ሳያቋርጥ ይሙላባችሁ> ብሎ ያዘዘው፡፡ ይህ ደግሞ አንድ ክርስቲያን ሊኖረው የሚገባ ሕይወት ነዉ፡፡ አንዲት ጥምቀት፣ ነገር ግን ብዙ የመንፈስ ቅዱስ መሞላቶች፡፡” (Johannes Mager, *Auf den Spuren des Geistes,* (Lüneburg, 1999) page 100-101 (with permission from the publishing house)

ጌታ እራሱ ነው ትእዛዙን የሰጠው፣

ያለማቋረጥ፣ ሁልጊዜ፣ በተደጋጋሚ መንፈስ ቅዱስ ይሙላባችሁ!!

(E.G. White, Mount of Blessing, MB 20.3 - egwwritings.org)

(Johannes Mager, *Auf den Spuren des Heiligen Geistes* (Lüneburg, 1999), Seite 101)

ምዕራፍ 4

# በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ወይም ያለመሞላት ውጤቶች

## በመንፈስ ቅዱስ በመሞላታችን ምን ጥቅም እናገኛለን? በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ባንጸልይስ ምን እናጣለን?

### በሥጋዊ ክርስትና እና በመንፈሳዊ ክርስትና መካከል ያለው ንጽጽር

ሥጋዊ ክርስትና በግለሰቦች ሕይወት ውስጥ ስለሚያስከትለው ዉጤት ከዚህ በፊት በከፊል ለመግለጽ ተሞክሮአል፡፡ ሌሎች የሥጋዊ ክርስትና ውጤቶች እንደሚከተለው ይገለፃሉ፡-

- ሥጋዊ ክርስቲያን በዚህ ሁኔታ ከቆየ አይድንም (ሮሜ 8፡ 6-8 ፤ ራዕይ 3፡16)
- መለኮታዊ ፍቅር (አጋፔ ፍቅር) በሥጋዊ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የለም (ሮሜ 5፡5 ፤ ገላትያ 5፡22)፡፡ ፍቅሩ በሰብአዊ ፍቅር ብቻ የተደገፈ ነዉ፡፡
- የኃጢአት ኃይል አልተሰበረም (ገላትያ 5፡ 16 ፤ ሮሜ 8፡2)
- ሥጋዊ ክርስቲያን <እንደ ክብሩ ባለጠግነት በውስጥ ሰውነቱ የሚያጠነክረውን ኃይል> አልተቀበለም (ኤፌሶን 3፡16፣17)
- ክርስቶስ በሥጋዊ ክርስቲያን ልብ ዉስጥ አይኖርም (1ዮሐንስ 3፡24)
- ሥጋዊ ክርስቲያን ክርስቶስን ለመመስከር የሚያስችለዉን ኃይል አልተቀበለም (የሐዋ 1፡8)
- እንደ ሰዉ ልማድ ይመላለሳል (1ቆሮንጦስ 3፡3) በመሆኑም በቀላሉ ወደ ክርክርና ወደ ጥል ይሄዳል፡፡
- እንዲህ ዓይነቱ ሰዉ ተግሳጽን መቀበል ይከብደዋል፡፡
- ምናልባትም የጸሎት ሕይወቱም ደካማ ነዉ፡፡
- ግለሰቡ ቀናተኛ ላለመሆንና ይቅርታን ለማድረግ ያለዉ የሰዉ ጥበብ ብቻ ነዉ፡፡
- ሥጋዊ ክርስቲያን ይቅርታ ለማድረግና ቂም ላለመያዝ በጣም ይከብደዋል (ሰው በተፈጥሮው ደካማ ስለሆነ)

ሥጋዊ ክርስቲያን አንዳንድ ጊዜ እንደ ተፈጥሮአዊ ሰዉ (ዳግም ያልተወለደ) ይመስላል፡፡ ሐዋሪያው ጳዉሎስ እንደሚለው፡- “እንደ ሰው ልማድ ይመላለሳል” (1ቆሮ. 3፡3)፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ይህ ሥጋዊ ክርስቲያን የሚያደርጋቸው ድርጊቶች በሙሉ የሚደረጉት በራሱ ጥረትና ችሎታ ብቻ ቢሁንም፣ መንፈሳዊ ሰዉ እንደሚያደርገዉ አይነት ለማስመሰል ይሞክራል፡፡

**መንፈሳዊ ክርስቲያን** የእግዚአብሔርን ሙላት ይለማመዳል፡-

"... በሰማይና በምድር ለሚኖሩ ቅዱሳን ሁሉ አባት በሆነው በእግዚአብሔር ፊት በጉልበቴ እንበረከካለሁ፡፡ ጸሎቴም፣ አምላክ እንደ ክብሩ ባለጠግነት መጠን ለውስጥ ሰውነታችሁ የሚያጠነክራችሁን የመንፈስ ቅዱስን ኃይል እንዲሰጣችሁ ነው፡፡ ክርስቶስ በእምነት በልባችሁ እንዲኖር፣ እንዲሁም በጌታ ፍቅር ሥር ሰድዳችሁና ተመስርታችሁ በእርሱ ኃይል እንድትመላለሱ እጸልያለሁ፡፡ ከሌሎች የእግዚአብሔር ልጆች ሁሉ ጋር አእምሮን ሁሉ የሚያልፈው የክርስቶስ ፍቅር ስፋቱ፣ ርዝመቱ፣ ከፍታውና ጥልቀቱ ምን ያህል እንደሆነ አውቃችሁ፣ እስከ እግዚአብሔር ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ እንድትሞሉ ከልብ እጸልያለሁ፡፡ ከምንለምነውና ከምናስበው አስበልጦ አስደናቂ በሆነው ኃይሉ በሕይወታችን ውስጥ ሊሰራ ለሚችለው ለእግዚአብሔር፣ በቤተ ክርስቲያን በኩል በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከትውልድ እስከ ትውልድ፣ ከዘላለም እስከዘላለም ለእርሱ ክብር ይሁን፡፡ አሜን!" (ኤፌሶን 3፡15-21)

## የሥጋዊ ክርስትና ውጤቶች

ከዚህ ቀደም በመንፈስ ቅዱስ ሳልሞላ በኖርሁት ሕይወት እንዲሁም እንደ ፓስተርም ባገለገልኩበት ጊዜ ስለደረሰብኝ ኪሳራ በጣም አዝናለሁ። ሌሎች ሰዎችን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ወደተሻለ ደረጃ እንዲያድጉ መምከር የምንችለው እኛ ራሳችን እስከደረስንበት መንፈሳዊ ደረጃ ድረስ ነው። በየግላችን፣ በየቤተሰባችን እንዲሁም በየቤተክርስቲያናችን በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሕይወት ከሌለን ችግሩን (ኪሳራውን) እናባብሰዋለን።

### ልጆችና ወጣቶች

ሥጋዊ ክርስትና፣ ለዘብተኛ የክርስትና ሕይወት የሚራባበት ምቹ ስፍራ ነው። ለምን ይሆን ብዙ ወጣቶች በቤተክርስቲያናችን ውስጥ የሌሉት? አንዳንድ ክርስቲያኖች ባለማወቅ ለእነርሱ መልካም መስሎ የታያቸውን፣ ነገር ግን በተግባር ለማዋል የማይችሉትን ነገር ለማድረግ

ይሞክሩና ከዚያ አልሳካ ሲላቸው፣ የሠሩትን ስህተት ለመሸፈን የተለያዩ ምክንያቶችን መስጠት ይጀምራሉ። ምናልባት ብዙ ወጣቶችን በቤተክርቲያናችን ያጣንበት ምክንያት ይሄ ይሆንን? ምናልባት ባለማወቅ ለልጆቻችንና ለወጣቶቻችን የሥጋዊ ክርስትና ምሳሌ ሆነን ይሆን? በውጤቱም እነርሱም ሥጋዊ ክርስቲያኖች ሆነው በተስፋ መቁረጥ ተሞልተው ይሆን? ምናልባት ብዙ ሰዎች የእምነትን ጉዳይ ከቁምነገር ተራ የማይመድቡት ወይም ወደ ቤተክርስቲያን የማይመጡት አልያም ከቤተክርስቲያን የሚቀሩት ለዚህ ይሆን?

በቅርቡ አንድ ሽምገል ያለ ወንድም ለቤተክርስቲያኑ ምዕመናን እንዲህ አላቸው፡-

“በእኛ በግል ሕይወትና በወጣቶቻችን ሕይወት ውስጥ ለምናያቸው ችግሮች መንስኤው እኛ በዕድሜአችን የገፋነው የመንፈስ ቅዱስን አሠራር ባለማስተዋላችንና በመንፈስም ባለመሞላታችን ነው።” (Garrie F. Williams, *Erfülltsein vom Heiligen Geist – Wie erfahren wird das?* (Lüneburg 2007), S. 8)

ለብ ያለ የክርስትና ሕይወት (ሙሉ በሙሉ ራስን ለክርስቶስ ያላስረከበ ሕይወት) የሚያስከተለውን ትልቅ አደጋ ላስታውሳችሁ እወዳለሁ፡- <የግማሽ ልብ ክርስቲያኖች (ለብ ያለ የክርስትና ሕይወት ያላቸው) ሃይማኖት ከሌላቸው ሰዎች እጅግ የከፋ ሁኔታ ላይ ናቸው። ምክንያቱም አታላይ ቃላቶቻቸውና ሙሉ በሙሉ ለጌታ ያልተሰጠው አቋማቸው ብዙዎችን ወደ ጥፋት ይመራልና። ሃይማኖት የሌለው ሰው ቢያንስ ማንነቱን በይፋ ያሳያል። ለብ ያለ ክርስቲያን ግን ሁለቱንም ጎራ ያታልላል። እንዲህ ያለው ሰው ወይ የለየለት ዓለማዊ አይደለም፣ ወይም ደግሞ ሙሉ በሙሉ ራሱን ለጌታ የሰጠ ክርስቲያን አይደለም። ሰይጣንም ሌላ ማንም ሊሠራ የማይችለውን ሥራ ለማከናወን እንደዚህ አይነቱን ሰው ይጠቀምበታል>። (EGW Letter 44, 1903, quoted in Adventist Bible Commentary, Vol.7, p.963 on Rev. 3:15-16)

ነገር ግን እንደ መንፈሳዊ ክርስቲያን ከኖርን፣ ልጆቻችን የእግዚአብሔርን የእርዳታ እጅ የሚጨብጡበትን መንገድ እናሳያቸዋለን። ኤለን ኋይት እጅግ አስገራሚ በሆነ መልኩ እንዲህ ትላለች፡-

“ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት በየዕለቱ መቀበል ለእነርሱ የተሰጣቸው የከበረ እድል እንደሆነ ልጆቻችሁን አስተምሯቸው። የሱስ ፈቃዱን ለመፈጸም የሚጠቀምባችሁ የእርሱ እጆች ሁኑ። ለልጆቻችሁ በምትሰጡት አገልግሎት ስኬታማ ሊያደርጋችሁ የሚያስችላችሁን ልምምድ በጸሎት ልታገኙ ትችላላችሁ።” (E.G. White, Child Guidance (1954), p. 69)

በርግጥ ልጆቻችንን መጸለይን አስተምረናቸዋል። ነገር ግን በየቀኑ በመንፈስ ቅዱስ ስለ መሞላት እንዲጸልዩ አስተምረናቸዋልን? ወይስ እኛ ራሳችን ይህ እንደሚያስፈልገን ገና አላወቅንም? እኔና ባለቤቴ ከዚህ ቀደም ይህንን አናውቅም ነበር። አለማወቃችንን በይቅርታው ስላለፈን እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ። ነገር ግን ከዚህ ቀደም ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት ባለመፀለያችን ስንት ኪሳራ ይሆን የደረሰብን?

መንፈሳዊ ወላጆች በየዕለቱ ራሳቸውን ለየሱስ ሲሰጡና በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ሲጸልዩ፣ ልጆቻቸው ግሩም ልጆች ይሆኑላቸዋል።

## በመለኮታዊ ፍቅር መውደድ ወይስ መልካም ለሆኑልን መልካም መሆን?

በዲሲፕሊን የተመራ ሕይወት እንድንኖር የሚረዳን የእግዚአብሔር ኃይል ባይኖር፣ የእግዚአብሔር ፍቅር ባይኖር እንዲሁም የኃጢአት ኃይል ባይሰበር ወይም ደግሞ በአንጻሩ እነዚህ ሁሉ ነገሮች በእግዚአብሔር ጸጋ ቢኖሩ፣ በሥጋዊ እና በመንፈሳዊ ክርስቲያን የትዳር፣ የቤተሰብ፣ የቤተክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ምን አይነት ልዩነቶች ይኖሩ ይሆን?

ወግ አጥባቂ ሥጋዊ ክርስቲያኖች መተቸት ይቀናቸዋል። ይህ ደግሞ መልካም አይደለም። ምንም እንኳን እግዚአብሔር ስለሰጠን መመሪያዎች ማውራት ቢኖርብንም፣ በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ መሠረታዊ ለውጥ የሚከሰተው ለውጡ ከውስጥ ሲመጣ ብቻ እንደሆነ ልናስተውል ይገባል።

ለዘብተኛ ክርስቲያኖች ደግሞ ነገሮችን ቀለል አድርገው ይወስዳሉ እንዲሁም ዓለማዊ ዘዴዎችን ወደ ቤተክርስቲያን ለማምጣት ይሞክራሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር ይህንንም አይባርክም።

ጆሴፍ ኪደር የቤተክርስቲያናችንን አጠቃላይ ሁኔታ በተመለከተ የሚከተሉት ነገሮች ጎልተው እንደሚታዩብን አስተውሎአል፡- “ግዴለሽነት፣ አስመሳይነት፣ ዓለማዊነት፣ የልግስና መጥፋት፣ የአገልጋዮች በሥራ ብዛት መዳከም፣ የወጣቶች ቤተክርስቲያንን ትቶ መሄድ፣ ውጤት አልባ እቅዶች፣ ጠንካራና ሙሉ በሙሉ ለጌታ የተሰጡ ሰዎች ቁጥር ማነስ” (Dr. S. Joseph Kidder, Anleitung zum geistlichen Leben (Andrews University), PPP Folie 3+4)

የችግራችን ዋናው መንስኤ ከክርስቶስ ጋር ያለን ግንኙነት መላላት፣ እንደዚሁም ደግሞ በሰብአዊ ጥበብ ላይ ያለን ከመጠን ያለፈ መደገፍ ነው (ዮሐንስ 15፡1-5 ፤ ዘካርያስ 4፡6)።

መፍትሔው በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሕይወትን መኖር እንደሆነ ጆሴፍ ኪደር አስተውሎአል (የሐዋርያት ሥራ 1፡8)።

የሱስ አዲሱን ትእዛዝ ሰጥቶናል፡-

"አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፤ ይኸውም እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ ነው፤ እንግዲህ እኔ እንደ ወደድኋችሁ እናንተም እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ። እርስ በርሳችሁ ብትዋደዱ፣ ሰዎች ሁሉ የእኔ ደቀ መዛሙርት እንደሆናችሁ በዚህ ያውቃሉ።" (ዮሐንስ 13፡34-35)

የሱስ እንደወደደው መውደድ ማለት፣ በመለኮታዊ ፍቅር (በአጋፔ ፍቅር) መውደድ ማለት ነው። ይህንን ማድረግ የምንችለው ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ስንሞላ በቻ ነው።

"የሰማዩ አባታችን ሊሰጠን የሚችለው ታላቁ ስጦታ <ፍቅር> ሲሆን ይሄም ፍቅር፡- *<ገደብ የሌለው ፍቅር ለእግዚአብሔር>* እንደዚሁም *<ራስ ወዳድነት የሌለበት ፍቅር ለእርስ በርስ>* ነው። ይህ ፍቅር ስሜታዊ ሳይሆን መለኮታዊ መርህ እንዲሁም ጽኑ ኃይል ነው። ያልተቀደሰ ልብ [በመንፈስ ቅዱስ ያልተሞላ ልብ] ይህንን አይነት ፍቅር ሊያመነጭ አይችልም። ይህ አይነት ፍቅር የሚገኘው የሱስ በነገሠበት ልብ ውስጥ ብቻ ነው። " (E.G. White, *Acts of the Apostles* (1911) p. 551.2)

በጎ በማሰብና ሰውን በእግዚአብሔር ፍቅር በመውደድ መካከል ልዩነት ያለ ይመስለኛል። ኤለን ኋይት ወሳኝ የሆነ መመሪያ ሰጥታናለች፡-

"የትህትናና የጭምትነት መንፈስ እንደጌጥ ቢለበስ ኖሮ፣ ሕይወትን እጅግ መራራ ከሚያደርጉት አንድ መቶ መከራዎች (ችግሮች) መካከል ዘጠናዘጠኙ በተወገዱ ነበር።" (E.G. White, *Testimonies for the Church,* volume 4, p. 348.3)

የእግዚአብሔር ቃል በ 1 ተሰሎንቄ 4፡3-8 ላይ ስለ ትዳር ሕይወት የሚናገረው አለ። እነዚህ ጥቅሶች በትዳር ሕይወት ውስጥ በቅድስናና በመከባበር ስለመኖር አስፈላጊነት ይናገራሉ። ይህም፣ አህዛብ ከሚኖሩት በፍትወት ስሜት ከሚመራው ሕይወት ጋር ተነጻጽሮ ቀርቦአል። ስለ

ተቀደሰ ሕይወት አስፈላጊነትና ስለ መንፈስ ቅዱስ ሦስት ጊዜ በመደጋገም መናገሩ፣ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሕይወት የትዳር ግንኙነታችንንም መለወጥ እንደሚችልና መለወጥም እንዳለበት ከዚህ ልንረዳ እንችላለን። እግዚአብሔር ታላቅ ደስታና እርካታ በትዳር ሕይወታችን እንዲኖረን ይፈልጋል። ከመጠን በላይ ባለፈ በፍትወት ስሜት ሳይሆን በእውነተኛ ፍቅር የትዳር ሕይወታችንን እንድንመራ እግዚአብሔር ሊረዳን እንደሚፈልግ ይህ ቃል አያሳየንምን?

የሱስ ለደቀ መዛሙርቱ አንድነት ፀለየ፡-

"አባት ሆይ፤ አንተ በእኔ፣ እኔም በአንተ እንዳለሁ ሁሉም አንድ እንዲሆኑ፣ እንዲሁም አንተ እኔን እንደ ላከኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፣ እነርሱም በእኛ እንዲሆኑ ነው።" (ዮሐንስ 17፡21)

ዊልያም ጂ. ጆንሰን እንዲህ ይላል፡- "ብዙ አድቬንቲስቶች ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ገና ጠንቅቀው ሊረዱ ይገባል። ምናልባት ከዚህ ቀደም ለዚህ እውነት ተገቢውን ትኩረት አልሰጠነው ይሆናል ወይም ደግሞ በተሳሳተ መንገድ ተረድተነው ይሆናል። " (William G. Johnsson, Adventgemeinde in der Zerreißprobe, (Lüneburg 1996), p. 118)

***" የእግዚአብሔር ህዝቦች በመንፈስ አንድነት አንድ ሲሆኑ ፣ የአይሁድ ህዝብ ኃጢአት የነበረው የፈሪሳዊነት፣ የመመጻደቅ ኃጢአት ሁሉ ከልባችን ይወገዳል"***

በመንፈስ ቅዱስ ስንሞላ ክርስቶስ በእኛ ውስጥ ይሆናል። የመንፈሳዊ ክርስትና ሕይወትን መኖር የጌታችን ጸሎት መልስ እንዲያገኝ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ኤለን ኋይት እንዲህ ትላለች፡- "የእግዚአብሔር ህዝቦች በመንፈስ አንድነት አንድ ሲሆኑ ፣ የአይሁድ ህዝብ ኃጢአት የነበረው፣ የፈሪሳዊነት፣ የመመጻደቅ ኃጢአት ሁሉ ከልባችን ይወገዳል፡፡ ከዘመናት እስከ ዘመናት ተሰውሮ የነበረውን የእግዚአብሔር ምስጢር እግዚአብሔር ይገልጣል። 'የዚህ ምስጢር ክብር ባለጠግነት ምን እንደሆነ ሊያስታውቅ ወደደ፣ ምስጢሩም፣ የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በእናንተ ዘንድ መሆኑ ነው።' (ቆላስያስ 1:27)" (E.G. White, Selected Messages, Book 1 (1958), p. 386.1)

## የማስተካከያ ምክር

የማስተካከያ ምክር በፍቅር ሲተገበር ወይም ደግሞ በፍቅር ሳይተገበር ሲቀር ልዩነት አለውን? በአብዛኛው፣ በሥጋዊ ክርስቲያን አባሎች የተሞላች ቤተክርስቲያን እንደዚሁም በሥጋዊ ፓስተርና የፊልድ (የሰበካ) ፕሬዚደንት የምትመራ ቤተክርስቲያን ምን አይነት ውሳኔ ልትወስን ትችላለች? እንደ ፓስተር የሠራሁበትን ጊዜ ወደኋላ ተመልሼ ሳስብ፣ መንፈሳዊ አባላት፣ ተሰናክለው የወደቁን ክርስቲያኖች በሚያስተካክል ምክር ወደ ሕሊናቸው ለመመለስ እንዲችሉ የማድረግ ችሎታ እንዳላቸው ተርደቻለሁ። ተሳስቶ የነበረው ግለሰብ ንስሃ ሲገባና ሲናዘዝ፣ የማስተካከያ ምክሩ ግቡን መታ ማለት ነው። አንዳንድ ጊዜ ሥጋዊያን ክርስቲያኖች የማስተካከያ ምክርን ለቅጣት፣ እንዲሁም አንዳንዴ ስልጣናቸውን ያላግባብ ለመጠቀም ያውሉታል። (ማቴዎስ 18:15-17; 1ቆሮንጦስ 3:1-4; 2 ቆሮንጦስ 10:3; ይሁዳ 19)፡፡

## የእግዚአብሔር ትንቢታዊ ቃል ለመጨረሻዎቹ ቀናት

እግዚአብሔር አስፈላጊ መልዕክቶችን በነቢያቱ አማካይነት የማሳወቅ ልማድ አለው፡፡ (አሞጽ 3፡7) በመሆኑም ለመጨረሻው ዘመን የሚሆኑ አስፈላጊ ትንቢታዊ መልዕክቶችን በኤለን ኋይት አማካኝነት ሰጥቶናል፡፡ የምንኖርበት የመጨረሻው ዘመን ጥንት ከነበረው ዘመን ጋር ሲነፃፀር ብዙ ልዩነቶች ያሉት በመሆኑ፣ ጠቃሚ የሆኑ ተጨማሪ መረጃዎችን ከእግዚአብሔር ማግኘት አስፈላጊ እና የግድ ነው፡፡ በዘመናዊ አባባል ይህንን “update” ብለን እንጠራዋለን፡፡ እንደ ኤለን ኋይት ገለጻ ከሆነ እነዚህ መልዕክቶች የሱስ ዳግም እስኪመጣ ድረስ ለምዕመናን የሚጠቅሙ ናቸው፡፡ ምክሮቿ፡- የአኗኗር ዘይቤ ለውጥን፣ ምክርን፣ ግሳጼን ወ.ዘ.ተ. ያካተቱ ስለሆኑ ከሥጋዊ ክርስቲያን ይልቅ መንፈሳዊ ክርስቲያን በቀላሉ ይቀበላቸዋል፡፡ (ነገር ግን አንድ ሰው እነዚህን ምክሮች በትኩረት ስለተቀበለ ብቻ መንፈሳዊ ነው ማለት አይደለም)፡፡ ከዚህ ነጥብ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ቃል በዘዳግም 18፡19 ላይ ይገኛል፡፡ በጥሞና እናንብበው፡- “ነቢዩ በስሜ የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ አበቀላለሁ” ይህ በግልፅ የሚያሳየን በእውነተኛው ነቢይ በኩል የመጣው መልዕክት ጉዳዩ መልዕክቱን ካመጣው ሰው ጋር ሳይሆን ከራሱ ከእግዚአብሔር ጋር መሆኑን ነው፡፡

ታዲያ አንድ ሰው እውነተኛ ነቢይ መሆኑን እንዴት ማወቅ እንችላለን? የእግዚአብሔር ቃል ይህንን የምንመዝንበትን አምስት ነጥቦች ይነግረናል፡፡ እውነተኛ ነቢይ አምስቱንም ነጥቦች ማሟላት ይኖርበታል፡-

1. በአኗኗራቸው "ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ" ማቴዎስ 7፡15-20
2. የትንቢቶቹ መፈጸም፡- ዘዳግም 18፡21-22 (ከቅድመ-ሁኔታዊ ትንቢቶች በስተቀር ለምሳሌ፣ ትንቢተ ዮናስ)
3. ሰዎች ለእግዚአብሔር (ለእግዚአብሔር ቃል) ብቻ ታማኞች እንዲሆኑ የሚያስተምር፣ ዘዳግም 13፡1-5
4. የሱስ ክርስቶስ በሥጋ የመጣ (የተገለጠ) አምላክ መሆኑን መቀበሉ፡- 1ኛ ዮሐንስ 4፡1-3
5. ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር የሚስማማ መሆኑ፡- ዮሐንስ 17፡17

በነቢያት የተሰጡንን ምክሮች ጨምሮ፣ ሁሉም የእግዚአብሔር ትዕዛዛት ለራሳችን ጥቅም ነው የተሰጡን፡፡ ከዚህም የተነሳ እነዚህ ምክሮች ለእኛ እጅግ በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡ እኛም መንፈሳዊ ክርስቲያኖች፣ በነቢያት የተሰጡንን ምክሮች በሕይወታችን ስኬታማ ለመሆን እንደሚጠቅሙን አውቀን በእግዚአብሔር ኃይልና በደስታ ልንታዘዛቸው ይገባናል፡፡ "በአምላካችሁ በእግዚአብሔር እመኑ ትጸኑማላችሁ በነቢያቱም እመኑ ነገሩ ይሰላላችኋል፡፡" 2ኛ ዜና 20፡20

የጎልማሶች የሰንበት ትምህርት ጥናት መመሪያ ውስጥ፣ በመንፈስ ቅዱስ በተሞላ ሕይወት እና በእውነተኛ ነቢይ ቃላት መካከል ያለውን ግንኙነት ሲናገር የሚከተለውን ይላል፡- "የነቢያትን ቃል የማይቀበል ሁሉ የመንፈስ ቅዱስን ምክሮች እየተቃወመ ነው። የዚህ ተቃውሞ ውጤት ደግሞ በጥንት ዘመን ከነበረው የተለየ አይሆንም፤ ይኸውም ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነትን ማቋረጥ እና ለከፋ ተጽዕኖዎች የተጋለጠ መሆን ነው።" (Studienanleitung Standardausgabe, Philip G. Samaan, 10.11.1989, to question 8)

## ወንጌልን የማሰራጨት እቅድ/ስልት

ለክርስቲያኖች ወሳኝ ከሆኑት ኃላፊነቶች ውስጥ አንዱ በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ እና ወንጌልን በማሰራጨት አገልግሎት ውጤታማ መፍትሔዎችንና የክንውን ዘዴዎችን መቀየስ ነው። ማለትም እቅዶችንና ስልቶችን ማውጣት። ይህን የምናደርግበት ዋና ምክንያት ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ምዕመናንን በመንፈሳዊ ሕይወት ለማጠንከር እና ብዙ አዳዲስ ነፍሳትን ለማዳን ነው።

እኔ ከተጠመኩ 65 ዓመት ሆኖኛል፤ ለ43 ዓመታት ያህል ደግሞ በፓስተርነት አገልግያለሁ። በእነዚህ ዘመናት በርካታ እቅዶችንና የክንውን ዘዴዎችን አውጥተናል። እጅግ ታታሪዎችም ነበርን። ሃሳቡ ከዚህ ጋር ስለሚያያዝ እ.ኤ.አ. በ2005 ዓ.ም. የጀነራል ኮንፈረንስ ስብሰባ ላይ ድዋይት ኔልሰን ምን እንደተናገረ እንደገና ለማስታወስ ተገደድኩ፡-

"በርግጥ ቤተክርስቲያናችን ባላሰለሰ ጥረት እጅግ በጣም ጥሩ ንድፎችን፣ ዕቅዶችን እና መርሐ-ግብሮችን ቀርጻለች። ነገር ግን፡- እኛ አገልጋዮችና የቤተክርስቲያን መሪዎች በመንፈሳዊ ኪሳራ ውስጥ መሆናችንን ካልተቀበልን (ማለትም በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት እጥረት እንዳለብን አምነን ካልተቀበልን) በስተቀር በክርስትና ሕይወታችን ለውጥ አናይም።" (Helmut Haubeil (Hrsg.), Missionsbrief Nr. 34, (Bad Aibling, 2011) page 3)

ዴኒስ ስሚዝም ተመሳሳይ ነገር ተናግሯል፡- "እቅዶችን ማውጣት፣ መርሃ ግብሮችንና የክንውን ዘዴዎችን ማውጣት ትክክል አይደለም እያልኩ አይደለሁም፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሔርን የወንጌል ሥራ ለመሥራት በእነዚህ ነገሮች ላይ እየተማመንን እንዳይሆን እፈራለሁ፡፡ እቅዶች፣ መርሃ ግብሮችና የክንውን ዘዴዎች የእግዚአብሔርን ሥራ አይጨርሱትም፡፡ ታላላቅ ሰባኪያን፣ ድንቅ ክርስቲያናዊ ኮንሰርቶች፣ የሳታላይት ስርጭቶች የእግዚአብሔርን ሥራ አይጨርሱትም፡፡ በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉ ወንዶች እና ሴቶች ክርስቲያኖች ውስጥ ሆኖ በሚናገረው እና በሚያገለግለው በእግዚአብሔር መንፈስ ነው የወንጌል ተልዕኮ የሚጠናቀቀው፡፡" (Dennis Smith, *40 Days – Prayers and Devotions to Prepare for the Second Coming* (Wien, 2012), p. 88)

## ማጥመቅ/ነፍሳትን ማዳን

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያሳየን ከሆነ ሰዎችን ለክርስቶስ ለመማረክ መንፈስ ቅዱስ አስፈላጊ ሚና እንዳለው ነው (የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን ይመልከቱ)፡፡ በጀርመን ሃገር ውስጥ በአንድ በኩል እያደጉ ያሉ ቤተክርስቲያናት ሲኖሩ በሌላው በኩል ደግሞ ማደግ ያቆሙ ወይም እየኮሰሙኑ ያሉ ቤተክርስቲያናት አሉ፡፡ በርግጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ የቤተክርስቲያናችን ምዕመናን ቁጥር ባለፉት 60 ዓመታት በሃያ እጥፍ አድጓል፡፡ ነገር ግን አሁን በጀርመን አገር ስላለው አሳሳቢ ሁኔታ በርካታ ምክንያቶችን መዘርዘር ይቻላል፡፡ ለእኔ ግን አንድ ነገር ግልጽ ነው፤ ቤተክርስቲያን የማታድግበት ዋናው ምክንያት የምዕመናን በመንፈስ ቅዱስ አለመሞላት ነው፡፡ እርግጥ ነው፣ ችግሩ አስከፊ መሆኑን ስለተገነዘብን በርካታ እቅዶችን እና የወንጌል ስርጭት መርሃ ግብሮችን ቀርጸናል፡፡ አላስፈላጊ ወይም ያልተሳኩ እቅዶችን ከማውጣታችን የተነሳ እንዲሁም በጥረቶቻችን ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ባለመኖሩ የበጀት እና የጊዜ ኪሳራ እንዳስከተለብን ተመልክተናል፡፡

ሁለት የኤለን ኋይት ምክሮች ይህንን ያብራሩልናል፡-

"ዳግም ባልተወለዱ እንዲሁም ዳግም ተወልደው በነበሩ በኋላ ግን ባፈገፈጉ የቤተክርስቲያን አባላት የተነሳ፣ ጌታ በአሁኑ ጊዜ በርካታ ነፍሳትን ወደ እውነት ለማምጣት እየሠራ አይደለም፡፡ እነዚህ ያልተቀደሱ አባላት [ሥጋውያን ክርስቲያኖች] በአዳዲስ ነፍሳት ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ ይኖራቸው ይሆን?" (E.G. White, *Testimonies for the Church* Vol. 6, (1901) p. 370.3)

"በእግዚአብሔር ፊት ራሳችንን ዝቅ ብናደርግ፣ ደግ፣ ተግባቢ፣ ትሁት፣ የፍቅር ልብ ያለን እና ለሌሎች የምናዝን ብንሆን ኖሮ በአሁኑ ጊዜ እንደምናየው አንድ ሰው ብቻ ሳይሆን ጌታን የሚቀበለው፣ መቶ ሰዎች ሕይወታቸውን ለጌታ አሳልፈው ይሰጡ ነበር" (E.G. White, *Testimonies for the Church* Vol. 9 (1909), p. 189.4)

በሌላ በኩል ደግሞ በበቂ ሁኔታ ሳይዘጋጁ የሚጠመቁ ሰዎች አሉን፡፡ ኣለን ኋይት እንዲህ ጽፋለች፡-

"ዳግም መወለድ በዚህ ዘመን ያልተለመደ ልምምድ ነው፡፡ በቤተክርስቲያኖቻችን ውስጥ ብዙ ችግሮች ያሉብን ከዚህ ምክንያት የተነሳ ነው፡፡ የክርስቶስን ስም የያዙ (ክርስቲያን ነን የሚሉ) ብዙዎቹ፣ እጅግ በርካቶቹ ያልተቀደሱ ናቸው፡፡ ተጠምቀዋል ነገር ግን በሕይወት ሳሉ የተቀበሩ ናቸው፡፡ እኔነት አልሞተም፡፡ በውሃ ጥምቀት ከተጠመቁ በኋላ በአዲስ ሕይወት አልተነሱም" (E.G. White, MS 148 (1897))

ይህ የተጻፈው እ.ኤ.አ. በ1897 ዓ.ም ነው፡፡ ያ ዘመን ከአሁኑ ዘመን ጋር ተመሳሳይ እንዲሆን ያደረገው ሁኔታ ምንድን ነው? ችግሩ ይህ ነው፡- ዳግም ያልተወለደ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ አይደለም፡፡ የሱስ እንደዚህ አለ፡- "ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም" ዮሐ. 3፡5፡፡ በሁሉም የሕይወት ጎዳናዎች የመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ አስፈላጊነትን እየተገነዘብን ነውን?

## መንፈስ ቅዱስ እና ቃሉን መስበክ

ቃሉን መስበክ በተመለከተ መንፈስ ቅዱስ ስላለው ሚና እግዚአብሔር የሚከተለውን ይነግረናል፡ "ያለ መንፈስ ቅዱስ እገዛ እና ያለ እርሱ ያላቋረጠ መገኘት፣ ቃሉን [እንዲሁ] መስበክ ውጤታማ አይሆንም፡፡ የመለኮታዊ እውነት ብቸኛው ውጤታማ አስተማሪ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ የተሰበከውን የእውነት ቃል ወደ ልብ ውስጥ እንዲሰርፅ የሚያደርገው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ያን ጊዜ ነው ህሊና የሚነቃቃው ወይም ሕይወት የሚለወጠው፡፡ አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ቃል በደንብ ማስረዳት ይችል ይሆናል፣ ትዕዛዛቶቹንና ተስፋዎቹን ሁሉ ጠንቅቆ የሚያውቅ ሊሆንም ይችላል፣ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ የተሰበከውን ቃል ወደ ልብ ጓዳ ካላደረሰ በቀር የትኛውም ነፍስ <በማዕዘኑ ድንጋይ> ላይ ሊወድቅ እና <ሊቀጠቀጥ> አይችልም። የትኛውም የትምህርት ደረጃ፣ የትኛውም ምድራዊ ጥበብ ያለ እግዚአብሔር መንፈስ እርዳታ አንድን ሰው ውጤታማ ሰባኪ ሊያደርጉት አይችሉም፡፡" (E.G. White, *The Desire of Ages* (1898), p. 671.4)

የቃሉ ስብከት በቤተክርስቲያን አገልግሎት ብቻ ሳይሆን ትምህርታዊ በሆኑ ፕሮግራሞች ላይ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወቅት እንዲሁም በቤት ውስጥ በሚሰበሰቡ ትንንሽ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች ውስጥም የሚፈጸም ነው፡፡

ራንዲ ማክስዌል እንዲህ ይላል፡-

"መንፈሳዊ ኃይል የሌለን እና በወንጌል ስርጭት ውጤታማ ያልሆንንበት ምክንያት ሕያው ከሆነው ጌታችን ጋር ግንኙነት ስለሌለን ነው" (Randy Maxwell, *If my people pray …* (Pacific Press, 1995), p.11)

የመንፈስ ቅዱስ እጦት የፍርሃት መንስኤ ሊሆን ይችላልን? ኢሚሊዮ ክኔህትሌ ከዚህ ቀጥሎ የተፃፈውን ሲናገር ትክክል ነበር ማለት ነው? "ይህንን የተበላሸ ዓለም እና ስርዓቱን ለመገልበጥ ለምን ስኬታማ አልሆንንም? በስህተት የተረዳነው ነገር ስላለ ነው፡፡ ግጭቶችን፣ አለመግባባቶችን፣ ችግሮችን እንፈራለን፣ *ሥራችንን* ማጣት እንፈራለን፣ ስማችንን ማጣት እንፈራለን፣ ሕይወታችንን ማጣት እንፈራለን፡፡ ስለዚህ ፀጥ እንላለን፣ እንደበቃለን፡፡ ወንጌልን በፍቅር እና በኃይል ለዓለም ለማወጅ እንፈራለን" (CD *Die letzte Vorbereitung,* Teil 6)

ለዚህ ችግር መፍትሔ በሐዋርያት *ሥራ* 4፡31 ላይ ይገኛል፡- "ከጸለዩም በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ፣ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፣ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ [ያለፍርሃት] ተናገሩ"

## መንፈስ ቅዱስ እና መንፈሳዊ ጽሁፎቻችን

ስለ መንፈሳዊ ጽሁፎቻችን ኤለን ኋይት የሚከተለውን ጽፋለች፡- "የእግዚአብሔር መንፈስ ጽሁፉን ከሚጽፈው ሰው ጋር ከሆነ ያው መንፈስ ደግሞ ከአንባቢው ጋር ይሆናል፡፡ በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፈውን መልዕክት አንባቢው እንዲያስተውል መላእክት ተግተው ይሠራሉ፡፡" (E.G. White, *PH 016,* p. 29.1)

ይህንን ደግሜ መናገር እወዳለሁ፡- በርግጥ ያደረግነው አገልግሎት ሁሉ የተሳሳተ ነበር ማለት አይደለም፡፡ በፍጹም፡፡ ጥሩ እና በጣም ጥሩ ነገሮችን አከናውነናል፡፡ ብዙዎቻችንም ወንጌልን ለማሰራጨት ተግተናል፡፡ በተቻለ መጠን ሁሉ እግዚአብሔር ሰብአዊ ጥረቶቻችንን በእርግጥ ባርኮልናል፡፡ ነገር ግን አስፈላጊው ጥያቄ፤ <እኛ እነዚህን አገልግሎቶች እንደ መንፈሳዊ ወይስ እንደ *ሥጋዊ* ክርስቲያኖች ነው እያከናወንን ያለነው?> የሚለው ነው፡፡ አንድ ነገር እርግጥ ነው፤ *ሥጋን መሠረት* አድርገን መፍትሔዎችን ለማግኘት ስንታገል ጊዜአችንን በከንቱ እናባክናለን፡፡ ብዙ ተግባራትን እንፈጽማለን ግን ውጤታማ አንሆንም፡፡

## ያለፊተኛው ዝናብ የኋለኛው ዝናብ አይኖርም

"የፊተኛው ዝናብ፣ ማለትም በመንፈስ ቅዱስ መሞላት፣ መንፈሳዊ ብስለት እንዲኖረን ያደርጋል፡፡ ይህም ዝናብ፣ የኋለኛው ዝናብ ተጠቃሚዎች እንድንሆን ስለሚያደርገን ያስፈልገናል፡፡" (Dennis Smith, *40 Days – Prayer and Devotions to Revive Your Experience with God,* Book 2, (Vienna, 2013), p. 175)

"የምድርን መከር ለአጨዳ የሚያበቃው የኋለኛው ዝናብ ለሰው ልጅ ዳግም ምጻት (ለክርስቶስ ዳግም ምጻት) ቤተክርስቲያንን የሚያዘጋጃትን መንፈሳዊ ጸጋን ያመለክታል፡፡ ነገር ግን አስቀድሞ የፊተኛው ዝናብ ካልዘነበ በቀር ሕይወት አይኖርም፤ አረንጓዴውም ሀመልማል መብቀል አይችልም፡፡ የፊተኛው ዝናብ ሥራውን ካልሠራ በስተቀር የኋለኛው ዝናብ የትኛውንም ዘር ለመከር (ለአጨዳ) ሊያደርስ አይችልም" (E.G. White, *The Faith I live By,* (1958), p. 333.3)

## መንፈስ ቅዱስ እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቅድስና

"መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቅድስና በክርስቶስ በመታመንና በውስጣችን በሚያድረው የእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል ብቻ ነው የሚከናወነው" (E.G. White, *The Great Controversy,* (1911), p. 469.3)

## ታላቁ የወንጌል ስርጭት ሥራ ያለ መንፈስ ቅዱስ?

ታላላቅ ተቋማት፣ ውጤታማ የወንጌል መርሐ-ግብሮች እና የላቁ የወንጌል ስርጭት ስልቶች ያለመንፈስ ቅዱስ ሊዘጋጁ ይችላሉን? ወደ ደቡብ አፍሪካ የሄደው ታላቁ ሚስዮናዊ አንድሪው ሙሪ የሚከተለውን ሲጽፍ ይህ ሁናቴ ሊከሰት የሚችል እንደሆነ እና በክርስትናው ዓለም ውስጥ በብዙሃኑ ዘንድ በእርግጥም እውነታ መሆኑን ያውቅ ነበር፡-

*"ወንጌልን መስበክ ወይም መፃፍ እችል ይሆናል፣ ስለ ወንጌል ማሰብ ወይም ማሰላሰል እንዲሁም በእግዚአብሔር መጽሐፍ ውስጥ እና በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ባሉ ነገሮች በመጠመድ ደስታን አገኝ ይሆናል፤ ይህንንም ሁሉ ባደርግም፣ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ እጅግ የጎደለኝ ልሆን እችላለሁ፡፡ የሚያስፈራኝ ነገር ቢኖር በመላው የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያለውን የስብከት አገልግሎት ስንመለከት፣ <ለምንድን ነው በሚሰበከው ቃል ውስጥ እጅግ ጥቂት የሚለውጥ ኃይል ያለው?> <ሥራው ብዙ ሆኖ ሳለ ነገር ግን ሰዎችን ለዘለዓለም ድነት ለማብቃት ስኬታችን ለምን ጥቂት ሆነ?> < ምዕመናን በሙሉ መሰጠት እና በቅድስና እንዲኖሩ ለማድረግ ቃሉ ለምን ኃይል አነሰው?> ብለን ብንጠይቅ መልሳችን፡- < የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ያለመኖር ነው> የሚለው ነው፡፡ እንዲሁም <ሥጋዊነት> እና <በሰው አቅም/ጉልበት መተማመን> መንፈስ ቅዱስ መውሰድ የነበረበትን ስፍራ ስለወሰደ ነው ከሚለው መልስ በስተቀር ሌላ ምክንያት ሊኖር አይችልም (ገላ 3፡3)፡፡"* (Randy Maxwell, *If My People Pray* (Pacific Press 1995), p. 145)

## መንፈስ ቅዱስና ጤና

*"እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው።"* (ሮሜ 12፡1)

*"እናንተ ራሳችሁ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ፣ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውስጣችሁ እንደሚኖር አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፤ ያም ቤተ መቅደስ እናንተ ናችሁ።"* 1ኛ ቆሮንጦስ 3፡16-17

“ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።” ፲ኛ ቆሮንጦስ 6፡19-20፣ ዘጸአት. 15፡26

በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ሰዎች የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ናቸው፡፡ ይህ ለአንተ ሕይወት ምን አይነት ትርጉም እንዳለው ቆም ብለህ አስበህ ታውቃለህ? ቤተ-መቅደስ የእግዚአብሔር ማደሪያ ስፍራ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ አለው፤ “በመካከላቸውም አድር ዘንድ መቅደስ ይስሩልኝ”፡፡ ዘጸአት 25፡8

ይህንን እውነታ ከልባችን ብንቀበለው፣ ለጤናችን እና ለአኗኗር ዘይቤአችን ጥንቃቄ መውሰድ የደቀ-መዝሙርነታችን አንዱ ክፍል ይሆን ነበር፡፡ አካላችን የእግዚአብሔር ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ንብረት በጥንቃቄ ልትንከባከቡ ትፈልጋላችሁ? አዎን፣ አካላቶቻችንን በጥንቃቄ መንከባከብ እንፈልጋለን፣ ያውም እንደ እግዚአብሔር ትዕዛዛት መሠረት! ይህ ደግሞ በተወሰነ መልኩ የግል ዲሲፕሊን (ቁርጠኝነትን) ይጠይቃል፡፡ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው ይህንን ቁርጠኝነት በደስታ ሊተገብረው ይችላል፣ ይተገብረውማል፡፡ ለዚህም ሽልማቱ የአካል፣ የመንፈስና የነፍስ የተሻለ ጤንነት ማግኘት ነው፡፡ በአንጻሩ ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ያልተሞላ ሰው ይህ ቁርጠኝነት ስለሌለው ይቸገራል፣ በመሆኑም ይጎዳል፡፡ እርሱን እንድናከብር፣ እርሱን እንድናገለግል እንዲሁም ደስተኛ እንድንሆን ስለሚፈልግ አግዚአብሔር አካላችንን እና መንፈሳችንን በጤንነት እንድንይዝ ይፈልጋል (ከእኛ ይጠብቃል)፡፡ በዚህ ረገድ በመንፈስ ቅዱስ ከመሞላት በስተቀር ሌላ አማራጭ የለንም፡፡ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በእኛ ውስጥ ሲኖር እርሱ “ፈዋሽህ እግዚአብሔር ነው”(ዘጸአት 15፡26)፡፡ ፈውስ ለሚድነው ሰው ምንጊዜም ቢሆን የተሻለ ነገር ነው፣ ለእግዚአብሔርም ክብር ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሚከተለውን ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል፡- <ታላቁ ሐኪም ሁላችንንም ይፈውሳልን?>

“አንዲት በእድሜ ጠና ያለች ካምቦዲያዊት ሴት በአንድ ወቅት በታይላንድ ሃገር ወደ ሚገኝ የስደተኞች ጣቢያ ስደተኛ ሆና በስደተኞች ጣቢያ ውስጥ ወዳለው የክርስቲያን ሆስፒታል መጣች፡፡ የቡድሃ ሃይማኖትን የመነኩሴ ልብስ ለብሳ ነበር፡፡ <ዶክተር የሱስ> በተባለው ሐኪም ለመታከም እንደምትፈልግ ፍላጎቷን ገለፀች፡፡ ከዚያም የሆስፒታሉ ሠራተኞች ስለ ክርስቶስ

ነገሯት፡፡ እርሷም እምነቷን በየሱስ ላይ ጣለች፣ በአካልም በነፍስም ተፈወሰች፡፡ ወደሃገሯ ካምቦዲያ ከተመለሰች በኋላ 37 ሰዎችን ለክርስቶስ ለመማረክ ቻለች፡፡" (Author unknown, *Our Daily Bread – Worship book* (RBC Ministries), 26. Nov. 1993)

ታማኙ ንጉሥ ሕዝቅያስ በታመመ ጊዜ ጌታ መልዕክት ላከለት፡- "እነሆ እፈውስሃለሁ" (2ኛዜና 20፡1-10)፡፡ ነገር ግን ለምንድን ነው ጌታ ቃሉን ልኮ በመፈወስ ፋንታ የበለስን ጥፍጥፍ እንዲጠቀም ያዘዘው? ጌታ ተፈጥሮአዊ መድኃኒቶችን ወይም የአመጋገብ ስርዓት ለውጥን፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴን ወይም በቂ እረፍትን ወ.ዘ.ተ. እንድናደርግ የእኛን ተሳትፎ ይጠብቅ ይሆን? ለምነድን ነው ጌታ ጳውሎስን ያልፈወሰው? የ"ሥጋ መውጊያ" ከእርሱ ጋር እንዲሆን ለምን ተወው? ጳውሎስ ራሱ ሲናገር እንዲህ አለ፡- "በመገለጥ ታላቅነት እንዳልታበይ" (2ኛ ቆሮንጦስ 12፡7-10)፡፡ ቢሆንም ኤለን ኋይት እንዲህ ብላ ተናግራለች፡- "አንድ የታመመ ወንድ ወይም አንዲት የታመመች ሴት ሊቀበል/ልትቀበል የሚችለው/የምትችለው እጅግ ምርጡ መድኃኒት የእግዚአብሔር መንፈስ ተጽዕኖ (መሞላት) ነው፡፡ ሰማይ የሙሉ ጤናማነት ስፍራ ነው፤ የሰማይን ተጽዕኖ በጥልቀት ባስተዋልን ቁጥር የታመመው ሰው ጤንነት ማገገም ይበልጥ እርግጠኛ እየሆነ ይመጣል" (E.G. White, *Medical Ministries* (1932) p.12.3)

አንድ ነጋዴ እንዲህ በማለት የጻፈው ነገር አስገራሚና ጠቃሚ አይደለምን? ይህ ሰው ከዚህ በፊት የወሰዳቸው የጤና ትምህርቶች ምንም እንዳልጠቀሙት ተናገረ፡፡ ነገር ግን በየቀኑ ስለመንፈስ ቅዱስ መጸለይ ሲጀምር ሙሉ በሙሉ ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን ወደ መከተል እና የአትክልትና ፍራፍሬ ተዋዕጾ ብቻ ተመጋቢ ወደ መሆን ተቀየረ (Email from 7.3.2013)፡፡ ታዲያ ይህ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት፣ ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን በደስታ እንድንቀበል የሚያነቃቃና ኃይልን ሊሰጥ የሚችል እንደሆነ አያመላክትም?

የዚህን ነጋዴ ልምምድ ካነበበች በኋላ አንዲት እህት እንደዚህ ብላ ጻፈች፡- ሕይወቴን ሙሉ በሙሉ ለየሱስ በማስረከቤ እግዚአብሔር በአንድ ወር ውስጥ ሕይወቴን ሙሉ በሙሉ ለወጠው፡፡ ራሴን ለጌታ ያስረከብኩበትን ጸሎት ከፀለይኩ በኋላ በቀጣዩ ማለዳ ወደ ኩሽና ሄጄ በቡና ማፍያው ማሽን አጠገብ ቆሜ ራሴን አወዛወዝኩና እንዲህ አልኩ <በፍጹም! ከዛሬ በኋላ ቡና አልጠጣም!>፡፡ ከዚህ በፊት ይህንን ማድረግ የማይታሰብ ነበር፡፡ ምክኒያቱም ቡና

መጠጣትን ለማቆም በሞከርኩ ቁጥር ቡና ማቋረጤን ተከትሎ ከባድ የራስ ምታት ለአምስት ቀናት ያህል ይኖረኝ ነበር፡፡ አሁን ግን ይህንን ቁርጥ ውሳኔ ስወስን፣ ውሳኔዬ ምን አይነት መዘዝ ይዞብኝ እንደሚመጣ እንኳ አላሰብኩም፡፡ የማውቀው ነገር ቢኖር ከዚያ ወዲያ ቡና መጠጣት እንደማልፈልግ ብቻ ነው፡፡ እነሆ ዛሬ ለቡና ምንም አይነት ፍላጎት የለኝም" (Email from November 18, 2014 from Sister M.)፡፡ ይህ በእርሷ ሕይወት ከተደረጉ ለውጦች አንዱ ምሳሌ ነው፡፡ (ከሱስ ነጻ መውጣት ለሚፈልግ ሁሉ አልኮሆል እና ትንባሆን ድል ስለማድረግ 5ኛውን "Andreasbrief" የተሰኘውን ጽሁፍ እንድታነቡ እጋብዛለሁ፡፡ በጸሎት እና በእግዚአብሔር የተሰፉ ቃሎች የሚገኘውን ነጻ የመውጣት መንገድ በስፋት ያትታል (በጀርመንኛ ቋንቋ ብቻ የሚገኝ ነው) (Andreasbrief Nr.5, Sieg über Tabak und Alkohol, www.missionsbrief.de – Andreasbriefe. Man kann ihn auch beziehen bei Wertvoll leben, Adventist Book Center und TopLife – Wegweiser Verlag.)

**ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የሚመራ ሕይወት የአኗኗር ዘይቤ ተሐድሶ እንዲኖር በእጅጉ ያግዛል፡፡ ለውጥን ከሚያመጣው ኃይል ጋር ተጣምረው የሚመጡ ለጤናችን የሚጠቅሙ መረጃዎች ያስፈልጉናል፡፡**

ዶን ማኪንቶሽ በካሊፎርኒያ ዌይማር ኢንስቲትዩት የ Newstart Global መሪ እንደዚህ ይላሉ፡-

"በዘመናችን የጎደለን ነገር የጤና ትምህርት አይደለም፤ ስለጤና አጠባበቅ እጅግ በጣም ጥሩ መረጃዎች አሉን፡፡ የሚያስፈልገን ግን፣ ከጤና መረጃ ጋር የተጣመረ በተግባር ለማዋል የሚያስችል ኃይል ነው፡፡ ማለትም ለውጥን የሚያመጣ ኃይል፡፡" (Dave Fiedler, *D'Sozo,* (Remnant Publications), Forward)፡፡ ታዲያ ይህ የለውጥ ኃይል፣ የወንጌል ኃይል፣ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል አይደለምን?!

ዶክተር ቲም ሆው ሲናገሩ ደግሞ እንዲህ አሉ፡- "የጤና ትምህርት አገልግሎት፣ የጤናን ትምህርት በመስጠት ብቻ ላይ የተወሰነ አይደለም፡፡ ጤናማነትን ወይም አካላዊ ፈውስን ለመቀዳጀት የሚለውጠውን የእግዚአብሔርን ኃይል መለማመድ ያስፈልጋል፡፡" (Dave Fiedler, *D'Sozo*, (Remnant Publications), Forward)

በመጨረሻም ይህንን ጥያቄ ልጠይቅ እወዳለሁ፤ በእምነት የሚገኙ ፈውሶችስ? መንፈስ ቅዱስን ሳንሞላ እነዚህን ፈውሶች ልንጠባበቅ እንችላለን? (ማርቆስ 16፡17-18፣ ያዕቆብ 5፡14-16ን ይመልከቱ)፡፡

## ለየሱስ ዳግም ምጻት መዘጋጀት

በመንፈስ ቅዱስ በኩል ከየሱስ ጋር የሚኖረን ጥልቅ ሕብረት፣ ለየሱስ ዳግም ምጻት እንድንዘጋጅ በጣም ይረዳናል፡፡ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ክርስቶስ በእኔ ውስጥ ሲኖር ያን ጊዜ በእርግጥም በጸጋው የተዘጋጀሁ እሆናለሁ፡፡ ከዚህ በታች የተብራሩት ሶስት መንገዶች ይህንን ሃሳብ በዝርዝር ይገልፁልናል፡፡ *(ይህ በዴኒስ ስሚዝ በተጻፈው Spirit Baptism and Earth's Final Events በሚለው መጽሐፍ ውስጥ ስለዚህ ነጥብ በዝርዝሩ ተጠቅሷል)*

### (1) ከክርስቶስ ጋር የሚኖረን የግል ግንኙነት

ክርስቶስ እንዲህ አለ፡- "እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን፣ የላክኸውንም የሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት" (ዮሐንስ 17፡3)፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ***"ማወቅ"*** ሚለው ቃል በዘመናችን ቋንቋ ውስጥ ከምንጠቀመው ያለፈ ጥልቅ ትርጉም አለው፡፡ ሙሉ በሙሉ የሆነ፣ በፍቅር የተሞላ የእርስበርስ መሰጠት ማለት ነው፡፡ ይህ በመንፈስ ቅዱስ በተሞላ ሕይወት ውስጥ ብቻ የሚገኝ ነው፡፡ በሚከተለው ጥቅስ ውስጥ ይህ ሃሳብ ተገልጾ እናገኘዋለን፡-

"ከእግዚአብሔር ጋር ሕያው የሆነ ግንኙነት ሊኖረን ይገባናል፡፡ ከፍተኛ ወደሆነ መንፈሳዊ ደረጃ እንደርስ ዘንድ፣ በመንፈስ ቅዱስ በመሞላት ከላይ የሚላከውን ኃይል ልንለብስ ይገባናል፣ ምክንያቱም ከዚህ በቀር ሌላ ረዳት የለንምና" (E.G. White, *Review and Herald,* April 5, 1892)፡፡ በአስርቱ ቆነጃጅት ታሪክ ላይ የሱስ ለአምስቱ ሰነፎች እንደዚህ አላቸው 'አላውቃችሁም'፡፡ ምክንያቱ ምንድን ነበር? ዘይት ስላልነበራቸው ነው፡፡ ይህም የመንፈስ ቅዱስን እጦት የሚያመላክት ነው (ማቴዎስ 25፡1-13)፡፡

የሱስን የሰቀሉት ሰዎች የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ጠንቅቀው ያውቁ ነበር፣ ነገር ግን መጽሐፉን በተሳሳተ መንገድ ስለተረጎሙት (የተሳሳተ መረዳት ስለነበራቸው) ከየሱስ ጋር የግል ግንኙነት ለማድረግ ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡

እኛ በመጨረሻው ዘመን የምንኖር ትውልዶች ከመጨረሻው ዘመን ሁኔታዎችና ክስተቶች የተነሳ ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንደሚያስፈልገን እናውቃለን?

## (2) ጽድቅ በእምነት

በሶስቱ መላዕክት መልዕክት ውስጥ እግዚአብሔር ለሰብአዊው ዘር የሰጠው የመጨረሻው መልዕክት "የዘላለሙን ወንጌል" መስበክ (ማሰራጨት) ነው (ራዕይ 14፡6-7)፡፡ መላው ዓለም ሊሰማው የሚገባው የዚህ መልዕክት ዋናው ቁም ነገር ምንድን ነው? በጸጋ በክርስቶስ የሱስ ባለ እምነት ብቻ ስለሚገኘው ጽድቅ ነው (ኤፌሶን 2፡8-9)፡፡ ይህንን የመጨረሻ ዘመን መልዕክት በኃይል የሚሰብኩ ሁሉ የመልዕክቱን ኃይል ራሳቸው በግል ሊለማመዱ ይገባል፡፡ ኃጢአታቸውን ይቅር በሚልላቸውና ከኃጢአት ነፃ በሚያወጣቸው አዳኝ የሱስ ብቻ በመታመን የሚገኘውን ጽድቅ ሊያውቁና በግል ሕይወታቸው ሊለማመዱ ይገባል፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው የሱስ ክርስቶስ በእኛ ውስጥ ሆኖ መታዘዝ እንድንችል በሚያደርገን በመንፈስ ቅዱስ በተሞላ ሕይወት ነው፡፡ የሱስ በእኛ ሕይወት ውስጥ መኖሩ የሚገለጸው፣ ለሁሉም የእግዚአብሔር ሕጎች በመታዘዝ ነው፡፡ ዓለማችን የዚህ መልዕክት ብርሃን ነው የሚበራላት (ራዕይ 18፡1)፡፡

## (3) እውነትን መውደድ

እውነትን ለመውደድ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናት እና የተገለጠልንን እውነት በሕይወታችን ለመተግበር በመንፈስ ቅዱስ መሞላታችን ወይም አለመሞላታችን ምን አይነት ልዩነቶች ሊያመጡ ይችል ይሆን? 2ኛተሰ. 2፡10 እንዲህ ይላል፡- "ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉት"፡፡ ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ የማይመሩት፣ እነርሱ ከልባቸው እውነትን ስለሚወድዱ ነው፡፡ ታዲያ ይህንን መውደድ እንዴት ማግኘት እንችላለን? የሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ሙላት በውስጣችን ሲኖር ብቻ ነው እውነትን የምንወድበት ፍቅር ሊኖረን የሚችለው፡፡ ይህ ፍቅር ወደ ልባችን የሚመጣው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እንደሆነ ሮሜ 5፡5 ይነግረናል፡፡ ኤፌሶን 3፡17 ደግሞ፣ እኛ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በዚህ ፍቅር "ስር እንድምንሰድድና እንደምንመሠረት" ይነግረናል፡፡ በዮሐ. 16፡13 ላይ መንፈስ ቅዱስ "የእውነት መንፈስ" ተብሎ ተጠርቷል፡፡ ይህ በግልጽ የሚያሳየን፣ ለእውነት ፍቅር ይኖረን ዘንድ መንፈሳዊ ክርስቲያኖች መሆን አስፈላጊ እንደሆነ ነው፡፡ እውነትን የመውደድ፣ የእግዚአብሔር ቃልን

የመውደድ እንዲሁም የትንቢት ጽሁፎችን የመውደድ ችግሮች አሉን? የሚከተለውን ምክር በጥንቃቄ እናሰላስለው:- "ብዞዎችን በሃሰት ትምህርት ማርከው ካስቀሩት ኃይለኛ ማሳሳቻዎች ሊጠበቁ የሚችሉት ቅዱሳን መጽሐፍትን በትጋት የሚያጠኑት፣ እንዲሁም እውነትን የሚወዱት ብቻ ናቸው፡፡ የእግዚአብሔር ህዝቦች በስሜቶቻቸው ባለመመራት፣ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ብቻ በሚያስተማምን ሁኔታ ተመስርተዋልን?" (E.G. White, *The Great Controversy* (1911), p. 625.3)

እግዚአብሔር ሁሉንም እውነት መርምረን አውቀን እንደሆነ አይጠይቀንም ነገር ግን እውነትን መውደዳችንን ይጠይቀናል፡፡

## የመንፈስ ፍሬ ወይስ የሥጋ ሥራ

"የመንፈስ ቅዱስ ተጸዕኖ ውጤት የየሱስ ክርስቶስ ሕይወት በእኛ ውስጥ እንዲገለጽ ያደርጋል፡፡ ክርስቶስን አናየውም፣ ፊት ለፊትም አናናግረውምም፣ ነገር ግን የእርሱ መንፈስ ቅዱስ በሁሉም ስፍራ እኩል የቅርባችን ነው፡፡ ክርስቶስን በተቀበለ በማንኛውም ሰው ሁሉ በእርሱ ውስጥ እና በእርሱ በኩል መንፈስ ቅዱስ ይሠራል፡፡ **በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸውን የተረዱ ሁሉ፣ እነርሱ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ይታይባቸዋል፡፡**" (Editor Francis D. Nichol, *Adventist Bible Commentary* Vol. 6 (Hagerstown, 1980), p. 1112)

**ገላትያ 5፡22**:- ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት፡፡ **ኤፌሶን 5፡9**፡- ጽድቅ፤ እውነት፡፡

**ገላትያ 5፡16-21**፡- የኃጢአት ኃይል በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እንደሚሰበር ያሳየናል፡፡

"በመንፈስ ተመላለሱ **የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ**፡፡ *ሥጋ* በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፣ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም፡፡ **በመንፈስ ብትመሩ ግን ከህግ በታች አይደላችሁም** (ሮሜ 7፡23 እና 8፡13) ይመልከቱ፡፡ "የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው፣ እርሱም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣኦትን ማምለክ፣ ምዋርት፣ ጥል፣ ክርክር፣ ቅንዓት፣ ቁጣ፣ አድመኛነት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ ዘፋኝነት፣ ይህንም የሚመስል ነው፡፡ አስቀድሜም እንዳልሁ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርሱም፡፡" (ገላትያ 5፡16-21)

## መንፈሳዊ ስጦታዎች

"መንፈሳዊ ስጦታዎች በመንፈስ ቅዱስ ተሰጥተው በእርሱ እርዳታ የሚከናወኑ ስጦታዎች ናቸው፡- በ1ኛ ቆሮንጦስ 12፡28 እና ኤፌሶን 4፡11 ላይ እንደዚህ ተዘርዝረዋል፡- ሐዋሪያት፣ ነቢያት፣ ወንጌልን ሰባኪዎች፣ እረኞች፣ አስተማሪዎች፣ ተአምራት ማድረግ፣ መፈወስ፣ መርዳት፣ ማስተዳደር እና ልዩ ልዩ ልሳኖችን መናገር፣ መተርጎም፡፡ እነዚህ ስጦታዎች ቅዱሳንን ለወንጌል አገልግሎት ብቁ በማድረግ ጉልህ ሚና ይጫወታሉ" (Hrsg. Gerhard Rempel, *Schlüsselbegriffe adventistischer Glaubenslehre* (Hamburg), p. 44)፡፡ በተጨማሪም፣ መንፈስ ቅዱስ ሌሎች ስጦታዎችንም ለተለየ ዓላማ ይሰጣል፤ "በተለያዩ የሙያ ብቃቶች (ችሎታዎች)" (ዘጸአት 31፡ 2-6) ወይም የስነ-ህንጻ ጥበብ (1ኛ ዜና. 28፡12፣19)፡፡

እኛ የክርስቶስ ደቀ-መዛሙርት ስንሆን ያለንን ሁሉ እና ማንነታችንን ሁሉ ለእርሱ እናስረክባለን፡፡ ከዚህ የተነሳ በተፈጥሮም ሆነ በትምህርት ወይም ደግሞ በልምምድ ያገኘናቸው ችሎታዎቻችን እና መክሊቶቻችን ሁሉ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ይውላሉ፡፡ እግዚአብሔር ተጨማሪ መክሊቶችን ሊሰጠን ወይም ደግሞ ተፈጥሮአዊ ችሎታዎቻችንን ሊያጠራና ሊያዳብርልን ይችላል፡፡

የመንፈስ ቅዱስ እጦት እያለን መንፈሳዊ ስጦታዎች ሊኖሩን ይችላሉን?

## የእግዚአብሔር ምርጫ ወይስ የሰዎች?

ዓለምአቀፋዊ ቤተ-ክርስቲያናችን ዲሞክራሲያዊ አወቃቀር ነው ያላት፡፡ ቢሆንም ግን ቤተክርስቲያን በሰዎች እንድትመራ አይደለም የተቋቋመችው፡፡ <ዲሞክራሲ> ማለት ሕዝባዊ አመራር ማለት ነው፡፡ በተለያዩ የቤተክርስቲያን ምርጫዎች ላይ መሪዎችን በምንመርጥበት ጊዜ መራጩ የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምቶ በዚያ መሠረት ድምጹን መስጠት ነው መሆን ያለበት፡፡ መራጩ የእግዚአብሔርን ድምፅ በመስማቱ ምክንያት የእግዚአብሔር ፈቃድ በምርጫ ሂደቱ ይገለጻል፡፡ በርግጥ ማንኛውም የቤተክርስቲያን አመራር ምርጫ ስብሰባዎች ላይ እና በማንኛውንም የቦርድ ስብሰባ ላይ ድምፅ ከመስጠታችን በፊት እግዚአብሔር እንዴት እና ማንን መምረጥ እንዳለብን እንዲያሳየን ፀሎት እንደርጋለን፡፡ ነህምያ "አምላኬ በልቤ አደረገ" አለ (ነህምያ 7፡5)፡፡ ኤለን ኋይት ስለ ነህምያ ምዕራፍ 1 እንዲህ ትላለች፡- "ሲጸልይም

የተቀደሰ ዓላማ በውስጡ [በነህምያ መንፈስ ውስጥ] እየተቀረጸ ነበር”፡፡ (E.G. White, *Southern Watchman* (www.egwwritings.org), March 1, 1904)

*ሥጋዊ* ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ድምጽ ሊሰማ ይችላልን? በሙሉ ልቡ እና በፈቃዱ ራሱን ለእግዚአብሔር ካልተሰጠ በስተቀር ፈጽሞ መልስን ሊያገኝ አይችልም (መዝሙረ ዳዊት 66፡ 18 ፤ መዝ. 25፡12)፡፡ *ሥጋዊ* ክርስቲያን የሆነ አንድ ሰው ባለው እውቀት እና በተረዳው መሠረት በህሊናው ቢመርጥ በሰው አስተያየት ይህ መልካም ነው፡፡ ነገር ግን፣ ሰዎች እጃቸውን ጣልቃ አስገብተው በስውር ተነጋግረው ምርጫውን ካካሄዱ ግን ይህ ኃጢአት ነው፡፡

መሪዎች በእግዚአብሔር ሥራ ላይ ታላቅ ተጽዕኖ አላቸው፡፡ ለአገልግሎት በእግዚአብሔር በተጠሩ ወይም ደግሞ በሰው ጣልቃ ገብነት በተመረጡ ወንድምና እህት መሪዎች መካከል በርግጥ ትልቅ ልዩነት ያለው ሲሆን፣ ዋጋ የሚያስከፍል ሊሆን ይችላል፡፡

ስለ ጸሎት አስፈላጊነት የተጻፈ አንድ መጽሐፍ ሳነብ፣ የምንሄድበትን መንገድ እንዲመራን (እንዲያሳየን) እግዚአብሔርን መጠየቅ እንደምንችል አስተዋልኩ (መዝሙረ ዳዊት 32፡8)፡፡ ከዚያም በጽሞና የእግዚአብሔርን ድምፅ የመስማት ልምምዴ ሕይወቴን ሙሉ ለሙሉ ለወጠው፡፡ ስለዚህ ልምምዴ *“From Business Representative to Pastor”* (በጀርመንኛ ቋንቋ ብቻ የሚገኝ) (www.gotterfahren.info – Gott verändert Leben – Vom Prokurist zum Prediger) በተባለው ጽሁፍ መስክሬአለሁ፡፡ በተጨማሪም “ትክክለኛውን ውሳኔ እንዴት መወሰን እችላለሁ?” (በጀርመንኛ ቋንቋ ብቻ የሚገኝ) (www.gotterfahren.info – Wege zum Ziel: Gott erfahren – Gottes Botschaft für unsere Zeit – Thema Nr. 11) በሚል ርእስ በ*ኩርት ሀዝል* የተሰበከ ጥሩ ስብከት አለ፡፡ ከብዙ ጊዜያት በፊት በ*ሄነሪ ድረ ምንድ* “የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት ማወቅ እችላለሁ?” (በጀርመንኛና በእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቻ የሚገኝ) (Missionsbrief.de – Predigten lesen – Henry Drummond: Wie erkenne ich den Willen Gottes? (Deutsch und Englisch)) በሚል ርዕስ የተሰበከ ግሩም ስብከትም እንዲሁ ይገኛል፡፡

እ.ኤ.አ. በ2014 ዓ.ም የተፈጸመ አንድ ልምምድ ይህን ይመስላል፡- በኦስትሪያ ሀገር ካሪንቲያ ከተማ “Country Life Institute Austria” (TGM Training Institute) የተሰኘው የሚሽን ማዕከል የውሳኔ አጣብቂኝ ገጥሞት ነበር፡፡ <ተጨማሪ ህንጻ እንገንባ ወይስ አንገንባ?> ሕንጻውን ለመገንባትም ሆነ ላለመገንባት በቂ ምክንያቶች ነበሩን፡፡ ዋናው ጥያቄ በዚህ ጉዳይ ላይ <የእግዚአብሔር ፈቃድ ምንድን ነው?> የሚለው ነበር፡፡ በመገንባትና ባለመገንባት ዙሪያ በሰበሰብናቸው ምክንያቶች ላይ ማተኮርን ትተን፣ በጥቅምት 23 ላይ በምናደርገው የጸሎት ስብሰባችን ላይ መገንባት እንዳለብን ወይም እንደሌለብን እግዚአብሔር የእርሱን መልስ

እንዲሰጠን እና የእርሱን ድምጽ ለመስማት ዝግጁዎች ያደርገን ዘንድ ለአስር ቀናት ያህል በየቀኑ ጸለይን፡፡

በዚህ የጸሎት ስብሰባ ላይ ከ20 በላይ የሆኑ ተሳታፊዎች ተገኙ፡፡ የሕብረት ጸሎት ካደረግን በኋላ እያንዳንዱ ሰው መገንባት እንዳለበት ወይም እንደሌለበት በጥሞና እግዚአብሔርን በግሉ ጠየቀ፡፡ እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን መልስ ለተሳታፊዎች በዚህ መልክ ነው ያቀረበው፡- እያንዳንዱ ሰው በሚሰጠው ትንሽ ወረቀት ላይ፣ ሕንጻው መገንባት ካለበት፡- ይህንን ምልክት እንዲጽፍ "+"፣ መገንባት ከሌለበት ደግሞ "-" ፣ መልስ ከሌለው ደግሞ "0"፣ እንዲሁም በመልሱ የሚጠራጠር ካለ ደግሞ "?" እንዲጽፉ ተደረገ፡፡ ውጤቱ የእግዚአብሔርን አስደናቂ ምሪት የሚያመለክት ነበር፡፡ 14ቱ "+" (ከነዚህ አራቱ "+?") ነበሩ፣ 6ቱ ደግሞ "0" እና 4ቱ ደግሞ ምንም ያልተጻፈበት ንጹህ ወረቀት ነበር የመለሱት፡፡ (ግልጽ ምልክት ስለሌላቸው ያልተቆጠሩ 2 መልሶችም ነበሩ)፡፡ የእግዚአብሔር ምሪት እጅግ በግልጽ እንደሚያሳየው፣ ሕንጻው እንዲገነባ ወሰንን፡፡ በምንኖርበት በዚህ የመጨረሻ ዘመን የእግዚአብሔርን ምክር በቀጥታ መፈለግ (መጠየቅ) እንደሚገባን ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ነኝ።

ኢዮኤል. 2፡28-29 ስለዚህ ጉዳይ አስፈላጊነት ይነግረናል፡፡ ኤለን ኋይትም እንዲህ በማለት ጽፋልናለች፡- "እግዚአብሔር ለልባችን ሲናገረን፣ እያንዳንዳችን በግላችን ድምፁን ልናዳምጥ ይገባል፡፡ ሌላው ድምጽ ሁሉ ዝም ብሎ በጥሞና የእርሱን መልስ ስንጠባበቅ፣ በጸጥታ ውስጥ የእግዚአብሔርን ድምጽ የበለጠ ማዳመጥ እንችላለን፡፡ እርሱም "እረፉ እኔም አምላክ እንደሆንኩ እወቁ" ይለናል፡፡ (መዝ. 46፡10) (E.G. White, *The Desire of Ages* (1898), p. 363.3)

## ገንዘብ

በገንዘብ አጠቃቀም እንዲሁም ሃብትን በማካበት ረገድ በመንፈሳዊ እና በሥጋዊ ክርስቲያኖች መካከል ምን አይነት ልዩነቶች አሉ? ራሳችንን እንደ እግዚአብሔር ባለአደራዎች ነው ወይስ የሃብቶቻችን ባለቤቶች አድርገን ነው የምንመለከተው? "ገንዘብን መውደድ እና ከመጠን በላይ ያለፈ የዲታ (ሃብታማዊ) ኑሮ መውደድ ይህችን ዓለም የሌቦች እና የዘራፊዎች ዋሻ አድርጓታል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ከክርስቶስ ዳግም ምጻት በፊት ስስት እና ጭቀና እንደሚስፋፋ ይናገራል" (E.G. White, *Prophet and Kings* (1917), p. 651.1)፡፡

## የእግዚአብሔር ጥበቃ በሕይወታችን

የእግዚአብሔር መላዕክት እርሱን የሚፈሩ ሰዎችን ይጠብቃሉ፡፡ “የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል፣ ያድናቸውማል” (መዝሙረ ዳዊት 34፡7) “ለእያንዳንዱ የክርስቶስ ተከታይ ጠባቂ መልአክ ተመድቦለታል፡፡ እነዚህ ሰማያዊ ጠባቂዎች ጻድቃንን ከክፉ ኃያላት ይከልላሉ፡፡” (E.G. White, *The Great Controversy,* (1911), p. 512.2) እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች፣ የክርስቶስ ተከታዮች እና ጻድቃን በእግዚአብሔር ከለላ ስር ናቸው ስንል፣ ራሱን እንደ ክርስቲያን ለሚመለከት ሁሉ ይህ ተግባራዊ ይሆንለታል ማለታችን ነው? ሕይወታቸውን ሙሉ በሙሉ ለየሱስ ላላስረከቡት ሁሉ ይህ የሚሠራ ነውን? በእርግጥ ይህ ህጻናትን ይመለከታል፤ ምክንያቱም የሱስ በማቴዎስ 18፡10 ላይ “ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን እንዳትንቁ ተጠንቀቁ መላዕክቶቻቸው በሰማያት ዘወትር በሰማያት ያለውን የአባቴን ፊት ያያሉ እላችኋለሁና”ብሎ ተናግሯል፡፡ ሕይወቱን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር የሰጠው ዳዊት የሚፈራበትና የሚሰጋበት አንዳች ምክንያት እንደሌለው ያውቅ ነበር፡፡ “እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው፤ የሚያስፈራኝ ማን ነው? እግዚአብሔር የሕይወቴ መታመኛዋ ነው፤ የሚያስደነግጠኝ ማን ነው?” በማለት ምስክሯል (መዝሙረ ዳዊት 27፡1) ፡፡

(ስለ ቅዱሳን መላዕክት አገልግሎት <ታላቁ ተጋድሎ> በሚለው መጽሐፍ 31ኛውን ምዕራፍ እንድታነቡ አደፋፍራለሁ፡፡ ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ለሆነ ሁሉ ታላቅ ደስታን የሚሰጥ ነው)

## የመዝጊያ ሃሳቦች

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ያነሳናቸው ነጥቦች ጥቂቶቹን የሕወታችንን ክፍሎች ብቻ ነው፡፡ በእምነታችን እና በሕይወታችን ዙሪያ ልናነሳቸው ምንችላቸው ሌሎች ብዙ ጉዳዮች ይኖራሉ። ለሁሉም በሕይወት ለሚገጥሙን ነገሮች የሚከተለው ሃሳብ ገጣሚ ሆኖ እናገኘዋለን፡-

**በመንፈስ ቅዱስ ሙላት በመኖር እያንዳንዱ የሕይወት ክፍል የተሻለ ተጠቃሚ እንደሚሆን ተመልክተናል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ያለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት በምንኖረው ሕይወት ውስጥ በጽኑ እንደምንጎዳና ኪሳራ እንደሚደርስብን አይተናል፡፡ ታዲያ ይህ ለእኛ ሕይወታችንን**

**በየቀኑ ለእግዚአብሔር እያስረከብን በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት እንጠይቅ ዘንድ ታላቅ መነቃቃት አይሆነንምን?**

“ከተወሰኑ ዓመታት በፊት አንድ ቦይንግ 707 የሆነ አውሮፕላን ከቶክዮ (ጃፓን) ወደ ለንደን ለመብረር ተነሳ፡፡ አነሳሱ ያማረ ነበር፡፡ ንጹህ እና ፀሐያማ ቀን ነበር፡፡ ጥቂት እንደተጓዙም መንገደኞቹ <ፉጂ> የተባለውን ታዋቂውን የጃፓን ተራራ መመልከት ቻሉ፡፡ በዚያን ወቅት በድንገት ፓይለቱ በዚህ ተራራ ዙሪያ ከብ በመዞር መንገደኞቹ ይህንን ያልተለመደ ማራኪ እይታ እንዲመለከቱ የማድረግ ሃሳብ መጣለት፡፡

ከዚያም በበረራ ተቆጣጣሪዎች ከተመደበለት የጉዞ አቅጣጫ ወጥቶ ራሱ በመረጠው አቅጣጫ አውሮፕላኑን ማብረር ጀመረ፡፡ ፓይለቱ በቅርብ ርቀት ተራራውን ከበታቹ ተመለከተ። የከፍታ መለኪያው 4000 ሜትር ርቀት ላይ እንዳለ ያሳያል፡፡ ፓይለቱ ያልተመለከተው (ያላስተዋለው) ነገር ቢኖር በፉጂ ተራራ ዙሪያ የነበሩትን በመሬት ስበት ወደታች የሚወረወሩ ከባድ ነፋሳት እና ነፋሳቱ የፈጠሩትን ግፊት ነበር፡፡ ቦይንግ 707 እነዚህን ነፋሳት ፈጽሞ የሚቋቋም አይደለም፡፡ አውሮፕላኑ አየር ላይ ሳለ ተሰበረ ወድቆም ሁሉም መንገደኞች አለቁ፡፡ (Kalenderzettel February 17, 1979 by Reinhard Petrik)

ሥጋዊ ክርስቲያን ልክ እንደዚህ ፓይለት ራሱ በመረጠው አቅጣጫ የሚሄድ ነው፡፡ ውሳኔዎቹን ሁሉ በራሱ ነው የሚወስነው፡፡ ምንም ያህል ጥሩ ዓላማ ቢኖረውም፣ ይከሽፋል፡፡ መንፈሳዊ ክርስቲያን ግን ከአምላኩ ጋር አስተማማኝ እና በፍቅር በተሞላ ግንኙነት ወደ መልካም መዳረሻ በሚመራው በመንፈስ ቅዱስ አመራር ይኖራል፡፡

**ጸሎት፡-** በሰማይ ያለህ አባት ሆይ፣ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በውስጤ የሚኖረው የሱስ በሕይወቴ እና በአገልግሎቴ ላይ ስለሚያስከትለው መልካም ተፅዕኖ ከልቤ አመሰግንሃለሁ፡፡ የመንፈስ ቅዱስ አሠራርን እንዳስተውል የበለጠ ዓይኖቼን ከፈትልኝ፡፡ በመንፈስ ቅዱስ በኩል የሱስ ሊሰጠኝ የሚፈልገውን የተሟላ ሕይወት ስጠኝ፡፡ በሚቀጥለው ምዕራፍ ውስጥ ለዚህ ችግር መፍትሔ የሆነውን ቁልፍ እንዳስተውልና በተግባር እንዳውለው እርዳኝ፡፡ ከልብ አመሰግንሃለሁ! አሜን፡፡

# ምዕራፍ 5

# በተግባር ለማዋል የሚያስችል መፍትሔ

## እግዚአብሔር ለእኔ ያለውን መፍትሔ ልተገብር እና ልለማመድ የምችለው እንዴት ነው? በመንፈስ ቅዱስ እየተሞላሁ መሆኔን እርግጠኛ የምሆነው እንዴት ብጸልይ ነው?

### ጸሎት እና በመንፈስ ቅዱስ መሞላት

ይህንን ጉዞ በእምነት መጓዛችንና የመንፈስ ቅዱስ ሙላትን በእምነት መጠየቃችን አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት ከጸለይን በኋላ ጌታ ጸሎታችንን እንደመለሰ እና እየጠየቅነው በነረበት በዚያኑ ሰዓት የመንፈስ ቅዱስ ሙላትን እንደሰጠን ልናምን እና እርግጠኞች ልንሆን ያስፈልጋል፡፡

ገላትያ 3፡14 ፡- “የመንፈስን ተስፋ **በእምነት** እንድንቀበል” ይላል፡፡ በሌላ ትርጉም ደግሞ “እግዚአብሔር ቃል የገባውን የመንፈስ ቅዱስን ተስፋ በሙሉ **መተማመን** እንድንቀበል” ይላል፡፡

የሰማዩ አባታችንን በቀላሉ እንታመነው ዘንድ እግዚአብሔር አስፈላጊ ምክር ሰጥቶናል። ይህንንም ምክር “በተስፋ ቃሉ ተማምኖ (ታምኖ) መፀለይ” ብለን እንጠራዋለን፡፡

## በተስፋ ቃሎቹ ታምኖ መጸለይ

በቅድሚያ አንድ ጠቃሚ ምሳሌ እናንሳ፤ ልጄ በትምህርት ቤት ውስጥ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ጥናት ጎበዝ የሚባል አይደለም ብለን እናስብ፡፡ እኔም ልጄ እንግሊዘኛ ቋንቋን በርትቶ እንዲያጠና ላደፋፍረው ፈለግሁ፡፡ ከዚያም፣ በዓመቱ መጨረሻ ላይ ጥሩ ውጤት ካስመዘገበ 10 ዩሮ ከእኔ እንደሚቀበል ቃል ገባሁለት፡፡ ልጄም በርትቶ ማጥናት ጀመረ፡፡ እኔም እየረዳሁት ጥሩ ውጤት አስመዘገበ፡፡ ከዚያ በኋላስ? ልጄ ከትምህርት ቤት እንደመጣ፣ ገና በበሩ ሲገባ ድምጹን ከፍ አድርጎ “አባባ፣ 10 ዩሮ ስጠኝ!” በማለት ይጣራል፡፡ ልጄ 10 ዩሮ እንደሚያገኝ ለምን እርግጠኛ ሆነ? ቃል ተገብቶለት ስለነበር ነው፡፡ ለዚህም የሚያበቁትን ቅድመ መጠይቆቹን ሁሉ አሟልቶ ስለ ነበር ነው፡፡ ይህ ምሳሌ በብዙ ሰዎች ዘንድ የተለመደ ይመስለኛል፡፡

ነገር ግን በሰዓቱ ለልጄ የምሰጠው 10 ዩሮ ላይኖረኝ ይችላል፡፡ ይህ በእግዚአብሔር ዘንድ ሊሆን ይችላልን? እግዚአብሔር ራሱ ቃል የገባው ነገር ላይኖረው ይችል ይሆንን? በፍጹም!

ወይም ደግሞ ቃሌን አጥፌ “ልጄ ሆይ፡- በትምህርት ዙሪያ የተጻፈ አንድ መጽሐፍ ሳነብ ልጆችን ለገንዘብ ብለው እንዲያጠኑ ማድረግ ተገቢ እንዳልሆነ ስላነበብኩ 10 ዩሮውን ልሰጥህ አልችልም” ልለው እችላለሁ፡፡ እግዚአብሔርስ እንዲሁ ሃሳቡን ሚለውጥ አምላክ ነውን? በፍጹም!

ከዚህ የምንመለከተው፣ ከእግዚአብሔር የተሰጠን የተስፋ ቃል ኖሮን (ማለትም ቃል የተገባልን ነገር ኖሮ) ቅድመ መጠይቆቹን ካሟላን በኋላ አንድ አማራጭ ብቻ ነው ያለው፣ ይህም ቃል የገባልንን ነገር መቀበል ብቻ ነው፡፡

እግዚአብሔር ቃል የሚገባቸውን ነገሮች <**የተስፋ ቃሎች**> ብለን እንጠራቸዋለን፡፡ በተስፋ ቃሎቹ አማካኝነት እግዚአብሔር እኛን ወደ አንድ አቅጣጫ እንድንጓዝ ያደፋፍረናል፡፡ ማለትም፣ ሕይወታችን በእግዚአብሔር ኃይል የተመራ እንዲሆን የሚረዳንን የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ እንድንቀበል፡፡ እንዲሁም እርሱን በቀላሉ እንድንታመነው ያደርገናል፡፡ መታመን የእምነት ማዕከል ነው፡፡

በተስፋ ቃል ላይ ታመኖ መፀለይን በተመለከተ ከተጻፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ውስጥ አንዱ በ 1ኛ ዮሐንስ 5፡14-15 ላይ ይገኛል፡-

"በእርሱ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ **እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል**"

እግዚአብሔር እንደ ፈቃዱ የሆኑ ጸሎቶችን እንደሚመልስ በዚህ ጥቅስ ውስጥ ጠቅለል ባለ መልኩ ተስፋ ሰጥቶናል፡፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ በትእዛዛቶቹ እና በተስፋ ቃሎቹ ውስጥ ተገልጸዋል፡፡ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለሚፀልዩት ሁሉ ቁጥር 15 እንዲህ ይላል፡-

"የምንለምነውንም ሁሉ [እንደ እርሱ ፈቃድ] እንዲሰማልን **ብናውቅ ከእርሱ የለመንነውን ልመና እንደተቀበልን እናውቃለን**"

በሌላ ትርጉም ላይ እንዲህ ይላል፡- "ጌታ የጠየቅነውን እንደሚሰማ ካወቅን፣ **የጠየቅነውን በእጃችን እንደያዝን እናውቃለን**" ይህ ምን ማለት ነው? እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የጸለይነው ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ባቀረብነው በዚያኑ ሰዓት ተመልሷል ማለት ነው፡፡ ጸሎቶቻችን የሚመለሱት በእምነት እንጂ በስሜቶቻችን አይደለም፡፡

የሲጋራ እና የአልኮሆል ሱስ ካለባቸው ሰዎች ጋር ስጸልይ ይህንን ተምሬአለሁ፡- ነጻ ለመውጣት ፀሎት በሚፀልዩበት ጊዜ፣ በዚያኑ ሰዓት በርግጥ ነፃ ቢሆኑም አንድ ነገር መከሰቱን አያስተውሉም፡፡ መልሳቸውን በእምነት ይቀበላሉ፡፡ ነገር ግን ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ለሲጋራም ሆነ ለአልኮሆል ምንም አይነት ፍላጎት እንደሌላቸው ይገነዘባሉ፡፡ በዚህ ሰዓት (ማለትም ፍላጎት እንደሌላቸው በተገነዘቡበት ሰዓት) ፀሎታቸው እንደተሰማና ለፀሎታቸው መልስ እንዳገኙ ያረጋግጣሉ፡፡

በማርቆስ 11፡24 ላይ የሱስ ይህን ተናግሯል፡- "ስለዚህ እላችኋለሁ የጸለያችሁትን፣ የለመናችሁትንም ሁሉ **እንዳገኛችሁ** እመኑ፤ ይሆንላችሁማል፡፡"

ኤለን ኋይት ደግሞ እንደዚህ ትላለች፡- "ለተሰጡን በረከቶች ውጫዊ የሆነ ማረጋገጫን መፈለግ የለብንም፡፡ ስጦታው በተስፋ ቃሉ ውስጥ ነው፣ እናም እግዚአብሔር ቃል የገባውን ሊፈጽመው እንደሚችል እና ያ **ተቀብለን የያዝነው ስጦታችን እጅግ ባስፈለገን ሰዓት**

**እንደሚገለጥ** እርግጠኞች ሆነን ወደ ተግባራችን ልንሰማራ ይገባናል፡፡” (E.G. White, *Education* (1903), p. 258.2)

ስለዚህ ውጫዊ ማረጋገጫን ልንፈልግ አይገባም፡፡ ማለትም፣ ስሜታዊ የሆነ ልምምድ ማለቴ ነው፡፡ ሮጀር ጄ. ሞርኖ ይህንን ተናግሮ ነበር፡- “ክፉ መናፍስት፣ ሰዎች የክርስቶስን ቃልና የእርሱን ነቢያት ሳይሆን ስሜቶቻቸውን እንዲያደምጡ ያደፋፍራሉ፡፡ እነዚህ ክፉ መናፍስት፣ በስሜት የሚመላለሱት ሰዎች ሳያስተውሉ፣ የእነርሱን ሕይወት ሊቆጣጠሩ የሚችሉበት ከዚህ የተሻለ መንገድ የለም፡፡” (Roger J. Morneau, *A Trip into the Supernatural,* Review and Herald 1982, p. 43)

በተስፋ ቃሉ ታምኖ መጸለይ የእግዚአብሔርን ግምጃ ቤት ለእኛ ክፍት ያደርገዋል፡፡ አፍቃሪ ሰማያዊ አባታችን ተወስዶበት ሊጨረስ የማይቻል መዝገብን ለእኛ አዘጋጅቷል፡፡ “የክርስቶስ ደቀ-መዛሙርቶች በእርሱ የተስፋ ቃላቶች እምነት ካላቸው፣ ታላላቅ ነገሮችን ከእርሱ ሊጠባበቁ ይችላሉ፡፡” (E.G. White, *The Desire of Ages,* (1898), p. 668.1)

## ሁለት አይነት የተስፋ ቃሎች

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን የተስፋ ቃሎች በጥንቃቄ ልንለይ ይገባናል፡፡ “ለኃጢያት ይቅርታን ማግኘት፣ የክርስቶስን ጽድቅ መልበስ፣ የመንፈስ ቅዱስን ሙላት መቀበል፣ የመንፈስ ቅዱስ ባህሪያችንን የመለወጥና የእርሱን ሥራ ለመሥራት የሚያችል ኃይልን እንዲሰጠን መጠየቅ፤ እንደነዚህ ያሉ **መንፈሳዊ የተስፋ ቃሎች በየትኛውም ጊዜ ለሚያምኑ ሁሉ ሊሰጡ ዝግጁ የሆኑ** የተስፋ ቃሎች ናቸው (የሐዋርያት ሥራ 2፡38-39)፡፡ ነገር ግን ለጊዜያዊ በረከት የሚሰጡ የተስፋ ቃሎች፣ በዚህች ምድር በሕይወት መኖርን ጨምሮ፣ ለግላችን ወይም ለአገልግሎት የሚጠቅሙን ይሁን ወይም አይሁን ጠንቅቆ ስለሚያውቅ፣ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ጊዜን ጠብቀው ሊሰጡን ወይም ላይሰጡን የሚችሉ በረከቶች ናቸው፡፡”(Morris L. Venden, *95 Theses on Righteousness by Faith,* (Pacific Press 1987), p. 60)

ለምሳሌ ኢሳያይስ 43፡2 ፡- “በእሳት ውስጥ በሄድህ ጊዜ አትቃጠልም፣ ነበልባሉም አይፈጅህም”። እግዚአብሔር ይህንን ተስፋ በአስደናቂ ሁኔታ በእቶን እሳት ውስጥ ለነበሩት

ሶስቱ እስራኤላውያን ምርኮኞች ፈጽሞላቸው ነበር (ትንቢተ ዳንኤል 3)፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ *ሃስ* እና *ጀሮም* የተባሉት የኃይማኖት የተሃድሶ አራማጆች፣ ኮንስታንስ በሚባል ስፍራ ከግንድ ጋር ተጠፍረው በእሳት ተቃጥለዋል፡፡ ይህንን ታሪክ ስናስብ፣ <ጸሎቶቻቸው አልተሰሙም> እንል ይሆናል፡፡ የሆነ ሆኖ ግን እኛ በማናውቀው (በማናስተውለው) መንገድ ጸሎታቸው አልተመለሰምን? እንዴት? አንድ የጳጳሱ ጸሐፊ የነበረ ሰው ስለነዚህ ሰማዕታት ሞት እንዲህ በማለት ጽፎ ነበር፡- "በአሰቃቂ ሁኔታ በእሳት የሚቃጠሉበት የመጨረሻ ሰዓታቸው ሲቃረብ ሁለቱም በማያወላውል አዕምሮ ራሳቸውን አጽንተው ነበር፡፡ ወደ ሠርግ ግብዣ እንደሚሄዱ ያህል ራሳቸውን ለእሳት አዘጋጅተው ነበር፡፡ አንዳችም የህመም ለቅሶ አላሰሙም፡፡ የእሳት ነበልባሉ ሲንቦለቦል የውዳሴ መዝሙሮችን መዘመር ጀመሩ፤ የእሳቱ ንዳድ ዜማቸውን ሊያቆመው ፈጽሞ አልቻለም፡፡" (E.G. White, *The Great Controversy*, (1911), p. 109.3 Neander, "Kirchengeschichte", 6.Per., 2. Abschnitt, 2. Teil, §69; Hefele „Konziliengeschichte" Bd. VI, S.209 f)፡፡ አንድ ሰው በእሳት ሲቃጠል መጮሁ የማይቀር ነው፡፡ እነርሱ ያሳዩት ድርጊት ለእኛ በቀላሉ የምናስተውለው አይሁን እንጂ እግዚአብሔር በእርግጥም ጣልቃ ገብቶላቸዋል፡፡ ጊዜያዊ የተሰፋ ቃሎችም እንኳ ቢሆኑ ለእኛ ትልቅ ዋጋ እንዳላቸው ይህ ታሪክ ያሳየናል፡፡

## ለተመለሰልኝ የፀሎት ጥያቄ ማመስገን

ሌላም ከዚህ ጋር የተያያዘ አስፈላጊ ነጥብ አለ፡- በጠየቅነው በዚያኑ ሰዓት እግዚአብሔር የጠየቅነውን የሚመልስልን ከሆነ፣ በዚያኑ ሰዓት ለመልሱ እርሱን ማመስገን ተገቢ ነው፡፡ በዚህ ሰዓት የምናቀርበው ምሥጋና እግዚአብሔር ጸሎታችንን ስለመለሰ እና እጅግ ባስፈለገን ሰዓት ደግሞ በተግባር እንደሚፈጽመው በእርሱ ላይ ያለንን መተማመን የሚገልጽ ነው፡፡ አንዳንድ አማኞች ልክ ፀልየው እንደጨረሱ ወዲያውኑ ለውጥን ያያሉ፡፡ ብዙ አማኞች ግን የኤልያስ አይነት ልምምድ ነው ያላቸው፡- ጌታ በነፋሱ ውስጥ፣ በምድር መናወጥ ውስጥም እንዲሁም በእሳቱ ውስጥም አልነበረም፣ ነገር ግን በትንሽ የዝምታ፣ የለስላሳ ድምጽ ውስጥ ግን ነበረ፡፡ (1 ነገሥት 19፡11-12) ይህ የኔም ልምምድ ነበር፡፡

ከብዙ ጊዜ በኋላም እንኳ ምንም ለውጥ የተከናወነ አልመሰለኝም ነበር፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን እኔ ባልጠበቅሁት ጊዜ ብዙ ነገሮች እንደተከናወኑልኝ ማስተዋል ጀመርኩኝ፡፡

# አስተሳሰቤን መለወጥ

**የተከናወኑልኝን ለውጦች ማስተዋል በምጀምርበት ጊዜ፣ በዚያን ሰዓት አስተሳሰቤን መለወጥ ይኖርብኛል፡-** "... በልባችሁ መታደስ ተለወጡ. . ." (ሮሜ 12፡2)

በመቀጠልም፡- "ጸሎቴን ስለመለስክልኝ አመሰግንሃለው፣ ለጥያቄዬ መልስን ስለሰጠኸኝ አመሰግንሃለሁ፣ በትክክለኛው ጊዜና ሰዓት የልመናዬን መልስ በተግባር ስለምለማመደው አመሰግንሃለሁ" ማለት ተገቢ ነው፡፡

ይህንን ማድረግ ራስን በራስ ለማሳመን መሞከር ማለት አይደለም፡፡ ራሴን በራሴ ለማሳመን የምሞክር ከሆነ ራሴን ለማሳመን እያስገደድኩ ነው፡፡ ነገር ግን የተስፋ ቃሉን ተመርኩዤ ስፀልይ፣ ፀሎቴ በእምነት እንደተመለሰ ስለማውቅ ለአስተሳሰቤ መለወጥ አምላካዊ ድጋፍ አግኝቻለሁ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ፣ አስተሳሰቤን የማልለውጥ ከሆነ፣ በስሜት የምመራ መሆኔንና በእግዚአብሔር አለመታመኔን እያሳየሁ ነው ማለት ነው፡፡ በዚህ አይነት ባህሪዬ እግዚአብሔርን ሃሰተኛ እያደረግሁት ነው ማለት ነው፣ በመሆኑም ምንም አይነት መልስ ሳልቀበል እቀራለሁ ማለት ነው፡፡

ሌላው ነጥብ ደግሞ፣ ምንም አይነት ለውጥ ባላይም እንኳ፣ ይህንን አቋሜንም በተግባር ማሳየት አለብኝ፡፡ እግዚአብሔር ሁልጊዜ በእምነት እንድንመላለስ ይፈልጋል፡፡ በእርሱ እንድንታመን ይፈልጋል፡፡ የዮርዳኖስን ወንዝ ስለተሻገሩት የእስራኤል ህዝብ አስታውሱ፡፡ የዮርዳኖስ ወንዝ የተከፈለው ካህናቱ እግራቸውን ወደ ውሃው ካስገቡ በኋላ ነው፡፡ ንእማንም እንዲሁ ለምጹ ከመንጻቱ በፊት ሰባት ጊዜ በውሃው ውስጥ መስጠም ነበረበት፡፡

ምናልባት "እኔ ይህንን ማድረግ አልችልም" ትል ይሆናል፡፡ ነገር ግን እኛ የማናስተውላቸው ብዙ ነገሮች እንዳሉ መዘንጋት የለብንም፡፡ ሁላችንም ዕለት በዕለት የኤሌክትሪክ ኃይልን እየተጠቀምን ብንሆንም፣ ኤሌክትሪክ ምን እንደሆነ እስከዛሬ ድረስ አናውቅም፡፡ ሕጻናቶች እንዴት አድርገው መናገር እንደሚማሩም ማስረዳት አንችልም፣ ነገር ግን ሲናገሩ እናያለን፡፡ "በምንኖርበት ዓለም ውስጥ ከማስተዋል በላይ በሆኑ በብዙ ተአምራቶች ተከበን እያለን፣

በመንፈሳዊው ዓለም ውስጥ ስላሉት፣ ልናስተውላቸው ስለማንችላቸው ሚስጥሮች ለምን እንገረማለን?" (E.G. White, *Education* (1903), p. 170.1)

በመጽሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ 3፡5-6 ላይ የተጻፈውን እናስታውስ፡- "በፍፁም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፣ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ፣ በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ፣ እርሱም ጎዳናህን ያቀናልሃል፡፡" በዚህ ጥቅስ ውስጥ እግዚአብሔር የሰጠውን የተስፋ ቃል እንዲፈጸም እኛ አስቀድመን ማድረግ የሚገባንን ግልጽ መመሪያ እናገኛለን፡፡ እኛ አስቀድመን ልናደርጋቸው የሚገቡን ነገሮች እንድናሟላ እግዚአብሔር አዞናል፡፡ እርሱ ከእኛ የሚጠብቀውን ስለማድረጋችን እርግጠኛ ካልሆንን ደግሞ ፈቃደኞች እንዲያደርገን ልንፀልይ ይገባል፣ ለፀሎታችን ወዲያውኑ መልስ እንደሚሰጠን በመታመን፡፡ "ፈቃደኛ እንዲያደርጋችሁ ፈቃደኞች ከሆናችሁ፣ እግዚአብሔር ሥራችሁን ያከናውንላችኋል (ፈቃደኞች እንድትሆኑ ያደርጋችኋል)…" (E.G. White, *Thoughts from the Mount of Blessing* (1896), p. 142.1)

አንድ ሊረዳን የሚችል ተጨማሪ ሃሳብ፡- በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ላይ ተመርኩዘን ከፀለየን በኋላ፣ እርሱ ከእኛ የሚጠብቀውን ሁሉ ካደረግንም በኋላ ፀሎታችን አለመሰማቱን በመጠራጠር እግዚአብሔርን ሃሰተኛ እንዳናደርገው መጠንቀቅ አለብን፡፡ እርግጥ ነው፣ <እግዚአብሔር ሃሰተኛ ነው> ብለን መናገር በፍፁም አንፈልግም፡፡ ስለዚህ "ጌታ ሆይ፡- እታመንብሃለሁ፣ አለማመኔን አግዝ!" ብለን ልንፀልይ ይገባል፡፡ ከዚያ በኋላ በእርሱ ልንታመን ይገባናል!

**ኤለን ጂ. ኋይት በጻፈችው "ሥነ ትምህርት" በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ "እምነትና ፀሎት" በሚለው ምዕራፍ ውስጥ በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ላይ ተመርኩዞ ስለመጸለይ ጠቃሚ ምክሮችን በተጨማሪ እናገኛለን፡፡**

## በመንፈስ ቅዱስ እንድንሞላ መጸለይ

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ሃሳቦች የተከተልን ከሆነ፣ አሁን በሙሉ እምነት በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት መፀለይ እንችላለን። ነገር ግን ይህ እግዚአብሔር የኛን ፈቃድ እንዲያደርግ እርሱን ከማሳመን ጋር እንደማይገናኝ ልንገነዘብ ይገባናል፣ ይልቁንም በተስፋ ቃሎቹና በታማኝነቱ

በማመን ላይ የተመረኮዘ መሆኑን ልንረሳ አይገባም።

## መንፈስ ቅዱስን እንደምንቀበል የተሰጡን የተስፋ ቃሎች

ጌታ፣ መንፈስ ቅዱስን እንደምንቀበል ግሩም የተስፋ ቃሎችን ሰጥቶናል፡-

ሉቃስ 11፡13 "እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፥ **በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው**?"

በዚህ ጥቅስ ላይ የሰማይ አባታችን በጽኑ ቁርጠኝነት ቃል አልገባምን? በዚህ ግሩም የተስፋ ቃል ውስጥ ከእኛ የሚጠብቀው ነገር ቢኖር **መለመን**! ብቻ ነው። በዚህ ጥቅስ ውስጥ የሱስ፡- <አንድ ጊዜ ብቻ ለምኑ> እያለ ሳይሆን፣ <ያለማቋረጥ ለምኑ!> እያለ ነው።

ይሁን እንጂ አውዱን መመልከት ጠቃሚ ነው። ስለተመሳሳይ ነገር የሚናገሩ ሌሎች ጥቅሶችንም ማንበብ ይገባናል። ለምሳሌ ያህል፡-

**የሐዋርያት ሥራ 5፡32** *"እኛም ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን፥ ደግሞም እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ምስክር ነው።"*

በዚህ ስፍራ የቀረበው መስፈርት **መታዘዝ** ነው። በአንድ ጥቅስ ላይ ብቻ መደገፍ እንደሌለብን ይህ ጥቅስ ግልጽ ያደርግልናል። የተስፋ ቃሉ የተሰጠበትን አውድ በተጨማሪ ከግምት ውስጥ ማስገባት አለብን። ለመታዘዝ ለሚቀልለንን ነገር አንድ ጊዜ ብቻ መታዘዝ ማለት አይደለም። ይልቁንም አስደናቂውን አዳኛችንንና ወዳጃችንን ከመታዘዝ ጋር የሚያያዝ ጉዳይ ነው። መታዘዝ ደስታን ይፈጥራል። በየማለዳው ታዛዥ ልብ እንዲኖራችሁ ጸለዩ። እርሱ የሚፈልገውን ሁሉንም ነገር ማድረግ እንድትችሉ ፈቃደኛ እንዲያደርጋችሁና ያንንም በተግባር ማድረግ እንድትችሉ እንዲረዳችሁ ጸልዩ። በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ይህ በጥሩ ሁኔታ ቅድመ-መጠይቁን (መስፈርቱን) ያሟላል።

**ዮሐንስ 7፡37-39** *"ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ"*

ይህ ጥቅስ ደግሞ፣ መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል **ፍላጎትን ማሳየት** እንዳለብን ያሳየናል። ፍላጎት ከሌለህ አልያም ጥቂት እንዳለ የምታስብ ከሆነ ፍላጎት እንዲኖርህ ልትጸልይ ትችላለህ። ይህ እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ የምንጠይቀው ጥያቄ ሲሆን ወዲያውኑ በፍጥነት የሚመለስ ጥያቄ ነው። አስገራሚው አምላካችንን ስንጠይቀው በእኛ ውስጥ "መፈለግንና

ማድረግን” ይፈጥራል። ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖረን፣ በሙሉ ልባችን እንድንወድደው፣ በደስታ እንድናገለግለው፣ የሱስን የበለጠ እንድንወድደውና፣ ቶሎ ዳግም እንዲመለስ እንዲሁም በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ የመገኘት ፍላጎት እንዲኖረን፣ የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናትና ከእርሱም ጥልቅ እውቀትን ለማግኘት ፍላጎት እንዲያድርብን በተጨማሪም የጠፉትን ለመርዳትና ይድኑ ዘንድ ለማዳን የታጠቅን ለመሆን ፍላጎት እንዲኖረን ልንጸልይ እንችላለን።

**የዮሐንስ ወንጌል 7፡38-39** *“በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ፥ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ። ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ፤ የሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና”*

እዚህ ጥቅስ ውስጥ ያለው ቅድመ-መጠይቅ ደግሞ **እምነት** ነው! በዚህ ስፍራ መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል በየሱስ ክርስቶስ ላይ ያለን እምነት፤ ማለትም በእግዚአብሔር ማመናችን፣ እጅግ አስፈላጊ መስፈርት እንደሆነ እንመለከታለን። በተስፋ ቃሎቹ ታምነን በምንጸልይበት ጊዜ፣ እምነት ቀላል ነገር ይሆንልናል።

**ገላትያ 5፡16** *“ነገር ግን እላለሁ፥ በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ”*

በዚህ ጥቅስ ላይ የተሰጠው የተስፋ ቃል በትዕዛዝ መልኩ ነው የተጻፈው። እግዚአብሔር በመንፈስ እንድመላለስ የሚፈልግ ከሆነ፣ በመንፈስ ቅዱስ ሊሞላኝ ይፈልጋል ማለት ነው። በመንፈስ ቅዱስ ስንሞላ ደግሞ በሥጋ ፍላጎቶቻችን ቁጥጥር ስር እንደማንሆን ያሳየናል። በእኛ ውስጥ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ የኃጢአትን ኃይል ይሰብራል (ሮሜ 8፡1-17 በተለይም ቁጥር 2 አንብቡ)። በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት “የሥጋ ሥራ” ይገደላል (ሮሜ 8፡13)። ስለ ራሱ “በየቀኑ እሞታለሁ” ብሎ ስለተናገረው ስለ ጳውሎስ እስቲ አስቡ። ይህ የሚያሳየን፣ ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከጌታ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንደነበረው ነው፡፡ በሥጋ ሥራችን (ገላትያ 5፡18-21) ቁጥጥር ስር አለመሆንና ይልቁንም በመንፈስ ፍሬዎች (ገላትያ 5፡22) ማደግ ዋጋ ያለው ድንቅ ነገር ነው።

ኃጢያት ሕይወታችንን እንዳይወርስ የምናደርገውን ጥረት፣ አቅርቦ የሚያሳይ መነጽር በፋብሪካ ሲሠራ ካለው ሂደት ጋር ልናነፃፅረው እንችላለን:: ምንም ዓይነት አቧራ አጉሊ መነጽሩ ብርጭቆ ውስጥ እንዳይገባ ውስጡ በኃይለኛ የአየር ግፊት መሞላት አለበት።

ማለትም፣ የመነፅሩ መዝጊያ ሲከፈት አየር ወደ ውጭ ነው የሚወጣው። በዚያች ጊዜ የውጪ አቧራ ሊገባ አይችልም። በተመሳሳይ መልኩ እኛም በመንፈስ ቅዱስ ስንሞላ "*የሥጋን ፈቃድ ከቶ አንፈጽምም*"። ("ሰው መንፈሳዊ እንደሆነ መቆየት ይችላልን?" በሚለው ርዕስ ስር ተጨማሪ መረጃ ታገኛላችሁ:- ገጽ 106

**ኤፌሶን 3:16-17** *"በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት መጠን ይሰጣችሁ፤ የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ፥ ... እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ"*

***ኃይል*** የሚባለው ነገር ምን እንደሚመስል ላናውቅ እንችላለን። ይህን ለመረዳት ምናልባት ተፈጥሮ ጥሩ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል፡፡ በበጋ ወቅት ዛፎች እርቃናቸውን ሲሆኑ በክረምት ደግሞ ለምለም ናቸው። ዛፎቹ በሚለመልሙበት ወቅት እጅግ ብዙ ኃይሎች ውስጥ ለውስጥ (ሳይታዩ) ሥራቸውን ይሠራሉ። ነገር ግን እነዚህን ኃይሎች አናያቸውም ወይም አንሰማቸውም፤ ውጤቶቹን ግን እናያለን። በእኔም ሕይወት የእግዚአብሔር አሠራር እንደዚህ ነበር። ብዙ ኃይል የሰጠኝን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።

ሌላው ምሳሌ:- ከጥቂት አስርት ዓመታት ወዲህ በሰውነታችን ውስጥ የኤሌክትሪክ ኃይል እንዳለ አውቀናል (በጥናት ተረጋግጧል)። በሰውነታችን የኤሌክትሪክ ኃይል አለ፤ ነገር ግን ስለመኖሩ እኛ የምናየው የለንም።

**ኤፌሶን 5:18** *"መንፈስ ይሙላባችሁ ..." ወይም "**ያለማቋረጥና** በተደጋጋሚ እንደገና በመንፈስ **ተሞሉ**"* (Johannes Mager, *Auf den Spuren des Heiligen Geistes,* (Lüneburg, 1999), Seite 101)

**የሐዋርያት ሥራ 1:8** *"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ ... ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።"*

የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እስከሚመጣ ድረስ ደቀ-መዛሙርቱ እንዲጠብቁ ትዕዛዝ ተሰጧቸው የነበረ ቢሆንም፣ እንዲሁ ሥራ ፈት ሆነው አልጠበቁም። "በየዕለት ሕይወታቸው ሰዎችን ለመገናኘት ኃይል እንዲሰጣቸውና ኃጢአተኞችን ወደ ክርስቶስ ይመሩ ዘንድ ትክክለኛ ቃላቶች እንዲኖራቸው በትጋት ሲጸልዩ ነበር። ሁሉንም አለመግባባታቸውን እና ለስልጣን

ያላቸውን ጥማት ለመተው ፈቃደኞች ሆኑ።" (E. G. White, *The Acts of the Apostles,* p. 36-37) እኛም ቢሆን በዚህ የተስፋ ቃል ላይ ተመርኩዘን መንፈስ ቅዱስ እንዲወርድልን ልንጸልይ እንችላለን።

## በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ፀልዬ ካልተሳካስ...?

"አንድ ወጣት በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ስለፈለገ ምክር የሚሰጠውን ፓስተር ይፈልግ ነበር። በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ለረዥም ጊዜ ይታገል ነበር ነገር ግን አልተሳካለትም። ፓስተሩም 'ፈቃድህን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አስገዝተሃልን?' ሲል ጠየቀው። 'ሙሉ በሙሉ ያስገዛሁ አይመስለኝም' ብሎ መለሰ ወጣቱ፡፡ 'እንግዲህ ፈቃድህን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር እስካላስገዛህ ድረስ መጸለዩ [በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት መጸለዩ] ምንም ፋይዳ የለውም' አለው ፓስተሩ። 'ፈቃድህን ለእግዚአብሔር አሁኑኑ ማስገዛት ትፈልጋለህንን?' ብሎ ጠየቀው ፓስተሩ፡፡ 'አልችልም' በማለት መለሰ ወጣቱ። 'ይህንን እግዚአብሔር ላንተ እንዲያደርግልህስ ትፈቅዳለህን?' ብሎ ጠየቀው ፓስተሩ፡፡ 'አዎ' በማለት መለሰ ወጣቱ። 'እንግዲህ እንዲያደርግልህ ጠይቀው' አለው ፓስተሩ፡፡ ወጣቱም እንዲህ ብሎ ፀለየ፡- 'እግዚአብሔር ሆይ፥ ከገዛ ፈቃዴ ነፃ አድርገኝ፥ ፈቃዴን ሙሉ በሙሉ ባንተ ፈቃድ ስር እንዳደርግ እርዳኝ፥ ፈቃዴን ባንተ ፈቃድ ስር አስገዛልኝ፥ በየሱስ ስም እጸልያለሁ፣ አሜን'። ከዚያም ፓስተሩ እንዲህ ሲል ጠየቀው፡- 'መልስ አገኘህ?' 'ያገኘሁ ይመስለኛል፥ አንድን ነገር እንደ ፈቃዱ እግዚአብሔርን ጠይቄዋለሁ ስለዚህ ያ የፀለይኩትን ጥያቄ እንደመለሰልኝ አውቃለሁ (1ኛ ዮሐንስ መልዕክት 5፡14-15)። አዎን ሆኗል፥ ፈቃዴም ለእርሱ ተገዝቷል።' በማለት ወጣቱ መለሰ፡፡ ከዚያም ፓስተሩ 'አሁን ደግሞ ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት [በመንፈስ ቅዱስ ስለመሞላት] ጸልይ' አለው። ጸለየም 'እግዚአብሔር ሆይ በመንፈስ ቅዱስህ አጥምቀኝ፥ በየሱስ ስም እጸልያለሁ።' ፈቃዱን ለጌታ ስላስገዛ ወዲያውኑ ፀሎቱ ተመለሰ።" (Reuben A. Torrey, *Der Heilige Geist – Sein Wesen und Wirken* (Frankfurt, 1966), p. 150)

## በተስፋ ቃሎቹ ላይ ተመሥርቶ በመፀለይና ባለመፀለይ መካከል ያለው ታላቅ ልዩነት

ምንም እንኳን ለረዥም ጊዜያት በእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ላይ ታምኖ መፀለይ አስፈላጊ እንደሆነ ባውቅም፣ እንዲሁም በተለያዩ አጋጣሚዎች ይህንን ተሞክሮ በመጠቀም

ለጸሎቶቼ ግሩም ምላሾችን ብቀበልም፤ ለብዙ ዓመታት በነዚህ ልዩ የተስፋ ቃሎች ላይ ሳልደገፍ እንደው በደፈናው ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት ብፀልይም በቂ ነው ብዬ ሳስብ ቆይቻለሁ። ብዙ ክርስቲያኖችም ተመሳሳይ ሃሳብ እንዳላቸው አውቃለሁ። በርግጥ ይህ ሙሉ በሙሉ ስህተት ነው ማለት አልፈልግም። ነገር ግን የግል ተሞክሮዎቼን ወደኋላ ተመልሼ ሳሰላስል፣ በተስፋ ቃሎቹ ላይ ተመስርቼ ባለመፀለዬ ይጸጽተኛል። ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ግን ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት በተስፋ ቃሎቹ ላይ ታምኜ በየዕለቱ እየጸለይኩ እገኛለሁ፡፡ ፀሎቴን ከጨረስኩ በኋላም በዚያኑ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ እንደተሞላሁ እርግጠኝነት ይሰማኛል፡፡ እ.አ.አ. በጥቅምት 28፣ 2011 ዓ.ም. በተለማመድኩት አንድ ተሞክሮዬ አማካይነት በበፊት ሕይወቴና በአሁኑ ሕይወቴ መካከል ትልቅ ልዩነት እንዳለ ተገነዘብኩ።

በተስፋ ቃሎቹ ታምኜ መጸለይን ከጀመርኩ ወዲህ ከእግዚአብሔር ጋር ያለኝ ግንኙነት ይበልጥ የጠበቀ ሆኗል፤ የሱስ እጅግ የቅርብ ወዳጄ ሆኖአል። ይህ የግል ስሜታዊነትን የሚያንፀባርቅ ሃሳብ እንዳልሆነ በሚከተሉት ነጥቦች ለማረጋገጥ እፈልጋለሁ፡-

- መጽሐፍ ቅዱስን በማነብበት ጊዜ ብዙ አዳዲስና የሚያበረታቱ እይታዎችን (ሃሳቦችን) አገኛለሁ
- ከፈተና ጋር በማደርገው ትግል፣ ድልን እቀዳጃለሁ
- የጸሎት ሰዓት ለእኔ እጅግ የምወደውና የምናፍቀው ሰዓት ሆኖኛል፣ ታላቅ ደስታም ይሰጠኛል
- ብዙዎቹን ጸሎቶቼን እግዚአብሔር ይመልስልኛል
- ለሌሎች ስለ የሱስ አዳኝነት መመስከር ታላቅ ደስታ ይሰጠኛል፣ የበለጠ ድፍረትም አለኝ (የሐዋርያት ሥራ 4፡31)
- አብሬአቸው ከምኖረው ሰዎች ጋር ይበልጥ ተግባብቻለሁ፣ ይህም ያስደስተኛል
- በእግዚአብሔር ጸጋ አማካይነት በደስታ ሕይወቴን እኖራለሁ፤ በክንዶቹም ላይ ስለተደገፍኩ ሙሉ ዋስትና እንዳለኝ ይሰማኛል
- በአስቸጋሪ ጊዜያት እግዚአብሔር በአስገራሚ ሁኔታ ተሸክሞኛል፤ ውስጤንም አጠንክሮታል
- እግዚአብሔር ምን አይነት መንፈሳዊ (የጸጋ) ስጦታዎችን እንደሰጠኝ ተረድቻለሁ
- ሌሎችን መውቀስ ትቼአለሁ። ሰዎች ሌሎችን ሲወቅሱ ስሰማ ጥሩ ስሜት አይሰማኝም።

ይህ ሁሉ ለውጥ የመጣው ቀስ በቀስ ነበር። በመጽሐፍ ቅዱሳዊ የተስፋ ቃሎች ላይ ታምኜ ለተወሰነ ጊዜ ያህል ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት መጸለይ ከጀመርኩ በኋላ ነበር በሕይወቴ ለውጥ መኖሩን ልብ ያልኩት። ከዚያ ጊዜ አንስቶ የተለየ አይነት ክርስትና እየተለማመድኩ እገኛለሁ። ከዚህ ቀደም ከእግዚአብሔር ጋር የነበረኝ ሕይወት አድካሚና አሰልቺ የነበረ ሲሆን አሁን ግን ደስታንና ኃይልን እየተለማመድኩ እገኛለሁ።

በመንፈስ ቅዱስ ጉድለት ምክኒያት ከዚህ ቀደም በግል ሕይወቴ፣ በትዳሬ እንዲሁም በቤተሰቤና እንደ ፓስተር ሆኜ ባገለገልኩባቸው ቤተ-ክርስቲያናት ውስጥ ስለመጣው ኪሳራ አዝናለሁ። ይህንንም በተረዳሁ ጊዜ ጌታ የቀድሞው ሕይወቴን ስህተት ይቅር እንዲለኝ ከልቤ ጠየቅሁት።

እኛ እራሳችን እስከደረስንበት ደረጃ ድረስ እንጂ ከዚያ ደረጃ በላይ አሳልፈን ሌሎችን መምራት እንደማንችል ይህ ልምምድ የበለጠ ግልፅ ያደርገዋል። በተጨማሪም፣ በቤተሰብም ይሁን በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ክርስቲያኖች የግል ጉድለቶች፣ ችግሩን የበለጠ እንደሚያባብሱት መዘንጋት የለብንም።

ሌሎችም እንደ እኔ በሕይወታቸው ይህን ተመሳሳይ ስህተት በመስራት እንዳያዝኑና እንዳይቆጩ፣ ከዚህ በታች ያሉትን የተወሰኑ ሃሳቦችን ልጨምር፡-

በ2ተኛ ጴጥሮስ 1፡3-4 ከክርስቶስ ጋር ባለን የጠበቀ ግንኙነት አማካይነት *"... ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች... እንድትሆኑ... የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን"*እንደሰጠን ይናገራል።

ይህ ማለት፣ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠኝ በተስፋ ቃሎቹ አማካይነት ነው ማለት ነው። የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች፣ ከባንክ ቼክ ጋር ማመሳሰል ይቻላል። ከሂሳቡ ባለቤት እጅ የተፈረመበት ቼክ ሲሰጠን፣ ከዚያ የባንክ አካውንት ገንዘብ ማውጣት እንችላለን። እንዲሁም እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆንን (ዮሐንስ 1፡12) በክርስቶስ የተፈረሙ ቼኮችን (የተስፋ ቃሎችን) በየዕለቱ ማውጣት እንችላለን። በድንቅ አርቲስት የተሠሩ የሚያማምሩ ቼኮች ቢኖሩንም እንኳን፣ እነዚህን የራሳችንን ቼኮች ለባንክ ቤቱ ብናሳይ ምንም አይፈይድልንም። በሂሳቡ ባለቤት የተፈረመ ቼክ ነው በእጃችን ሊኖረን የሚገባን።

በተስፋ ቃሎቹ ታምነን እንድንጸልይ የሚያደፋፍረን ሌላም ምክኒያት አለ። ኃይል ያለው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ነው። የሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ፣ መዝሙረ ዳዊት ውስጥ በሚገኙ ቃላቶች ሦስት ጊዜ የጸለየው ለምን ነበር? ሰይጣን በምድረ በዳ በፈተነው ጊዜ የሱስ

በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ራሱን የተከላከለውና ሰይጣንን ያሸነፈው ለምንድ ነበር? (ማቴዎስ 4፡4፣ 7ና 10) እርሱም መልሶ፡- *"ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ **ቃል ሁሉ** እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል አለው።"*

ፈጣሪያችን የሱስ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ኃይል እንዳለ ያውቃል። "በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ባለው በእያንዳንዱ ትዕዛዝና በእያንዳንዱ የተስፋ ቃል ውስጥ ትዕዛዙን መተግበር እንድንችል የሚያግዝና የተስፋ ቃሎቹም እንዲፈፀሙ የሚያደርግ የእግዚአብሔር ኃይል አለ" (E.G. White, *Christ's Object Lessons* (1900), p. 38.2)፡፡ ይህ እንዴት ያለ ግሩም አይነት አገላለፅ ነው! በእያንዳንዱ የተስፋ ቃል ውስጥ፣ የእግዚአብሔር ኃይል አለ። በተስፋ ቃሎቹ ታምነን ስንጸልይ በጸሎታችን ውስጥ የእግዚአብሔርን ቃል በመጥቀስ እንጠቀም። ስለ እግዚአብሔር ቃል እንዲህ ተፅፏል፡- "ከአፌ የሚወጣ ቃሌ እንዲሁ ይሆናል የምሻውን ያደርጋል የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም።" (ኢሳይያስ 55:11)

እኔ በበኩሌ በተስፋ ቃሎቹ ላይ ብቻ ታምኜ እነርሱንም እየጠቀስኩ ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት ለመጸለይ አቅጃለሁ። በ1ኛ ዮሐንስ መልዕክት 5፡15 ላይ *"የምንለምነውንም ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ **ከእርሱ የለመነውን ልመና እንደ ተቀበልን እናውቃለን።"*** የሚል ተስፋ ስለሰጠን፣ የተስፋ ቃሎቹን ታምኜ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት ስፀልይ በዚያ ጊዜ እንደተሞላሁ አውቃለሁ። የተስፋ ቃሎቹን እየጠቀስኩ ካልፀለይኩ፣ መመለሱን በደፈናው በተስፋ ነው የምጠብቀው። በምሽት የፀሎት ጊዜያችን ላይ በቀን ውሎአችን ስላልተሳኩት ነገሮች እያሰብን በማጉረምረም ፈንታ፣ የተስፋ ቃሎቹን እየጠቀስን በእነርሱም ታምነን እግዚአብሔር ቀኑን እንዲባርክልን ለመፀለይ ማለዳ በቂ ጊዜ ብንወስድ ይሻላል።

በታላቅ ደስታ ተሞልቶ የተጻፈ አንድ ኢ-ሜል ደርሶኝ ነበር፡- "በቀን ውሎዬ ሁሉ እግዚአብሔር እንዲመራኝ የገዛ ቃላቶቼን ተጠቅሜ በመጸለይ እና በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ባሉ የተስፋ ቃሎች ላይ ተመርኩዤ በመጸለይ መካከል ሰፊ ልዩነት ይኖራል ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር። በርግጥ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ከዚህ በፊትም ለእኔ በጣም ጠቃሚ ነበሩ። በእነርሱም ሁሌ እታመን ነበር፣ ነገር ግን በየዕለቱ የእኔ እንዲሆኑ (በየቀኑ በሕይወቴ ተግባራዊ እንዲሆኑ) በፀሎቶቼ ውስጥ አላካትታቸውም ነበር። አሁን ግን፣ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች እየጠቀስኩ እና በእነርሱ ተማምኜ ስጸልይ ከየሱስ ጋር ያለኝ ሕይወት የጠበቀ፣ ይበልጥ

በደስታ የተሞላ፣ ይበልጥ እርግጠኝነት የተሞላበትና የተረጋጋ የመሆንን አቅጣጫ ይዟል። እግዚአብሔርን ስለዚህ ልምምዴ አመሰግነዋለሁ።" (Email to H. Haubeil C.S.)

በዚህም ምክኒያት ነው እንዴት በተስፋ ቃሎቹ ታምኖ እና እነርሱን እየጠቀሱ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት መጸለይ እንደሚቻል የሚያሳይ ከዚህ በታች ያለውን ሞዴል ፀሎት በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ለማካተት የወሰንኩት። በርግጥ ፀሎቱ መርዘም የለበትም፣ ማሳጠር ይቻላል። የእግዚአብሔርን ቃል በመጥቀስ በራሳችን አገላለጽ መጸለይን መለማመድ አስፈላጊ ነው። ነገር ግን ወሳኙ ነጥብ፥ እምነታችን የሚጠነከረው በተስፋ ቃሎቹ ታምነን ከጸለይን በኋላ መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበልን እርግጠኞች መሆናችን ነው። በመንፈስ ቅዱስ የምንሞላው ፀሎታችንን እግዚአብሔር እንደመለሰልን ስናምን ነው።

## በተስፋ ቃሎቹ ላይ ተመሥርቶ፣ በእነርሱም ታምኖ

## ዕለት ተዕለት በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት የሚቀርብ ሞዴል ፀሎት

በሰማይ ያለህ አባት ሆይ፡- በአዳኛችን በክርስቶስ የሱስ ስም ወዳንተ እመጣለሁ። "ልብህን ስጠኝ" (ምሳሌ 23፡26) ስላልከኝ፣ እነሆ በሆንኩትና ባለኝ ነገር ሁሉ በዚህች ደቂቃ ራሴን ዛሬ ላንተ አስረክባለሁ። እንደ ፈቃድህ ከጸለይን፣ የለመንነውን እንደ ተቀበልን ቃልህ ያረጋግጥልናል (1ኛ ዮሐንስ 5፡15) ስለዚህ፣ እንደ ፈቃድህ ይህን ጸሎቴን ስለመለስክ አመሰግንሃለሁ። በተጨማሪ፣ "ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም" ብለሃል (ዮሐንስ 6፡37) ።

"እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችችሁ፥ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስ ይስጣቸው?" ብሎ የሱስ ተናግሯል (ሉቃስ 11፡13)፡፡ አንተም እንደዚሁ፡- "ባንተ ለሚያምኑ (ዮሐንስ 7:38-39)፣ ላንተ ለሚታዘዙ (የሐዋርያት ሥራ 5፡32)፣ በየዕለቱ በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ራሳቸውን ላንተ ለሚሰጡ (ኤፌሶን 5፡18) እና በመንፈስ ለሚራመዱ (ለሚኖሩ) (ገላትያ 5፡16) ሁሉ መንፈስ ቅዱስን እሰጣለሁ" ብለህ ተናግረሃል። የእኔም ምኞት ይህ ነው። እባክህ፡- ይህ የተስፋ ቃልህ በእኔ ሕይወት ውስጥ እንዲፈጸም አድርግ። ለዛሬ የሚሆነኝን (የሚያፈልገኝን) የመንፈስ ቅዱስ ሙላት እንድትሰጠኝ ከልቤ እጠይቅሃለሁ። ይህ እንደፈቃድህ መሠረት የቀረበ ልመና ስለሆነ አሁኑኑ መንፈስ ቅዱስን ስለሰጠኸኝ አመሰግናለሁ (1ኛ ዮሐንስ 5፡15)። ከመንፈስ ቅዱስ ሙላት ጋርም አያይዘህ የሰጠኸኝን አምላካዊ ፍቅርህን ስለተቀበልኩም አመሰግናለሁ፣ ምክኒያቱም ቃልህ "በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም" ይላልና (ሮሜ 5፡5ና ኤፌሶን 3፡17)። ከባለ መዝሙረኛው ጋር "አቤቱ ጉልበቴ ሆይ፥ እወድድሃለሁ" (መዝሙረ ዳዊት 18:1) ማለት ፈልጋለሁ። ከሰጠኸኝ ከአንተ ፍቅር የተነሳ አብረውኝ የሚኖሩትን ሰዎች መውደድ ስለቻልኩም አመሰግንሃለሁ።

በእኔ ውስጥ ሰልጥኖ የነበረ የኃጢአት ኃይል በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ስለተሰበረ አመሰግናለሁ (ሮሜ 8፡13፣ ገላትያ 5፡16)። ዛሬም ከኃጢአትና ከዓለማዊ ምኞት ከልለኝ፣ አድነኝ፣ ከወደቁት መላዕክት ተፅዕኖ ከልለኝ፣ ከፈተናዎች ከልለኝ፣ ከአሮጌው ኃጢአተኛ ተፈጥሮዬ ነጥቀህ አውጣኝ፣ አድነኝ (1ኛ ዮሐንስ 5፡18)። በቃልና በተግባር ምስክርህ እንድሆን እባክህ እርዳኝ (የሐዋርያት ሥራ 1፡8)። ጸሎቴንም ስለሰማህ ከፍ አደርግሃለሁ፣ አመሰግንሃለሁ። አሜን።

የሱስ ራሱ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በውስጣችን ሊኖር ይፈልጋል (1ኛ ዮሐንስ 3፡24፣ ዮሐንስ 14፡23)። ኤለን ኋይት እንዲህ ብላ ጽፋለች፡- “በአማኙ ሕይወት ውስጥ ሆኖ የሚሠራው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል፣ በአማኙ ውስጥ ያለው የክርስቶስ ሕይወት ነው” (Editor Francis D. Nichol, *Adventist Bible Commentary* Vol. 6 (Hagerstown, 1980), p. 1112)። ጴጥሮስን፣ ጳውሎስንና ሌሎች ብዙዎችን የለወጠው ኃይል ለኛም ተሰጥቶናል። *“በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነከሩ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት መጠን ይስጣችሁ ...”* በማለት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለእኛም እንደተሰጠን በተጨማሪ ያረጋግጥልናል (ኤፌሶን 3፡16)።

ደስተኛ፣ ኃይልና ፍቅር የተሞላበትን ክርስትናን ለመኖር፣ እንዲሁም በኃጢአት ላይ ድል የተቀናጀ ሕይወት ለመኖር፣ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ቁልፍ ነገር ነው። “...የጌታም መንፈስ ባለበት በዚያ አርነት አለ” (2ኛ ቆሮንጦስ 3:17)

ከእለታት አንድ ቀን በደረሰኝ አንድ የኢ-ሜል መልዕክት ላይ እንዲህ ተጽፏል፡- “ብዙ የቤተ ክርስቲያን አባላት ሁለት ሁለት ሆነን ይህንን ሞዴል ፀሎት ተከትለን እየፀለይን ነው። እኔ ላለፉት አምስት ወራት ያህል ከአንዲት ጓደኛዬ ጋር ሆኜ በዚህ መልኩ እጸልይ ነበር። ከዚያን ጊዜ ወዲህ ያየሁት ለውጥ በግል ጉዳዮቼ ዙሪያ ብቻ ሳይሆን፤ በቤቴ፣ ከሰዎች ጋር በነበረኝ ግንኙነት፣ በትዳር ሕይወቴ፣ በመንፈሳዊ ሕይወቴና በቤተ-ክርስቲያን ሕይወቴ ነበር ለውጥን ያስተዋልኩት፡፡ አላስፈላጊ አለመግባባቶችና ግጭቶች ሊፈጠር በሚችልበት መልኩ ሳይሆን ይልቁንም ለውጡ የሆነው በረጋና በቀላል መንገድ ነበር። የእግዚአብሔርን ቅርብነት በይበልጥ ከተለማመድን ወዲህ ሕይወታችንን ቀለል ያደረገልንን እና ሕይወታችንን ያስተካከልንበትን የእግዚአብሔርን አመራር ስንመለከት ተገረምን።” (Email to Helmut Haubeil: E.S.)

## ሰው መንፈሳዊ እንደሆነ መቆየት ይችላልን?

አዎ! የአለማመን አስተሳሰብ እንዲያድግ ሳንፈቅድ ስንቀርና በመንፈሳዊ አየር መተንፈስ ስንጀምር ይህ ይሆናል፡፡ ኃጢአታችንን በመናዘዝ “ወደ ውጭ ስንተነፍስ”፣ የእግዚአብሔርን ፍቅርና ይቅር ባይነትን ለመቀበል “ወደ ውስጥ አየር ስንስብ” እንዲሁም የእምነት ጸሎትን በመፀለይ በየቀኑ በመንፈስ ቅዱስ ስንሞላ፣ መንፈሳዊ ክርስቲያኖች እንደሆንን መቆየት እንችላለን። (Helmut Haubeil & Gerhard Padderatz, *Gott, Geld & Glaube* (Eckental, 2009), p. 97)

ይህንን ልምምድ ልክ ከልጆቻችን ጋር ካለን ግንኙነት ጋር ማነፃፀር እንችላለን። ልጃችን አልታዘዘም ቢልም እንኳ ያኔም ልጃችን እንደሆነ ይቆያል። ነገር ግን በግንኙነታችን መካከል ክፍተት እንዳለ ይሰማናል። ልጃችን ከሠራው ስህተት የተነሳ ዓይናችንን ለማየት አይደፍር ይሆናል፣ ቢሆንም ይህ ክፍተት መስተካከል የሚችለው በኑዛዜ ብቻ ነው።

አንድ ክርስቲያን ለረዥም ጊዜ ያህል እንደገና ሥጋዊ ሊሆን ይችላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ፡- "አንዴ የዳነ ፤ ሁልጊዜ እንደዳነ ይቆያል" የሚለውን አስተምሮ አናገኝም። ኃጢአተኛ ተፈጥሮአችን አሁንም ቢሆን አለ። "ሐዋሪያትም ሆኑ ነብያት፣ ማናቸውም ከኃጢአት ነጻ ነን ብለው ተናግረው አያውቁም"። (E.G. White, *The Acts of the Apostles* (1911), p. 561.1)

ነገር ግን ከመንፈስ ቅዱስና ከየሱስ ጋር በሚኖረን ሕይወት አማካይነት፤ በልቦቻችን ውስጥ ያለ የኃጢአት ኃይል ስለሚሰበር፣ ደስተኛና ጠንካራ የክርስትና ሕይወት ይኖረናል። ጽድቃችን *"... ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ጽድቅ ቅድስናም ቤዛነትም..."* (1ኛ ቆሮንጦስ 1:30-31) ባገኘነው በየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው።

ለረዥም ጊዜ ያህል መንፈሳዊ ሕይወትን ቸል በማለት ወይም ደግሞ መንፈሳዊ አየርን መተንፈስ በማቆም እንደገና ሥጋዊያን ብንሆንም፣ ርህሩህ የሆነው ተቤዢአችን (አዳኛችን) እጁን ዘርግቶ እየጠበቀን እንደሆነ አንዘንጋ።

በእግዚአብሔር ጸጋ እንደገና የምንታደስበትንና መንፈሳዊ ሕይወትን እንደገና መኖር የምንጀምርበትን መንገድ ማወቅ አስፈላጊ ነው። ማንም ሥጋዊ ሆኖ መቅረት የለበትም።

የግል ሕይወታችንንም ሆነ የቤተክርስቲያን ሕይወታችንን በተመለከተ ራንዲ ማክስዌል የተናገረውን እናስተውል፡- "የእግዚአብሔርን ቤተ-ክርስቲያን ከመንፈሳዊ ሞት እንደገና እንድትነቃ ለማድረግ ምንም ጥረት ማድረግ የማያስፈልግ ይመስላችኋልን?" (Randy Maxwell, *If My People Pray* (Pacific Press,1995), p. 158)

በምድር ለተሰጠን ለተትረፈረፈው ሕይወትና ወደፊት ለሚጠብቀን የዘላለም ሕይወት፣ ለብዙ ሰዎች መዳንና ለየሱስ ታላቅ መስዋዕትነት ለምንሰጠው ምሥጋና፣ ተገቢውን ጥረት ማድረግ ያዋጣል። ከምናደርገው ጥረት መካከል አንዱና ወሳኙ ነገር ለአምልኮ በማለዳ ተነስተን ከጌታችን ጋር በጸሎት መገናኘት ነው። በኃይል የሚያስታጥቀን በዚህ ስፍራ ስለሆነ።

ስለ ሐዋሪያው ዮሐንስ የሚከተለውን እናነባለን፡-

"ለጌታው በነበረው ታላቅ ፍቅር፣ ራስን ማየት እስከማቆም ድረስ ልቡ በየዕለቱ ወደ ክርስቶስ ይሳብ ነበር። የኩራትና የኃይለኝነት ባህሪው፣ ባህሪን በሚያስተካክለው የክርስቶስ ኃይል ተለወጠ። እንደገና የሚያድሰው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል አዲስ ልብ ሰጠው። የክርስቶስ የፍቅሩ ኃይል ሙሉ በሙሉ የባህሪ ለውጥን ሰጠው። ከየሱስ ጋር የመኖር ሕብረት ውጤት ይህ ነው። ክርስቶስ በልባችን ውስጥ ሲኖር መላው ማንነታችን ይለወጣል። (E.G. White, *Steps to Christ* (1892), p. 73.1)

ጌታ ሆይ፡- *"ዓይኖቼን ክፈት፥ ከሕግህም ተኣምራትህን አያለሁ"* ... *"ብዙ ምርኮ እንዳገኘ ሰው፣ እኔም በቃልህ ደስ አለኝ"* (መዝሙረ ዳዊት 119:18 ፣ መዝሙረ ዳዊት 119:162)፡፡ እየመራኸኝ ስላለህ አመሰግንሃለሁ፡፡

## ምዕራፍ 6

# በመንፈስ ቅዱስ ሙላት ዙሪያ የተከሰቱ ልምምዶች (ምስክርነቶች)

*የግል ፣ የሰበካ እና የዩኒየን ቢሮዎች ምስክርነቶች*

### የአንድ ወንድም ምስክርነት

“ካለፉት ሁለት ዓመታት ጀምሮ በየዕለቱ በመንፈስ ቅዱስ እንድሞላ እፀልያለሁ። ልመናዬም የሱስ በየቀኑ በሙላት በእኔ ውስጥ ይኖር ዘንድ ነው። ይህንን አይነት የፀሎት ሕይወት በጀመርኩበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረኝ አካሄድ የሚያስደንቅ ነበር። የሱስ በእኔ ውስጥ እንዲኖር፣ ፈቃዱን በእኔ ሕይወት እንዲያደርግና በመንፈስ ቅዱስ በየዕለቱ እንዲሞላኝ መጠየቅ ከጀመርኩ ወዲህ በገላትያ 5 ላይ የተጻፉት የመንፈስ ፍሬዎች በሕይወቴ ጎላ ብለው መታየት ጀምረዋል። መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ያስደስተኛል፣ ስለ ክርስቶስ ለሌሎች መመስከር እጅግ ታላቅ ደስታ ይሰጠኛል። ለሌሎች ሰዎች ለመፀለይ ብርቱ ፍላጎት አለኝ። በተጨማሪም በአስደናቂ ሁኔታ የአኗኗር ዘይቤዬ ተለውጧል። ይህ ሁሉ እግዚአብሔርን በየዕለቱ በመፈለጌንና በየዕለቱ መንፈስ ቅዱስ እንዲወርድልኝ መጠየቄ እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ።” (ሲ.ኤች.)

ይህ ወንድም በተጨማሪ እንዲህ ይላል፡-

***“በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ለስድስት ሳምንታት ያህል በየቀኑ ትጸልዩ ዘንድ አደፋፍራችኋለሁ፤ ከዚያ ምን እንደሚፈጠር ታያላችሁ”***

## በሰርቢያ አገር  የ40 ቀናት ጸሎት

"እ.አ.አ. በመስከረም 2010 ላይ *<40 ቀናት የፀሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ ለክርስቶስ ዳግም ምጻት ለመዘጋጀት>* የሚለውን መጽሐፍ ተርጉመንና አሳትመን፤ በዩኒየናችን ለሚገኙ የቤተ-ክርስቲያን አባላት በሙሉ እንዲደርስ አደረግን። ከዚያም በመቀጠል ለተከታታይ 40 ቀናት የሚቆይ፣ መንፈስ ቅዱስ እንዲወርድልን በጾምና በፀሎት የምንጠይቅበትን ሳምንታዊ የጸሎት ስብሰባዎችን በአጥቢያ ቤተ-ክርስቲያናትና በአባላት መኖሪያ ቤቶች አዘጋጀን።

ከዚያን ጊዜ ወዲህ፤ በአጥቢያ ቤተ-ክርስቲያናት ፍጹም አዲስ ሁኔታ ተፈጥሯል። ንቁ ያልነበሩ የቤተ-ክርስቲያን አባላት መነቃቃት ጀመሩ፤ ሌሎችን ለማገልገልም ይበልጥ ፍላጎት አደረባቸው። ለዓመታት በተለያዩ ጉዳዮች እርስ በርሳቸው ሲጣሉ የነበሩ [እርስ በርሳቸው እንኳን መነጋገር ያቆሙ!] አሁን ታርቀው ለሌሎች ወንጌልን ለመመስከር በጋራ ዕቅድ ማውጣት ጀመሩ።

ከዚያም በጥቅምት 2010 በነበረው ዓመታዊ ዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ ለ 5 ዓመታት የሚቆየው "የመነቃቃትና የተሃድሶ ንቅናቄ" ፕሮግራም እንደጀመረ ማስታወቂያ ተነገረ። እኛም እግዚአብሔር ቀድሞውኑ በዩኒየናችን ጀምሮ የነበረውን የመነቃቃትና የተሃድሶ ፕሮግራም በደስታ ቀጠልን።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እርስ በርሳችን የቀረበ ሕብረት፣ የበለጠ አንድነትና በዩኒየናችን ሠራተኞችም መካከል የተሸለ መግባባት አይተናል።" (M. Trajkovska, Southern European Union, Belgrade quoted in www.revivalandreformation.org)

## በዙሪክ / ስዊዘርላንድ የ40 ቀናት ጸሎት

"ፓስተራችንና እኔ በተለያዩ አጋጣሚዎች ለየብቻችን እያለን ይዘቱ ለሁለታችንም ጥልቅ የደስታ ስሜትን የፈጠረብንን በዴኒስ ስሚዝ ተዘጋጅቶ በሪቪውና ሔራልድ ማተሚያ ቤት የታተመ፣ *<40 ቀናት የፀሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ ለክርስቶስ ዳግም ምጻት ለመዘጋጀት>* የተሰኘ አንድ መጽሐፍ አግኝተን ነበር። ለእኔ ይህ መጽሐፍ ከተነበበ በኋላ እንዲሁ መጽሐፍ መደርደሪያ ላይ እንደሚቀመጥ መጽሐፍ አይደለም። የመጽሐፉ ይዘት ሕይወቴን ለውጦቶታል።

ወደ 100 የሚጠጉ አባላት ያሉበት በዙሪክ ዎልፍስዊንክል የሚገኘው ቤተ-ክርስቲያናችን፣

አባላት ለመነቃቃትና ለጸሎት ታላቅ ፍላጎት ስለነበራቸው፡፡ በ2011 ዓ.ም. የበልግ ወቅት ሲደርስ <የ40 ቀን> የጸሎት ፕሮግራም አቀድን። <40 ቀን> የሚለው መጽሐፍ ይህንን የፀሎት ጊዜ ለማከናወን የሚያስችል ዝርዝርና ጠቃሚ መረጃዎችን ከዚህም በተጨማሪ 40 ዕለታዊ አጫጭር የጥሞና ቃሎችን ይዟል።

ርዕሶቹ በመንፈስ ቅዱስ ስለመሞላት፣ ስለጸሎት፣ ወንጌልን ስለመስበክ፣ የሱስ በእኔ ውስጥ ሆኖ ስለሚመራው ሕይወትና ስለ መንፈሳዊ ሕብረቶች የሚገልጹ ናቸው።

እናም <40 ቀን> የሚለውን መጽሐፍ በጥቅምት 1፣ 2011 በታላቅ ናፍቆትና ጉጉት ማጥናት ጀመርን። ደስ የሚያሰኘው ደግሞ አብዛኛዎቹ የቤተ-ክርስቲያናት አባላት በዚህ ፕሮግራም ላይ መሳተፋቸው ነው። የጸሎት አጋሮች በዕለቱ ለመጸለይ ይገናኙ ነበር፣ ምእመናን አጫጭር የጽሑፍ መልዕክት በየዕለቱ ይላላኩ ወይም ደግሞ በስልክ በየዕለቱ ይጸልዩ ነበር። አንዱ ቡድን ደግሞ ሁሌ በየማለዳው 12፡00 ላይ ለአምልኮና ለጸሎት ይገናኝ ነበር።

ያሳለፍናቸው40 ቀናቶች የማይረሱ ልምምዶች ነበሩ። እግዚአብሔር ብዙ ጸሎቶቻችንን መለሰ፥ በተመሳሳይ ጊዜ በተለይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች ጋር በተያያዘ በተከታታይ ትምህርት ሲሰጥ ነበር። እነዚህ ትምህርቶች ታላቅ በረከት ነበሩ። ብዙ አዳዲስ እንግዶች ተሳትፈው የነበሩ ሲሆን ቀጥሎ ለነበረውም የትንቢተ ዳንኤል ሴሚናር 20 ሰዎች ተመዝግበው ነበር። [በመጋቢት 2013 በነበረው ክትትል መሠረት በዙሪክ ለ20 ዓመታት ተከስቶ በማውያቅ መልኩ ከ50-60 የሚሆኑ እንግዶች መጥተው የትንቢት ሴሚናሩን ተካፍለዋል።]

የእግዚአብሔር መንፈስ ለቤተ-ክርስቲያናችን ቀጣይነት የነበረውን ለውጥ አምጥቶላታል፤ ትናንሽ ቡድኖቻችን ማደግ ሲጀምሩ መመልከትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችን ለመስጠት ጉጉት የነበራቸውን የቤተ-ክርስቲያን አባሎቻችን ማየት ታላቅ ደስታን ሰጠን። በዚህ ፕሮግራም ላይ የተሳተፉ ሁሉ የተጀመረው የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ እንዲቀጥል ጥልቅ ፍላጎት ነበራቸው። እግዚአብሔርን በሙሉ ልባችን ሆነን ልናመሰግነውና ክብርንም ልንሰጠው እንፈልጋለን።" *(ቢትሪስ ኤገር ከዙሪክ ዎልፍስዊንክል ሊደቬንቲስት ቤተ-ክርስቲያን)*

## 40 ቀናት የጸሎትና የወንጌል ጥረት በኮሎኝ / ጀርመን

ፓስተር ጆአኦ ሎትዝ ጀርመን-ብራዚላዊ ነው። ለ38 ዓመታት በብራዚል አገር በቤተ-ክርስቲያናትና በሆስፒታሎች ውስጥ እንዲሁም በሰበካ ቢሮ እና በደቡብ አሜሪካ ዲቪዥን

መሥሪያ ቤት አገልግሎ በመጋቢት 2012 ዓ.ም. ጡረታ ወጥቷል። ከጡረታ በኋላ እርሱና ባለቤቱ በ"ሂዝ-ሃንድስ-ሚሽነሪዎች" የአገልግሎት ድርጅት ውስጥ ሆነው ፖርቱጋልኛና ስፓኒሽ ቋንቋ ተናጋሪ ቤተ-ክርስቲያናት ውስጥ ለማገልገል ወደ ኮሎኝ ከተማ ለመምጣት ተስማሙ።

በኮሎኝ ቤተ-ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ስለነበረው ልምምድ ፓስተር ጆአኦ ሎትዝ እንዲህ ይላል፡- "የቤተ-ክርስቲያን አባላትን ለማበረታታትና እንግዶችን ለመጋበዝ በኮሎኝ ትንንሽ ቡድኖችን ማቋቋም ጀመርን። በብራዚል የነበረንን ተሞክሮ መሠረት በማድረግ በኮሎኝ የ40 ቀናት ጸሎትን ማካሄድ ጀመርን። መጽሐፉ በፓርቱጋልኛም ቋንቋ ይገኝ ነበር።

ፓርቱጋልኛ፣ ስፓኒሽኛና ጀርመንኛ ተናጋሪ የነበሯት ቤተ-ክርስቲያን አባላት የ40 ቀናት የጸሎት ጊዜን በደስታ ተሞልተው ጀመሩ። በየዕለቱ ቁጥራቸው መቶ ለሚደርስ ጓደኞቻችንና ለምናውቃቸው ሰዎች መጸለይ ጀመርን። የእነዚህ ሰዎች ስም ዝርዝር በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ተጽፎ ነበር። ለእነርሱ እየጸለይንላቸው እንደሆነና ለእንግዶች ወደተዘጋጀው ልዩ የሰንበት አገልግሎት እንደምንጋብዛቸው እንዲያውቁ ያደረግነው በ30ኛው-35ኛው የፀሎት ቀን ነበር። ወደዚህ ልዩ የቤተ-ክርስቲያን ፕሮግራም 120 ሰዎች መጡ። ስብከቱን የወሰዱት የኖርድራይን-ዌስትፋለን ሰበካ ፊታደኛ ወንጌላውያን አገልግሎት ዳይሬክተር የሆኑት ክርስቲያን ባዶሬክ ነበሩ። በሰሌዳው ላይ ስማቸውን ያዩ አንዳንድ እንግዶች ከደስታ የተነሳ አለቀሱ።

ከዚያ በኋላ ከብራዚል የመጣው ወንጌላዊ አንቶኒዮ ጎንካልቬስ ለ15 ቀናት ያህል የወንጌል ጥረት አካሄደ። በእያንዳንዱ ምሽት ለ1 ሰዓት ከ50 ደቂቃ ያህል ይሰብክ ነበር። የተከታታይ ትምህርቱ ርዕስ "እስቲ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲያስገርምህ ፍቀድለት" የሚል ነበር። ርዕሶቹ በክርስቶስ ዳግም ምጻት እንዲሁም በትንቢተ ዳንኤልና በዮሐንስ ራዕይ ዙሪያ ያተኮሩ ነበሩ። ስብከቶቹና መዝሙሮቹ ከፖርቱጋልኛ ወደ ጀርመንኛ ይተረጎሙ ነበር። በእያንዳንዱ ምሽት ትናንሽ ኳየሮችና ጥሩ ሙዚቃ ይደመጥ ነበር። እያንዳንዱ ስብከት ከመጠናቀቁ በፊት ለነፍሳት ጥሪ ይደረግ ነበር። የቤተ-ክርስቲያን አባላት በ40 ቀናት የፀሎት ጊዜ ይፀለይላቸው ለነበሩት ሰዎች በብርቱ ይጸልዩ ነበር።

ቤተ-ክርስቲያናችን ለ80 ሰዎች ያህል ብቻ ነው የሚበቃው። ነገር ግን በእነዚያ ቀናት ከ100 በላይ ሰዎች መጥተው ፕሮግራሙን ይካፈሉ ነበር። በየሳምንቱ መባቻ ቤተ-ክርስቲያናችን ሙሉ የነበረ ሲሆን በሳምንቱ ቀናት ደግሞ ወደ 60 የሚደርሱ ሰዎች ይካፈሉ ነበር ነበሩ። 32

እንግዶች በየቀኑ ፕሮግራሙን ይከታተሉ ነበር። በመጨረሻም 8 ሰዎች ተጠመቁ፣ 14ቱ ደግሞ የጥምቀት ትምህርት ለመማር ፈቃደኞች ሆኑ። በዓመቱ መጨረሻ ላይ 13 ሰዎች ተጠመቁ።

በእነዚህ ሳምንታት የእግዚአብሔርን እጅ ያየንባቸው ብዙ የሚያስገርሙ ምስክርነቶች ነበሩን። ከፖርቹጋልኛ ወደ ጀርመንኛ የሚተረጉም ተርጓሚ ማግኘት እጅግ አስቸጋሪ ነበር። አንድ የካቶሊክ መምህርት በትርጉም ለመርዳት ፈቃድዋን ገለጸች። ነገር ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ብዙም ልምምድ እንዳልነበራት ነገረችን። ከዚያም የፕሮቴስታንት ተርጓሚ ለማግኘት ፀለይን። ከዚያም በኋላ ብዙ ሳይቆይ በአንድ ሬስቶራንት ውስጥ በጴንጤቆስጤ ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ በታላቅ ደስታ ከፖርቹጋልኛ ወደ ጀርመንኛ እንደምትተረጉም የገለጸችልንን አንዲት ሴት ተዋወቅን። ይህች ሴትም የወንጌል ጥረቱን ሙሉ ስትተረጉምልን ሰንብታ በመጨረሻም እርሷም ደግሞ ተጠመቀች።

በወንጌል ጥረቱ ተከታታይ ፕሮግራም ላይ ተርጓሚያችን የነበረችው ማሪያ በመተርጎም የምታግዛትን ኤልሳቤጥ የተባለችውን ጓደኛዋን ማምጣት (መጋበዝ) እንደምትፈልግ ገለጸችልን። ኤልሳቤጥ 13 አባላት የነበሩት ትንሽ የኮሎምቢያውያን ቤተ-ክርስቲያን መሪ ነች። ኤልሳቤጥ የቤተ-ክርስቲያኗን አባላት ከእርስዋ ጋር ይዛ መጣች። ከመጡት እንግዶች መካከል ሁለት ሰዎች ተጠመቁ። አሁን ኤልሳቤጥና ቤተሰቦቿ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እየተሰጣቸው ይገኛሉ።

ሌላው ምስክርነታችን ከሆፕ ቻኔል የቴሌቪዥን ፕሮግራም ጋር የተያያዘ ነው። አንዲት ጀርመናዊት ወይዘሮ የሆፕ ቻኔል ቴሌዚዥንን በአጋጣሚ ታገኝና ስለ ትክክለኛው ሰንበት እና ትርጉሙ የተሰጠውን ትምህርት ጨምሮ ሌሎች የሚባርኩ መልእክቶችን ሰምታ በጣም ተደንቃ ነበር። ባልዋንም ፕሮግራሞቹን እንዲያዳምጥ ጋበዘችው፡፡ እርሱም ባዳመጠው መልዕክት ደስ ተሰኘ፡፡ ከዕለታት በአንዱ ቀን እናትዋን ለመጎብኘት በምትሄድበት ጊዜ ዘወትር የምትሄድበትን መንገድ ትታ በሌላ መንገድ ለመሄድ ፈለገች። በዚያም መንገድ ላይ <የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ-ክርስቲያን> ምልክት ትመለከታለች። በሆፕ ቻኔል ቴሌዚዥን ላይ የሚሰራጩትን ፕሮግራሞች የሚያቀርቡት እነዚህ አድቬንቲስቶች መሆናቸውን ተገነዘበች። የሚቀጥለው ሰንበት ቀን ሲደርስ ወደዚያ ቤተ-ክርስቲያን ፕሮግራም አመራች። ከዚያም ባለቤቷና እናቷ አብረዋት እንዲሄዱ ጋበዘቻቸው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሦስቱም ተጠመቁ።

ሌላኛው ምስክርነት ደግሞ አንዲት ሩሲያ-ጀርመናዊት እህት የተለማመደችው ነው። በ40ው የፀሎት ቀናት ፕሮግራም ላይ ከተሳተፈች በኋላ፣ ራሽያኛ ተናጋሪ ለነበሩት ጎረቤቶቿ መጸለይ ጀመረች። ከጎረቤቶቿ ለአንዷ እየጸለየችላት እንደሆነ ስትነግራት ጎረቤቷ በጣም ተገርማ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ሰንበት የምትጠብቀዋን (የምታከብረዋን) ቤተ-ክርስቲያን ለማግኘት እንደምትፈልግ ነገረቻት። ከዚያም እርሷና ሌሎች ጎረቤቶቿም ወደ ወንጌል ጥረቱ ተከታታይ ፕሮግራም መጡ። ከእነርሱም ሁለቱ ተጠመቁ።

ሌላኛው ምስክርነት ደግሞ፣ ጄን የተባለች እህት ምስክርነት ነው። በብራዚል አገር ስትኖር ሳለ፣ የባፕቲስት ቤተ-ክርስቲያን አባል ነበረች፣ አሁን ደግሞ በኮሎኝ ከተማ ፖርቱጋልኛ ቋንቋ ተናጋሪ ቤተ-ክርስቲያን በመፈለግ ላይ ነበረች። እርሷም፣ ከአድቬንቲስት ቤተ-ክርስቲያን ጋር የመገናኘትን ዕድል አገኘች፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትን ከተማረች በኋላ ተጠመቀች። ጌታን በዚህ መልኩ ከተቀበለች በኋላ በብራዚል ለሚገኙት ዘመዶችዋ እና አድቬንቲስት ለሆነው አጎቷ እሷም አሁን አድቬንቲስት መሆኗን ነገረችው። ለእናቷ፣ ለወንድምና እህቶቿ እንዲሁም ከዚህ በፊት አባል ለነበረችበት በብራዚል ለሚገኘው የባፕቲስት ቤተ-ክርስቲያን ይህ ዜና በጣም አስገረማቸው። በብራዚል የሚኖሩት ቤተሰቦቿና ዘመዶችዋ ስለ ሰንበት ትርጉም ለማወቅ ስለፈለጉ በተከታታይ ወደ አድቬንቲስት ቤተ-ክርስቲያን ይሄዱ ነበር። ከጥቂት ጊዜ በኋላም በብራዚል 5 ሰዎች፡- እናቷ፣ ሁለት እህቶቿና ሌሎች ዘመዶችዋ ተጠመቁ። አሁን ደግሞ በአርጀንቲና የምትኖረው ሌላኛዋ እህቷ ጌታን እንድትቀበል እየጸለየች ነው።

በእግዚአብሔር አመራር ሌሎች ብዙ ምስክርነቶችን አይተናል። በመጀመሪያው የጥምቀት ስነ ስርዓት ላይ ከጣሊያን፣ ከጀርመን፣ ከፔሩ፣ ከብራዚል፣ ከዩክሬን፣ ከቬኔዙዌላ፣ ከኮሎምቢያና ከሩስያ ባጠቃላይ 8 ሰዎች ተጠመቁ።

በበልግ ወቅት እንደገና ከ40 የፀሎት ቀናት ፕሮግራም ጋር በማያያዝ ሌላ የወንጌል ጥረት ተከታታይ ፕሮግራም አኬሄድን። በአሜሪካ የሚኖሩ ትውልደ ብራዚላዊያን የሆኑት ወንድም ጂሚ ካርዶስና ባለቤቱ ነበሩ የወንጌል ጥረቱን ተከታታይ ፕሮግራም ያካሄዱት። ምንም እንኳን ተከታታይ ፕሮግራሙ ለአንድ ሳምንት ብቻ የተካሄደ ቢሆንም በመጨረሻ 4 ደስ የሚሉ ሰዎችን ለማጠመቅ ችለናል፡፡ እነርሱም ከዚህ ቀደም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሲያደርጉ የቆዩ ሦስት ጀርመናዊያንና አንድ ጣሊያናዊ ነበሩ።

ሁለቱም ጥምቀቶች የተካሄዱት 400 አባላት ባሏት እና ውብ የሆነ የጥምቀት ቦታ ባላት

የኮሎኝ ከተማ ዋና ቤተክርስትያን ውስጥ ነበር።

በዚህ አይነት ታላቅ መንገድ ያስደሰተንን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። ገና ከዚህ የሚበልጡ ሌሎች ብዙ ምስክርነቶች እንዳዘጋጀልን እርግጠኛ ነኝ። እባካችሁ በጸሎታችሁ አግዙን።" *(ጀአአ ሎትዝ፣ ኮሎኝ፥ ጀርመን)*

## ከተለያዩ ግለሰቦች የተላኩ ምስክርነቶች

**ሕይወት ያለው የምልጃ ፀሎት፡-** <40 ቀናት> የሚባለውን መጽሐፍ በመጀመሪያ እንዲሁ ቶሎ አንብቤ ጨረስኩት። ከመጀመሪያው ገጽ አንስቶ በመልዕክቱ እጅጉኑ እገረም ነበር። መጽሐፉ እንደሚመክረን ለአንድ ሰው መጸለይ ብቻ አይበቃም፥ የምንጸልይለትን ሰው በፍቅር ልንንከባከበው ይገባል። የምንጸልይለትን ሰው በፍቅር ስንንከባከበው፣ የምልጃ ፀሎታችን ሕይወት ይኖረዋል፡፡ ሕይወት ያለው ሕያው እምነት ማለት ይህ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም የምልጃ ጸሎትን በዚህ መልኩ ባለማየቴ በጣም አዝናለሁ። ይህ አይነት ፀሎት፣ ለሌሎች ለሚፀልየውንም ሆነ ለሚፀለይለት ሰው አስፈላጊ (ጠቃሚ) እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ። ሕይወት ባለው የምልጃ ፀሎት ልምምድ ምዕመናን በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ያላቸው ሕብረት እንደሚጠነክር ይህ መጽሐፍ አሳምኖኛል። አ! በመጽሐፉ የመጨረሻዎቹ ምዕራፍ ላይ እንደተገለጸው አይነት ሕብረት እንደሚኖረን ተስፋ አደርጋለሁ። እውነት ለመናገር ለረዥም ጊዜያት እንዲህ ያለውን ሕብረት እናፍቅ ስለነበር፣ ይህንን መጽሐፍ ሳነብብ አንባዬ ተናነቀኝ። "ክርስቶስ በእኔ ውስጥ" የሚለውን ትምህርት አጥብቆ ስለሚያተምር፣ እንዲሁም በራሳችን ጥረት የትም እንደማንደርስ ግልጽ ስለሚያደርግ ይህ መጽሐፍ ተስማምቶኛል። "ክርስቶስ በእኔ ውስጥ" በሚለው ርዕስ ዙሪያ በርካታ መጽሐፍትን አንብቤያለሁ፥ ሆኖም ግን ይህ መጽሐፍ ከሁሉም በበለጠ ግልፅ አድርጎልኛል። ይህ መጽሐፍ የእናንተንም የፀሎት ሕይወት እንደሚያጠነክር፣ በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ያላችሁን ሕብረት እንደሚጠነክርና የምልጃ ፀሎታችሁን ሕይወት እንዲኖረው እንደሚያደርግላችሁ እርግጠኛ ነኝ። ይህ መጽሐፍ ተስፋ ሰጪ ነው፡- ለእኔም ለቤተ-ክርስቲያንም፣ በዓለም ላሉት ሁሉም፡፡ ስለዚህ መጽሐፍ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።"

**ከጥቂት ሳምንታት በኋላ፡-** ከአንዲት እህት የኢ-ሜል መልዕክት ደረሰኝ፡- "እንደምታውቀው በመጀመሪያ መጽሐፉን እንዲሁ ቶሎ አንብቤ ጨረስኩት። ነገር ግን አሁን

እንደገና ከጸሎት አጋሬ ጋር በመሆን መልዕክቶቹን ማንበብ ከጀመርኩ ወዲህ፣ መጀመሪያ ካነበብኩት ይልቅ ይበልጥ ጠቃሚ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ከዚህ ቀደም ለብቻዬ ሆኜ ሳነብብ መልስ ላላገኘሁባቸው ጥያቄዎች ዛሬ መልስ አገኘሁ። በትጋትና በንቃት እየተሳተፈች ስላለችው የጸሎት አጋሬ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።" *(ሔቾ. ኬ.)*

***ብዙም እርግጠኛ አልነበርኩም፡-*** *<ወደ የግል መንፈሳዊ መነቃቃት የሚመራ መንገድ>* የምትለው ትንሽዬ መጽሐፍ በእጅጉ ባርካኛለች... በአድቬንቲስት ቤተሰብ ውስጥ ስለተወለድኩና ስላደግኩ በትክክለኛው መንገድ ላይ እየተራመድኩ እንዳለሁ ነበር ራሴን የምምለከተው። የአስሩ ቆነጃጅት ምሳሌ እና በተለይም ደግሞ ሮሜ 8፡9 *"የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም።"* የሚለው ጥቅስ በጣም አስደነገጠኝ። በሕይወቴ ውስጥ የመንፈስ ፍሬን ስለማላይ፣ በመንፈስ ቅዱስ መሞላቴን ብዙም እርግጠኛ አልነበርኩም፡፡ መንፈስ ቅዱስ በእኔ ሕይወት ይሥራ አይሥራ እርግጠኛ አልነበርኩም። ዛሬ ሰንበት ከሰዓት በኋላ ይህችን ትንሽዬ መጽሐፍ አንብቤ ስጨርስ፤ ጠለቅ ያለ፣ ይህ ነው ተብሎ የማይለካ ሐዘን ወረረኝ። ከዚያም በኋላ በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ የሚገኘውን ሞዴል ጸሎት ማንበብ ጀመርኩኝ፤ እናም፣ ልቤ እንዲለወጥና መንፈስ ቅዱስን እንድሞላ ጥልቅ ፍላጎት ተሰማኝ፣ እግዚአብሔርም እንደ ፈቃዱ እንዲያበጀኝ ምኞቴን ገለፅኩኝ.... *(ኤ. ፒ.)*

ይህችን መጽሐፍ ካነበበ በኋላ አንድ ወንድም እንዲህ ብሎጻፈልኝ፡-

"ከተወሰነ ጊዜ በፊት በመነቃቃት ዙሪያ የጻፍከውን ጽሑፍ አነበብኩት። ይህ ርዕስ ከሦስት ዓመት ጀምሮ በሃሳቤ ይመላለስ ነበር። እነሆ አሁን *<ወደ የግል መንፈሳዊ መነቃቃት የሚመራ መንገድ>* የሚለውን መጽሐፍ አነበብኩ። ልናገር የምችለው ነገር ቢኖር <አሜን!> ብቻ ነው! በዚህ መጽሐፍ ውስጥ፣ እኔም ትክክለኛ ናቸው ብዬ የማስባቸውን ሃሳቦች በማንበቤ ደስ ብሎኛል፡፡ እኛ ምዕመናን፣ የቤተ-ክርስቲያናችንን የደህንነትን ኢላማ (ግብ) ለጥቂት እየሳትን እንዳለን ይሰማኛል። በወሳኝ ወይም አስፈላጊ በሆኑት ነገሮች ላይ ያለን ትኩረት እየጠፋ እንዳለ ይሰማኛል! አብዛኛውን ጊዜ ትኩረት የምንሰጠው፡- 'እውነት ምንድነው' 'እንዴት ልንኖር ይገባናል' 'ትንቢት ምን ያህል አስፈላጊ ነው' በሚሉት ነጥቦች ላይ ነው። ስለነዚህ ርእሶች መነጋገር የለብንም ማለቴ ሳይሆን፣ ነገር ግን እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች **ለምን** እንደሰጠን ራሳችንን መጠየቅ አለብን!

<እውነት> የምንለው ነገር ዓላማው ከእግዚአብሔር ጋር ሙሉ ሕብረት እንዲኖረን አይደለምን? እነዚህ ነጥቦች እግዚአብሔርን የበለጠ እንድናውቀው የሚረዱን አይደሉምን? የትንቢት ዓላማ ዓለምን በሙሉ በእጁ የያዘው፣ የእኛንም ሕይወት የሚመራውና መልክ የሚያስይዘውን፣ የእግዚአብሔርን ታላቅነትና ሁሉን ቻይነት **እንድናውቅ** አይደለምን? የዘላለም ሕይወትስ ምንድነው? ዮሐንስ 17፡3 *"እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን **ያውቁ** ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።"* ሙሽራው ለአምስቱ ሰነፍ ቆነጃጅቶች 'አላውቃችሁም' ነበር ያላቸው። የእምነታችን ዋና ዓላማ  እግዚአብሔርን እንድናውቀው ነው፣ ልክ ያኔ ቤተ-መቅደሱን እንደሞላው [2ኛ ዜና 5፡13-14] እኛንም እንዲሞላን ከእርሱ ጋር ሕብረት እንድናደርግ ነው። በእኛ ሕይወት ውስጥ ሲኖር፣ ሁለንተናችንን ሲሞላ፣ ያኔ እኛ ሳይሆን እየኖርን ያለነው፤ ይልቁንም ክርስቶስ ነው በእኛ ውስጥ የሚኖረው።"

## አስገራሚ ምላሾች ለምልጃ ፀሎት

"የዴኒስ ስሚዝ ሁለተኛው <40 ቀናት መጽሐፍ> ለእኔ ትልቅ በረከት አምጥቶልኛል። ከምጸልይላቸው ሰዎች መካከል አንዳንዶቹ በሕይወታቸው ትልቅ ለውጥ አስተውለዋል።

በ40ዎቹ የፀሎት ቀናት ወቅት፣ ከአንድ ጓደኛዬ ጋር ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ውይይት አደረግን። ካለፉት ጥቂት ሳምንታት ጀምሮ ሕይወቱ እየተለወጠ እንደመጣ ነገረኝ። የፀሎት ጊዜ ለመውሰድ ፍላጎቱ እንደጨመረ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብና ማሰላሰል ደስ እንደሚያሰኘው፣ ከዚህ በፊት እርሱ ትልቅ ቦታ ይሰጣቸው የነበሩት ነገሮች አሁን ለእርሱ ዋጋ እንደሌላቸው ነገረኝ። ከዚያም በ 40 ቀናት የፀሎት ፕሮግራም ላይ ከምፀልይላቸው 5 ሰዎች ውስጥ አንዱ እርሱ እንደሆነ ነገርኩት። ከዚያም በደስታ መገረም እንዲህ ሲል መለሰልኝ፡- 'በሕይወቴ ለሚታየው ለውጥ ሁሉ ኃላፊነቱን የምትወስደው አንተ ነህ ማለት ነው!።'

አንዲት ወጣት ሴት ልጅ ደግሞ ሕይወቷን 100% ለእግዚአብሔር አሳልፋ ለመስጠት ውሳኔ አደረገች። ምንም እንኳን ከልጅነቷ ጀምሮ ስለ ክርስትና እምነት ብታውቅም፣ ሕይወቷን ያለ እግዚአብሔር ስትኖር ከርማለች። ስለ እምነት ጉዳይ ብዙም ፍላጎቱ ያልነበራትና በዓለማዊ ሕይወት ውስጥም ሙሉ በሙሉ የተጠመደች ነበረች። አሁን ግን ሙሉ በሙሉ ተለውጣለች፤ የሚያውቋትና የሚያዩዋት ሁሉ በጣም ተገርመዋል። አሁን ከእኔ ጋር መጽሐፍ ቅዱስ እያጠናችና በቤተ-ክርስቲያናችን እየተደረገ በሚገኘው የ40 ቀናት

የፀሎት ፕሮግራም ላይ እየተካፈለች ነው፤ ሌሎችም በእምነት ሕይወታቸው እንዲያድጉና እንዲጠነክሩ ልታደፋፍራቸው ትፈልጋለች።

ስጸልይላት የነበረች ሌላ ወጣት ሴት ደግሞ አንድ ሳምንት ያህል በሚፈጀው ስልጠና ላይ መካፈልና ከሌሎች ተሳታፊዎች ጋር በአንድ የእንግዳ ማረፊያ ውስጥ መቆየት ነበረባት። ከነዚህ ከማታውቃቸው ሰዎች ጋር ሳምንቱን ሁሉ ማሳለፍ እንዳለባት ስታስብ ተጨነቀች። ከመሄዷ አንድ ቀን አስቀድሞ በጸሎት አደፋፈርኳት፤ ከረዥም ጊዜ ወዲህ፣ ለእርሷ እየፀለይኩላት እንዳለሁ ነገርኳት፡፡ ከዚያም እግዚአብሔር በምትሄድበት ቦታ ሁሉ ሰላምን እንዲሰጣትና ይህ ፀሎት በእግዚአብሔር ፊት እንደተሰማ ማረጋገጫ እንዲሰጣት ፀለይን። ስልጠናው ከሚሰጥበት ቦታ ሆና ስልክ ደወለችልኝና በታላቅ ደስታ እግዚአብሔር በእርሷ ሕይወት ትልቅ የማይታመን ነገር እንዳደረገላት ነገረችኝ። ፍጹም ሰላም ብቻ ሳይሆን የሰጣት፣ ዳንኪራ፣ አልኮሆል እና የመሳሰሉት ነገሮች ባሉበት የምሽት ፕሮግራሞች ላይ ለመካፈል እንደማትፈልግ ድፍረትን ሰጣት።

እግዚአብሔር ባለማቋረጥ የምንፀልየውን ፀሎት እንደሚሰማ እርግጠኛ ስለሆንኩ፣ የ40 ቀናት የፀሎት ፕሮግራም ካለቀ በኋላም እንኳን ለእነዚህ ሰዎች መፀለይን ቀጥያለሁ።” (ኤ. ኤም)

## በምልጃ ፀሎት አማካይነት እግዚአብሔር እንዴት እንደሚሠራ

“ባለፉት አምስት አመታት ከአንድ ለእኔ በጣም ወሳኝ ከሆነ ግለሰብ ጋር የነበረኝ ግንኙነት ሙሉ በሙሉ ተቋርጦ ነበር። በተደጋጋሚ የምጽፍለትን መልዕክቶቼን ችላ ያላቸው ይመስለኛል። ላለፉት ሦስት ዓመታት ወደ ቤተ-ክርስቲያን ሳይሄድ እንደቆየ ሰምቼ ነበር (በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ነበር ያደገው)። ክርስቲያን ካልሆነች ሴት ጋርም ግንኙነት ጀምሮ እንደነበር ሰማሁ። ከእኔ 600 ኪ.ሜ ርቆ ስለሚኖርና እንዲሁም ለምጽፍለት መልዕክት አንዴም መልስ ሰጥቶኝ ስለማያውቅ፤ ምንም እንኳን ከእርሱ ጋር እንደገና እንገናኛለን ብዬ ባላስብም፤ የዚህን ወጣት ስም ከምፀልይላቸው ሰዎች የስም ዝርዝር ውስጥ አካተትኩት። እፀልይለት የነበረውም፣ ወይ እንዲደውልልኝ ወይም ደግሞ መልዕክት እንዲልክልኝና መኖሩን እንዲያሳውቀኝ ነበር።

ብዙም ሳይቆይ እኔ በምኖርበት አካባቢ በሚገኘው ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ (ማለትም፣ የ40 ቀናት የፀሎት ጊዜ ሲካሄድበት በነበረው ቤተ-ክርስቲያን) የእርሱ ወንድም እንደሚጠመቅ

ሰማሁ። በጥምቀት ፕሮግራሙ ላይ ስፀልይለት የነበረውን ወንድም አገኘሁት! ጠለቅ ያለ ውይይት ተወያየን፡፡ ከተወሰነ ጊዜ ወዲህ ወደ እግዚአብሔር የመመለስ ትልቅ ፍላጎት እንደነበረው፣ ነገር ግን የአኗኗር ዘይቤውን ይቀየር ዘንድ የሚችልበት አቅም እንዳልነበረው ነገረኝ። ላለፉት 20 ቀናት በትጋት ለእርሱ ስጸልይለት እንደነበረና ከዛም በፊት እንኳን ስሙ በጸሎት ዝርዝሬ ውስጥ እንደነበር ነገርኩት። በርግጥም በእነዚህ ቀናት እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ሲሠራ እንደነበር ተሰምቶት እንደነበር በአድናቆት ነገረኝ።

በዚህ እጅግ በተባረከ የጥምቀት ሥነ ሥርዓት ላይ የዚህ ወጣት ልጅ ልብ በጣም ተነክቶ ስለነበር፤ ፓስተሩ ጥሪ በሚያደርግበት ጊዜ በውስጡ ትልቅ ትግል እየተካሄደ እንደነበር አስተዋልኩ፡፡ ከረዥም ትግልም በኋላ በመጨረሻ በጉልበቶቹ ተንበርክኮ ማልቀስ ጀመረ። ዳግመኛ ራሱን ለእግዚአብሔር አሳልፎ ሰጠ! ከመሰነባበታችን በፊት ከዛሬ ጀምሮ ዘወትር ወደ ቤተ-ክርስቲያን ለመሄድ እና ለመለወጥ ውሳኔ እንዳደረገ ነገረኝ። ይህ ያሳለፈው የሰንበት መባቻ በዚህ መልኩ ይጠናቀቃል ብሎ በፍጹም አልጠበቀም ነበር።

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ፣ ለወጣቶች ተዘጋጅቶ በነበረው ልዩ መንፈሳዊ ኮንፍረንስ ላይ በድጋሚ አገኘሁት። ይህም ኮንፍረንስ የበለጠ አጠነከረው፡፡ ይህ የምወደው ወዳጄ ወደ ጌታ ስለተመለሰ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።" *(ኤም.ኤች.)*

## በሉድዊግስበርግ ከተማ (ባደን-ውርተንበርግ) ውስጥ ያለችው ቤተ-ክርስቲያን ምስክርነት

"በመጀመሪያ እኔና ባለቤቴ ለሁለት በመሆን <40 ቀናት> የሚለውን መጽሐፍ በማጥናትና በመፀለይ ጠቃሚ ትምህርትና በረከት አገኘን። ከዚያ በኋላም በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ በሳምንት ሁለት ቀን የጸሎት ስብሰባ አዘጋጅተን ከሌሎች የቤተ-ክርስቲያን አባላት ጋር መጽሐፉን አጠናን። በእነዚህ 40 ቀናት ውስጥ የእግዚአብሔርን ልዩ በረከትና አመራር እንዲሁም ብዙ ተአምራትን ተለማመድን። እግዚአብሔር ቤተ-ክርስቲያኑን አደሰ፣ አነቃቃ። ከዚህ በፊት ከእንግዶች ጋር የመነጋገር ድፍረቱ ያልነበራቸው የቤተክርስቲያን አባላት በራሳቸው ተነሳሽነት ከእንግዶች ጋር መነጋገር ጀመሩ። በሕብረት በምናደርገው ፀሎት አማካኝነት እግዚአብሔር እርስ በርስ የበለጠ አቀራረበን። በእነዚህ 40 ቀናት ውስጥ ስንፀልይላቸው የነበሩት 5 ሰዎች ሕይወት ውስጥ ጌታ ለውጥ አሳይቶናል። በነዚህ ሰዎች ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔር በተለየ ሁኔታ ሲሠራ ነበር። ሰዎች እግረ መንገዳቸውን ሲያልፉ

በሰንበት ቀን ወደ ቤተ-ክርስቲያን አገልግሎት በተደጋጋሚ ሲካፈሉ ተመለከትን። ከእነርሱ መካከል ለአንዱ ቤተሰብ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እየሰጠን እንገኛለን። ስለ ሰንበት እውነት ያወቁት በኢንተርኔት ላይ ከሚታዩ ቪዲዮችና *<ታላቁ ተጋድሎ>* ከሚለው መጽሐፍ ሲሆን ለረዥም ጊዜ ያህል ወደ ቤተ-ክርስቲያን መሄድ ይፈልጉ ነበር።” *(ካትያ እና ክርስቲያን ሺንደለር፣ ከሉደስዊግበርግ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ-ክርስቲያን)*

## የ40 ቀናት የፀሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ልምምድ

“ሁሉም ነገር የጀመረው *<ወደ የግል መንፈሳዊ መነቃቃት የሚመራ መንገድ>* በሚለው ርዕስ ዙሪያ ላይ በተሰጠ አንድ ሴሚናር ነበር። በዚያን ጊዜ በየዕለት ሕይወቴ እግዚአብሔርን የመለማመድ ጥልቅ ፍላጎት በውስጤ ማደግ ጀመረ። ከዚያም ስለ 40 ቀናት የፀሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ ሰማሁ። ይህንንም አድቬንቸር በግሌ መለማመድ እንደምፈልግ ወዲያው ግልጽ ሆነልኝ። ራሴን ወደምን አይነት ሁኔታ ውስጥ እየከተትኩ እንደሆነ በርግጥ አላውቅም ነበር። ተስማሚ የጸሎት አጋርን መምረጥ ለእኔ አዳጋች አልነበረም። ነገር ግን ለኔ አስቸጋሪ የነበረው ነገር ለ40 ቀናት ያህል በየዕለቱ የሕብረት የፀሎት ጊዜ ማግኘት ነበር። ነርስ ስለሆንኩ ሥራ የምገባበት ሰዓት የተለያየ ነው። ይህንን ከግምት ውስጥ አላስገባሁም ነበር። ቢሆንም፣ እግዚአብሔር ከመጀመሪያውኑ ጀምሮ ውሳኔዬን ባርኮት ነበር። ከፀሎት አጋሬ ጋር የእግዚአብሔርን ቃል የምንወያይበትንና መንፈስ ቅዱስ እንዲሞላን የምንፀልይበትን ይህንን ልዩ ጊዜ በታላቅ ጉጉት እናፍቅ ነበር። ፀሎታችን በሕይወታችን ለውጥ እያመጣ እንዳለ ተሰማን። ይህንን የበረከት ልምምዳችንን ለራሳችን ብቻ ይዘን መቆየት አልፈለግንም። ባገኘነው አጋጣሚ ለሌሎች እንነግር ነበር። ሌሎች ሰዎችም እንደ እኔ አይነት ልምምድ እንዲኖራቸው ማደፋፈር ነው የምፈልገው። ውጤቱም መና አልቀረም። አንዳንድ የቤተ-ክርስቲያን አባላት ያሳየነው የደስታ ስሜት እነርሱም ላይ ተጋባባቸው። ከጥቂት ጊዜ በኋላም የፀሎት ቡድኖች ተዋቀሩ። በየሳምንቱ ስለነበረን ልምምድ የምንመሰክርበትን ጊዜ እንናፍቅ ነበር። ይህ ‘ቫይረስ’ ወደ ብዙ የቤተክርስቲያን ወጣቶቻችን ተላለፈ። 40ው ቀናት እጅግ በፍጥነት ተጠናቀቁ። ቢሆንም ሕብረታችንን ለማቆም አልፈለግንም፤ አላቆምንምም። ከዚያ በመቀጠል ሌላ የ40 ቀናት የፀሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜአችንን *<ማራናታ- ክርስቶስ ይመለሳል>* የሚለውን፣ በኤለን ኋይት የተጻፈውን መጽሐፍን በማንበብ ቀጠልን። እግዚአብሔር ለረዥም ጊዜ እንድንጠብቀው አያደርግም። ገና 40ዎቹን የጸሎት ቀናት ከመጨረሳችን በፊት

እግዚአብሔር ለፀሎቶቻችን መልስ ይሰጠን ነበር። በዚህ ጊዜ ስንጸልይለት የነበረው አንድ ሰው ከረዥም የቤተ-ክርስቲያን መቅረት በኋላ ወደ ቤተ-ክርስቲያን መምጣት ጀመረ። እኛም እጅግ በጣም ደስ አለን። በዙሪያዬ ያሉ ሰዎች ለኔ ዋጋ ነበራቸው (ለእነርሱ ግድ ይለኝ ነበር)። የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሌሎች የማካፈል ምኞቴ የበለጠ እየጠነከረ መጣ። ሕይወቴ ተለወጠ። ብዙዎቻችን አንዳችን ከሌላችን ጋር ይበልጥ መተዋወቅና መግባባት ተፈጠረ። አንዱ የሌላውን ሸክም የመሸከም ፍላጎቱ ጨመረ። አሁን ስለ ሕብረት ያለኝ መረዳት የተለየ ነው፡፡ ሕብረት ለእኔ አዲስ ትርጉምን አግንቷል፡፡ የዴኒስ ስሚዝ <40 ቀናት የጸሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ> የሚለው መጽሐፍ ለኔ ሕይወት ታላቅ ለውጥ አምጥቶልኛል። የጸሎት አጋርን ማግኘትና እግዚአብሔርን መለማመድ የሚታሰበውን ያህል ከባድ አይደለም። ስለ እነርሱ የምንፀልይላቸው ሰዎች ወደፊት ያመሰግኑናል።" *(ሂልዴጋርድ ዌልከር በቀዶ ጥገና ክፍል ነርስ ነች፡፡ የክራልስሃይም ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ-ክርስቲያንም አባል ነች)*

## ምሳሌያችን የሱስ

ጌታችን የሱስ በሁሉም ነገሮች ታላቁ ምሳሌያችን ነው። በሉቃስ 3፡21-22 እንዲህ የሚለውን እናነባለን፡- *"ሕዝቡም ሁሉ ከተጠመቁ በኋላ ኢየሱስ ደግሞ ተጠመቀ። ሲጸልይም ሰማይ ተከፈተ፥መንፈስ ቅዱስም በአካል መልክ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ ..."*

ይህንን ክስተት አስመልክቶ ኤለን ኋይት የሚከተለውን ብላለች፡- "ወደ አባቱ ሲጸልይ፤ ለፀሎቱ መልስ ሰማይ ተከፈተ፤ መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል በመውረድ በእርሱ ላይ አረፈ።" (E.G. White, *Ye Shall Receive Power* (1995), p. 14.4)

ሌላው የሚያገርመው ነገር ደግሞ፣ በአገልግሎቱ ጊዜ የሆነው ነገር ነው፡- "በየማለዳው በሰማይ ካለው አባቱ ጋር በፀሎት ይነጋገር ነበር፡፡ **በየዕለቱ ከአባቱ አዲስ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት [ሙላት] ይቀበል ነበር።**" (E.G. White, *Signs of the Time*, Nov. 21, 1895) የሱስ በየቀኑ አዲስ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት (ሙላት) ካስፈለገው፤ እኛ ደግሞ ከዚያ በበለጠ ነው የሚያስፈልገን!

## የመዝጊያ ሃሳቦች

በየትኛውም የሕይወት ሁኔታዎች ውስጥ ብንሆን፣ መንፈስ ቅዱስ አስደናቂ መሪያችንና እንደ ክብሩ ባለጠግነት ኃይል ሰጪችን ነው።

መንፈስ ቅዱስ ባህሪያችንን ይቀርጻል፣ ጠቃሚ የእግዚአብሔር አገልጋዮችም ያደርገናል። በየዕለቱ ራሳችንን ለጌታ ስናስገዛና በመንፈስ ቅዱስ ስንጠመቅ ሕይወታችን ሙሉ በሙሉ ይለወጣል።

ጌታ፣ በምድር ታሪክ ውስጥ እጅግ በጣም ታላቅ ለሆነው ክስተት ሊያዘጋጀን ይፈልጋል። እያንዳንዳችን በግል ለዳግም ምጻቱ እንድንዘጋጅና በመንፈስ ቅዱስ ኃይልም የወንጌልን ሥራ በጋራ በመሥራት እንድናጠናቅቅ ይፈልጋል። ከፊታችን ባሉት አስከፊ ጊዜያት በድል አድራጊነት ሊመራን ይፈልጋል።

በየቀኑ ራሳችሁን ለጌታ እያስገዛችሁ፣ በየዕለቱ በመንፈስ ቅዱስ እየተሞላችሁ የግል መነቃቃትንና ተሃድሶን ተለማመዱ!

በአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስና ስለ መነቃቃት ጸሎት በማድረግ ጽሑፌን ልጨርስ፦

*"በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፥ ፊቴንም ቢፈልጉ፥ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፥ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፥ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፥ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ።" (2ኛ ዜና 7:14)*

ጸሎት፦ በሰማይ ያለህ አባት ሆይ፦ የትህትናን ባህሪ እባክህ ስጠን (ሚክያስ 6፡8)። እንድንጸልይና ፊትህን እንድንፈልግ በልቦቻችን ውስጥ ታላቅ ፍላጎትን አስቀምጥ። ከክፉ መንገዶቻችን እንድንመለስ እርዳን፣ የመመለስ ፈቃደኝነትም እንዲኖረን አድርግ። ቀድመን ልናሟላ የሚገባን ነገር ቢኖር አንተ እንድታሟላልንና በቃል ኪዳንህም መሠረት የፀሎታችንን መልስ እንድንለማመድ እርዳን። ኃጢአታችንን ይቅር በለን፤ ከለብታነት ሕይወትና ከክህደት ፈውሰን። በየዕለቱ ራሳችንን ለየሱስ እንድናስገዛና በእምነትም መንፈስ ቅዱስን እንድንቀበል እባክህ አግዘን። አሜን!

**"መንፈሳዊ መነቃቃትን የምናገኘው በፀሎት መልስ በኩል ብቻ ነው።"** (E.G. White, *Selected Messages, Book 1* (1958), p. 121.1) **"ልክ በጴንጤቆስጤ ቀን በነበረው አይነት መንፈስ ቅዱስ ሲወርድልን፣ ብዙ አስደናቂ ሥራዎችን እንድንሠራ የሚያችለንን መንፈሳዊ መነቃቃትን እናገኛለን።"** (E.G. White, *Selected Messages, Book 2* (1958), p. 57.1)

## 777 ዓለም አቀፉ የጸሎት ሰንሰለት (Global Prayer Chain)

‘777’ ምንድነው? ቀንና ማታ የሚፀለይበት ዓለምአቀፋዊ የፀሎት ሰንሰለት ነው። የመንፈስ ቅዱስ መገኘት በቤተሰባችን፣ በቤተ-ክርስቲያናችንና፣ በአገልግሎታችን እንዲኖር፣ የእግዚአብሔር ህዝቦች በሳምንት 7 ቀናት፣ ዘወትር ጠዋት በ1:00 ሰዓት [በፈረጆቹ 7:00am] እና ማታ በ1:00 ሰዓት [በፈረጆቹ 7:00pm] ይፀልያሉ። አንድ ሰው በየትኛውም አገር ቢኖር፣ በተቀጠረት ሰዓት ሲፀልይ በተለያየ የሰዓት ክልል ውስጥ ከሚገኙ በሺዎች ከሚቆጠሩ ክርስቲያኖች ጋር በአንድነት ይጸልያል ማለት ነው።

“ከልባቸው የሚፀልዩ ምእመናን፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ በፀሎት ሰንሰለት ተያይዘው የመንፈስ ቅዱስ ሙላትን ለመቀበል መፀለይ ይኖርባቸዋል፡፡” (ሪቪው ኤንድ ሔራልድ፣ ጥር 3 /1907) *www.revivalandreformation.org*

# ተጨማሪ መግለጫ

## ለተጨማሪ ጥናት የሚጠቅሙ ሃሳቦች

ጠቃሚ የሆነ ምክር:- ከቻላችሁ ይህችን ትንሽ መጽሐፍ ለስድስት ቀን ያህል በየቀኑ አንብቧት። አንድ ትምህርታዊ ጥናት እንዳረጋገጠው ከሆነ:- ለሕይወታችን እጅግ ጠቃሚ የሆነ ትምህርትን በትክክል ለማስተዋል ከስድስት እስከ አስር ጊዜ ደግሞ ደጋግሞ ማንበብ ወይም ማዳመጥ አስፈላጊ ነው። እስቲ ሞክሩት። ውጤቱ በርግጠኝነት ያሳምናችኋል።

አንዲት መምህርት ሞክራዋለች:- “እነዚህ የሚያደፋፍሩ ቃላቶች ማርከውኛል:-

ይህን በግሌ መለማመድ እፈልግ ነበር፡፡ በሦስተኛው ንባብ ዙር መካከል ልቤ ተማረከ፤ በመላ ሕይወቴ ዘመን ስናፍቀው የነበረው ለአዳኜ ያለኝ ታላቅ ፍቅር ተቀሰቀሰ። ይህችን ትንሽዬ መጽሐፍ በሁለት ወራት ውስጥ ስድስት ጊዜ ያህል አነበብኩ፤ ውጤቱም ታላቅ ነበር። የሱስ ወደኛ ቀረብ ብሎ ሲመጣና ንጹህ፣ ሩሩህና አፍቃሪ ዓይኖቹን መመልከት እንዴት የሚያስደንቅ እንደሚሆን የመገመት አይነት፣ እንደዚያ ነበር የተሰማኝ። በአዳኜ ያገኘሁትን ይህንን ደስታ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ማጣት አልፈለግሁም።” *(ሲ. ፒ.)*

ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ስላገኙት አዲስ ሕይወት የሚገልጹ ብዙ የምሥጋናና በአድናቆት የተሞሉ ምስክርነቶች ደርሰውኛል። እነዚህን ምስክርነቶች የላኩልኝ (አብዛኞቹ ማለት ይቻላል) ይህችን ትንሽዬ መጽሐፍ በትጋት እና በተደጋጋሚ ያነበቡ ናቸው።

### በርዕሱ ዙሪያ የተጻፉ ሌሎች ስነ-ፅሁፎች

- *40 Days[Book 1] Prayers and Devotions to Prepare for the Second Coming,* Dennis Smith, Reviewand Herald, 2009
- *40 Days [Book 2] Prayers and Devotions to Revive your Experience with God,*

Dennis Smith, Review and Herald, 2011

- *40 Days [Book 3] God's Health Principles for His Last-Day People,* Dennis Smith, Review and Herald, 2011
- *40 Days [Book 4] Prayers and Devotions on Earth's Final Events,* Dennis Smith, Review and Herald 2013
- *If My People Pray –An Eleventh-Hour Callto Prayer and Revival,* Randy Maxwell, Pacific Press 1995
- *Revive Us Again,* Mark A. Finley, Pacific Press 2010
- *How to Be Filled With the Holy Spirit und Know it,* Garrie F. Williams, Review and Herald 1991
- *The Radical Prayer,* Derek J. Morris, Review and Herald 2008

## የ40 ቀን መጽሐፍ የጥናት መምሪያ

የ<40 ቀን የፀሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ> በቤተ-ክርስቲያናቸው ለማዘጋጀት ለሚፈልጉና ይህን በዴኒስ ስሚዝ የተጻፈውን መጽሐፍ ካነበባችሁ በኋላ የወንጌል ጥረትን ለማድረግ የምታስቡ አገልጋዮች በ www.SpiritBaptism.org ድረ ገጽ አጋዥ ጽሑፎችን ማግኘት ትችላላችሁ።

## ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የመኖር አዲስ ልምምድ

ጌታችን የሱስ እንዲ ብሏል:- *" ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ"* (የሐዋሪያት ሥራ 1:8)

**ወንድማዊ ትብብር ከአንባቢዎች**:- በግል የክርስትና ሕይወታችሁ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በምታደርጉት የእምነት ጉዞ የተለማመዳችኋቸው ልዩ ልምምዶች (ምስክርነቶች) ካላችሁ:- ይህንን ምስክርነታችሁን ለ Helmut Haubeil በ*ሚሽን ብሪፍ መጽሔት* (በጀርመን የሚገኝ የሚሽን መጽሔት) ማካፈል እንዲችል ምስክርነቶቻችሁን በአጭር ጽሑፍ ብትልኩልን ደስ ይለናል። ስማችሁን በመጽሔቱ ውስጥ መጥቀስ ይፈቀድ ወይም አይፈቀድ መግለጻችሁን አትርሱ! የእናንተ ልምምዶች ሌሎች ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የሚያደርጉትን ጉዞ ወይም ላልጀመሩት ደግሞ እንዲጀምሩ ሚያጠነክር መሆኑን አስተዉሉ።

**Contact:**
Helmut Haubeil
Rosenheimerstr. 49
D-83043 Bad Aibling / Oberbayern, Germany
E-Mail: helmut@haubeil.net
Language: German or English

ማስታወሻ

# ወደ የግል መንፈሳዊ መነቃቃት የሚመራ መንገድ

**ሄልሙት ሃውባይል** በቢዝነስ ማኔጅመንት እና በፓስተርነት ሙያ የተመረቁ የጌታ አገልጋይ ናቸው። በአንድ የአስመጪና ላኪ ኩባንያ ውስጥ በዋና ወኪልነትና ሥራ አስፈጻሚነት ሥራ ውጤታማ የሥራ ጊዜያቸውን ካሳለፉ በኋላ በ37 ዓመት እድሜአቸው ለእግዚአብሔር የአገልግሎት ጥሪ ምላሽ በመስጠት ለ16 ዓመታት ያህል ጌታን በተለያዩ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት በፓስተርነት ሲያገለግሉ ቆይተዋል። ከዚያም በ ባድ አይብሊንግ ከተማ የሚገኘውን የአዛውንቶች መኖሪያ በሥራ አስኪያጅነት ሲመሩ ቆይተዋል። ሄልሙት ሃውባይል „ሚሲዮንስብሪፍ“ የተሰኘ በጀርመንኛ ቋንቋ የሚዘጋጅ መንፈሳዊ መጽሔት መስራችና አሳታሚ ናቸው። ጡረታ ከወጡ ጀምሮ በአብዛኛው በመካከለኛው እስያ እና በህንድ አገር ውስጥ የወንጌል አገልግሎት ስርጭት እንዲስፋፋ አስተዋጽዖ በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

**“ኃይልን እንደሚሰጠን እያወቅን ለምንድን ነው መንፈስ ቅዱስን የማንራበው እና የማንጠማው? ለምንድንስ ነው ስለ መንፈስ ቅዱስ የማናወራው፣ እንድንሞላ የማንጸልየው፣ ዘወትር የማንሰብከው?”**

ኤለን ጂ ኋይት፣ ቴስቲሞኒሰ ፎር ዘ ቸርች፣ ቮልዩም 8. ገጽ 22